አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሙዩኒኬሽን ኮሌጅ
የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል
የድህረ ምረቃ መረሐ ግብር

# በግጥም አማካይነት በአማርኛ የአንብቦ መረዳትና የጽሕፈት ችሎታን ማዳበር፤ በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ሙከራዊ ጥናት

በ
ነብዩ ጋሹ

ሰኔ /2005 ዓ.ም.
አዲስ አበባ

# በግጥም አማካይነት በአማርኛ የአንብቦ መረዳትና የጽሕፈት ችሎታን ማዳበር፤ በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ሙከራዊ ጥናት

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሙዩኒኬሽን ኮሌጅ
የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል
የድህረ ምረቃ መረሐ ግብር

ለ ተግባራዊ ስነ ልሳን አማርኛን ለማስተማር ኤም.ኤ. ዲግሪ
ማሟያ የቀረበ ጥናት

በ
ነብዩ ጋሹ

ሰኔ /2005 ዓ.ም.

## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሙዩኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

## የድህረ ምረቃ መረሐ ግብር

# በግጥም አማካይነት በአማርኛ የአንብቦ መረዳትና የጽሕፈት ችሎታን ማዳበር፤ በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ሙከራዊ ጥናት

በ

ነብዩ ጋሹ

ሰኔ /2005 ዓ.ም.

**የፈተና ቦርድ አባላት**

| | |
|---|---|
| የአማካሪ ስም | ፊርማ |
| የውስጥ ፈታኝ ስም | ፊርማ |
| የውጭ ፈታኝ ስም | ፊርማ |

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS
LIBRARY

# ምስጋና

በመጀመሪያ ይህን ጥናታዊ ጽሑፍ ሳካሂድ ጽሑፌን በማረም፣ በማስተካከል፣ ጠቃሚና ምሁራዊ ሀሳቦችን በመስጠት ከፍተኛ እገዛና ድጋፍ ላደረጉልኝ አማካሪዬ አቶ ደረጀ ገብሬ (ረዳት ፕሮፌሰር) ከፍ ያለ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡

ይህን ጥናት ለማከናወን እንድችል ክፍለ ጊዜ በመፍቀድ ለተባበሩኝ ለደምበጫ ከፍተኛ ትምህርት መሰናዶና አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ም/ር/መምህር ለአቶ ሽባባው በቀለ እንዲሁም እገዛቸውና ቀና ትብብራቸው ላልተለየኝ የት/ቤቱ የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህርት ለወ/ሮ ፍቅርተ አሰፋ ከፍተኛ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡ በጥናቱ ወቅት የሚሰጣቸውን መመሪያና ትዕዛዝ በማክበር ለጥናቴ መሳካት ትልቅ አስተዋጽኦ ላበረከቱልኝ ለ$9^{25}$ እና ለ$9^{29}$ ክፍል ተማሪዎች ትምህርታችሁን ይግለጽላችሁ እላለሁ፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የመልመጃዎችን ግልጽነት በመገምገም፣ የተማሪዎችን የቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተና በማረም እንዲሁም ስታትስቲካዊ ስሌቶችን ስሰራ የተባበሩኝን ጓደኞቼን ላመሰግን እወዳለሁ፡፡

በመጨረሻም ሁሌም በጸሎት ላልተለየችኝና አባትም እናትም ሆና ላሳደገችኝ ጠንካራዋ እናቴ ወ/ሮ የኔነሽ አላምረው፣ በትምህርት ቆይታየና ጥናቴን በማካሂድበት ወቅት የማበረታቻና የሞራል ድጋፋቸው ላልተለየኝ ውድ እህቶቼ የኔወርቅ ጋሹና ሜሮን ጋሹ እንዲሁም እጅግ በጣም ለማፈቅራት ጓደኛዬ ፀደኒያ ልመንህ ከልቤ የማይጠፋ ከባድ ውለታ አለብኝና ውለታ መላሽ ያድርገኝ፡፡

# ማውጫ

ርዕስ ገፅ

ምስጋና ........ i
ማውጫ ........ ii
የሰንጠረዥ ማውጫ ........ v
አጠቃሎ ........ vi
ምዕራፍ አንድ ........ 1
1. መግቢያ ........ 1
1.1 የጥናቱ ዳራ ........ 1
1.2 የጥናቱ አላማ ........ 4
1.3 የጥናቱ ጠቀሜታ ........ 5
1.4 የጥናቱ ወሰን ........ 6
1.5 የመሰረታዊ ጽንሰ ሀሳቦች ና የቁልፍ ቃላት ብያኔ ........ 6
ምዕራፍ ሁለት ........ 9
2. ክለሳ ድርሳናት ........ 9
2.1 ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት ........ 9
2.1.1 የግጥም ምንነት ........ 9
2.1.2 የግጥም ባህሪያት ........ 11
2.1.3 ግጥም አማርኛ ቋንቋን ለማስተማር ያለው ሚና ........ 14
2.1.4 ተማሪዎች ግጥምን በሚያነቡበት ጊዜ ሊያጋጥሟቸው የሚችሉ መሰናክሎች ........ 14
2.1.5. የግጥማዊ ስራዎች አመራረጥ ........ 16
2.1.6 ቋንቋን መሰረት ያደረጉ ስነ ዘዴያዊ አቀራረቦች ........ 20
2.1.7 ፈጠራዊ የቋንቋ ማስተማር ዘዴ ........ 23
2.1.8 በፈጠራዊ ዘዴ ግጥምን በምንጭነት ተጠቅሞ ቋንቋን በማስተማር ሂደት የመምህሩ ሚና ........ 26
2.1.9 ከአንድ አሀድ ውስጥ የሚዘጋጁ መልመጃዎች አይነትና ባህሪያት ........ 30
2.1.9.1 የመልመጃዎች ባህሪያት ........ 30
2.1.9.2 የመልመጃዎች አይነት ........ 32

2.2 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ....................................................................... 35
ምዕራፍ ሶስት .................................................................................................. 40
3. የጥናቱ ዘዴ .................................................................................................... 40
3.1 የት/ቤትና የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ ................................................... 40
3.1.1 የት/ቤት አመራረጥ ........................................................................... 40
3.1.2 የተማሪዎች አመራረጥ ....................................................................... 40
3.2 የግጥሞች አመራረጥ፣ የፈተናዎችና የመልመጃዎች አዘገጃጀት ........................ 41
3.2.1 የግጥሞች አመራረጥ ......................................................................... 41
3.2.2 የመልመጃዎችና የፈተናዎች አዘገጃጀት ................................................... 42
3.3 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች .............................................................. 43
3.3.1 የፈተና አሰጣጥ ............................................................................... 43
3.3.2 የፈተና አስተራረም ........................................................................... 43
3.3.3 የጽሑፍ መጠይቅ ............................................................................. 44
3.4 የመረጃ አተናተን ስልት ......................................................................... 44
ምዕራፍ አራት .................................................................................................. 45
4. የማስተማር ሂደትና የመረጃዎች ትንተና ........................................................... 45
4.1. የማስተማር ሂደት ................................................................................. 45
4.2. የመረጃዎች ትንተና ............................................................................... 59
4.2.1. የቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናዎች ውጤት ትንተና ................................ 59
4.2.1.1. የቅድመ ትምህርት ፈተና ውጤት ትንተና ......................................... 59
4.2.1.2. የድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት ትንተና ......................................... 61
4.2.2. የጽሑፍ መጠይቅ መረጃዎች ትንተና .................................................... 64
ምዕራፍ አምስት ................................................................................................ 79
5.ማጠቃለያና አስተያየት ................................................................................... 79
5.1 ማጠቃለያ .............................................................................................. 79
5.2 አስተያየት .............................................................................................. 80
ዋቢ ጽሑፎች .................................................................................................... 83
አባሪ አንድ ....................................................................................................... 87

አባሪ ሁለት ....94
አባሪ ሶስት ....99
አባሪ አራት ....103
አባሪ አምስት ....105
አባሪ ስድስት ....107
አባሪ ሰባት ....109
አባሪ ስምንት ....111
አባሪ ዘጠኝ....113
አባሪ አስር ሀ....114
አባሪ አስር ለ....115
አባሪ አስራ አንድ ሀ ....116
አባሪ አስራ አንድ ለ....117

## የሰንጠረዥ ማውጫ


| ርዕስ | ገፅ |
|---|---|
| ሰንጠረዥ 1፡- በሶስት አራሚዎች ለሁለቱም ቡድኖች የተሰጡ የቅድመ ትምህርት ፈተና ውጤቶች አማካይና መደበኛ ልይይት .......................... | 60 |
| ሰንጠረዥ 2፡- የሁለቱ ቡድኖች የቅድመ ትምህርት ፈተና ውጤት በቲ- ቴስት ቀመር ሲሰላ .......................... | 61 |
| ሰንጠረዥ 3፡- በሶስት አራሚዎች ለሁለቱም ቡድኖች የተሰጡ የድህረ ትምህርት ፈተና ውጤቶች አማካይና መደበኛ ልይይት .......................... | 62 |
| ሰንጠረዥ 4፡- የሁለቱ ቡድኖች የድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት በቲ- ቴስት ቀመር ሲሰላ .......................... | 63 |
| ሰንጠረዥ 5፡- የተማሪዎችን ዳራ የሚያሳይ .......................... | 64 |
| ሰንጠረዥ 6፡- ተማሪዎች ከትምህርቱ በፊት የነበራቸውን ስነ ጽሑፋዊ እውቀት ለማወቅ የቀረበ .......................... | 65 |
| ሰንጠረዥ 7፡- ተማሪዎች ግጥሞችን አንብበው በሚወያዩበት ወቅት የተሰማቸውን ስሜት ለማወቅ የቀረቡ .......................... | 68 |
| ሰንጠረዥ 8፡- በግጥም አማካይነት አማርኛ ቋንቋን በመማራቸው ስላገኟቸው ጠቀሜታዎች ለማወቅ የቀረበ .......................... | 70 |
| ሰንጠረዥ 9፡- ለመጠይቅ ጥያቄ ቁጥር 15 የተሰጠ ምላሽ .......................... | 71 |
| ሰንጠረዥ 10፡- ተጠኝ ተማሪዎች በግልም ሆነ በቡድን በግጥም አማካይነት አማርኛ ቋንቋን ሲማሩ ያልተደሰቱበት ነገር ካለ ለማወቅ .......................... ከቀረቡ ጥያቄዎች የተገኙ ምላሾች | 72 |
| ሰንጠረዥ 11፡- ለመጠይቅ ጥያቄ ‹‹16›› የተሰጠ ምላሽ .......................... | 74 |

# አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዋነኛ አላማም በደምበጫ ከፍተኛ ትምህርት መሰናዶና አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የሚማሩ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎችን በአማርኛ የአንብቦ መረዳትና የጽሕፈት ችሎታን ለማዳበር ግጥም ያለውን ሚና በሙከራ ማረጋገጥ ነው። ጥናቱም በደምበጫ ከፍተኛ ትምህርት መሰናዶና አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ከሚማሩ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች መካከል በሁለት ክፍል የሚገኙ 116 ተማሪዎችን (በየክፍሉ 58 ተማሪዎችን) በእጣ የናሙና ዘዴ ተመርጠው ጥናቱ ተካሂዷል። እነዚህ ሁለት ቡድኖች በቁጥጥርና በተጠኝነት የተያዙ ናቸው። በቁጥጥር የተያዙት በመደበኛዋ መምህርት እንዲማሩ ሲደረግ በተጠኝነት የተያዙት ደግሞ በአጥኝው እንዲማሩ ተደርጓል። ጥናቱ በዋናነት መጠናዊ የአጠናን ዘዴን የተከተለ ሲሆን የጥናቱን ውጤት በቁጥር ለመግለጽ ሲባልም የሁለት ቡድን ቅድመ ትምህርትና ድህረ ትምህርት ፈተና ተግባራዊ ሆኗል። ከዚህ በተጨማሪም የአይነታዊ ዘዴ አካል የሆኑት የጽሑፍ መጠይቅና ኢ. መደበኛ በሆነ መልኩ የቀረበ ቃለ መጠይቅ በአጋዥነት አገልግለዋል። ሁለቱም ቡድኖች የቅድመ ትምህርት ፈተና ከተፈተኑ በኋላ በተመሳሳይ ግጥሞች በተለያየ ዘዴ ለአራት ተከታታይ ሳምንታት እንዲማሩ ተደርጓል። የሙከራ ትምህርቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ደግሞ የድህረ ትምህርት ፈተና ተፈትነዋል። ተጠኝ ቡድኖች የመማር ማስተማር ሂደቱን አስመልክቶ አስተያየታቸውን እንዲሰጡ ታስቦ የጽሑፍ መጠይቅ እንዲሞሉ የተደረገ ሲሆን ኢ. መደበኛ ቃለ መጠይቅም ተደርጎላቸዋል። በዚህ መሰረት የቅድመ ትምህርት ፈተና ውጤቱ እንደሚያመለክተው በሁለቱ ቡድኖች መካከል ሰፊ ልዩነት የለም። ነገር ግን በድህረ ትምህርት ፈተናው የተገኘው ውጤት እንደሚያሳየው በሁለቱ ቡድኖች መካከል የጎላ ልዩነት ታይቷል። ይኸውም በአዲሱ ዘዴ (በፈጠራዊ ዘዴ) የተማሩት የተጠኝ ቡድን ተማሪዎች በተለመደው ዘዴ እንዲማሩ ከተደረጉት የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች የተሻለ ውጤት አስመዝግበዋል። ከተጠኝ ቡድኖች የጽሑፍ መጠይቅና ኢ. መደበኛ ቃለ መጠይቅ የተገኘው መረጃ እንደሚጠቁመው ደግሞ ተማሪዎች በፈጠራዊ ዘዴ በግጥም አማካይነት አማርኛ ቋንቋን በመማራቸው ደስተኞች ናቸው። ከዚሁ ጋር አያይዘውም በትምህርቱ ሂደት ያዩአቸውን ችግሮች ጠቁመዋል። በአጠቃላይ ከጥናቱ ግኝት በመነሳት የተለያዩ አስተያየቶች ቀርበዋል።

# ምዕራፍ አንድ

# 1. መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

ቋንቋን ለማስተማር ስነ ጽሑፍን መሳሪያ ማድረግ የተጀመረው እ.ኤ.አ. በ1980ዎቹ ውስጥ ነበር፡፡ ይህ ደግሞ የቋንቋ ትምህርት ከተጀመረበት ጊዜ አንጻር ሲታይ እጅግ በጣም አጭር እድሜ ያለው መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ ከተጠቀሰው ጊዜ ወዲህ ግን በባለሙያዎች በተደረገ ምሁራዊ ክርክር ምክንያት በተለይ እንግሊዝኛን በሁለተኛና በውጭ ቋንቋነት በማስተማር ተግባር ስነ ጽሑፍ ጉልህ አስተዋጽኦ እንዲኖረው ተደርጓል (Carter and Long, 1991፡ 1)፡፡

ምንም እንኳን የመስኩ ባለሙያዎች ስነ ጽሑፋዊ ስራዎችን ተጠቅሞ ቋንቋን ማስተማር አስፈላጊ መሆኑን ቢያትቱም በሌላ መልኩ ተቃውሞ የሚሰነዝሩም አልታጡም፡፡ Mckay (1986፡ 191) በስነ ጽሑፍ አማካይነት ቋንቋን የማስተማር ሂደትን የሚቃወሙ ወገኖች የሚያቀርቧቸውን የመከራከሪያ ሀሳቦች በተመለከተ የሚከተለውን ብለዋል፡፡

- ቋንቋን ስናስተምር ዋነኛ አላማችን ሰዋስዋዊ ህጎችን ማስተማር ነው። በአንጻሩ ስነ- ጽሑፋዊ ስራዎች ከዘወትራዊው የመግባቢያ ቋንቋ ያፈነገጠ አጠቃቀም ስለሚከተሉና ሰዋስዋዊ የመዋቅር ውስብስብነት ስለሚታይባቸው የሰዋስው ህጎችን ለማስተማር አያስችሉም፡፡
- ስነ ጽሑፋዊ ጥናት ራሱን ችሎ ሊካሄድ የሚችል ተግባር በመሆኑ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የትምህርቱን አላማና ተግባር ለማሳካት ምንም አይነት አስተዋጽኦ አይኖረውም፡፡
- ስነ ጽሑፍ የማህበረሰቡ ባህላዊ ጉዳዮችን የሚያሳውቅ በመሆኑ ለተማሪዎች ከባድ ሊሆን ይችላል፡፡

ይሁን እንጂ ስነ ጽሑፍ ቋንቋን በማስተማር ሂደት ውስጥ ካለው ጉዳት ይልቅ ያለው ሚና ላቅ ያለ ነው፤ በማለት በርካታ የመስኩ ምሁራን ይከራከራሉ፡፡ ስነ ጽሑፍ ቋንቋን

ለማስተማር ያለውን ፋይዳ በተመለከተም የተለያዩ ምሁራን የሰነዘሯቸውን የተለያዩ አስተያየቶች ከዚህ እንደሚከተለው እንመልከት፡፡

እንደ (Lazar, 1993፡ 15) አገላለጽ ስነ ጽሑፍ ቋንቋን በማስተማር ረገድ ያለው ጠቀሜታ እጅግ ከፍተኛ ነው፡፡ ተማሪዎች በከፍተኛ ደረጃ እንዲነሳሱ የማድረግ፣ የሌሎችን ባህሎች እንዲያውቁ የማድረግ፣ ቋንቋን እንዲማሩ የመገፋፋት፣ ሀሳባቸውንና ስሜታቸውን እንዲገልጹ የማበረታታት፣ የቋንቋ ግንዛቤያቸውን እንዲያሳድጉ የማድረግ፣ እየተዝናኑ እንዲማሩ የማድረግ ወዘተ. እምቅ አቅም ያለው የቋንቋ ማስተማሪያ ምንጭ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ስነ ጽሑፍ ቋንቋን ለማስተማር የሚያስችል እውነተኛ መሳሪያ ነው ፡፡

Hill (1986: 7-9) በበኩላቸው ስነ ጽሑፍን በቋንቋ ትምህርት ውስጥ መጠቀም አስፈላጊ የሚሆንባቸውን ምክንያቶች በተከታዮቹ ሶስት ነጥቦች ለማስረዳት ይሞክራሉ፡፡

አውድ ከሳችነት፡- የቋንቋ ትምህርቱን በእውነተኛ አውድ ለማስተማር ወይም ከተማሪዎች እለታዊ ህይወት ጋር አጣጥሞ በማቅረብ ተማሪዎች በፊት የሚያውቁትን እንዲያዳብሩና ቋንቋውንም የራሳቸው እንዲያደርጉት የበኩሉን ሚና ይጫወታል።

ተግባቦት አጎልባችነት፡- ተማሪዎች በራሳቸው ጊዜ ቋንቋውን በአውዱ በመገልገል ተግባቦት እንዲፈጥሩና ከክፍል ውጪም እንዲጠቀሙበት በር ይከፍትላቸዋል።

ተነሳሽነት ፈጣሪነት፡- የሚቀርቡ ልዩ ልዩ የስነ ጽሑፍ ስራዎች ተማሪዎችን ከተለያዩ ሰዎች ባህልና የህይወት ልምድ ጋር እንዲተዋወቁ ያደርጋቸዋል፡፡ ይህም ሂደት በተማሪዎች ላይ የመዝናናት ብሎም የማድነቅ ስሜትን ስለሚፈጥር ለትምህርቱ ያላቸው ጉጉት እንዲጨምር ያደርጋል።

> *ለቋንቋ ትምህርት መዳበር ስነ ጽሑፍ ጉልህ ድርሻ አለው፡፡ በአንድ ስነ ጽሑፍ ውስጥ የሚገኙ ቃላት የተመረጡ ናቸው፡፡ በቃላቱ የተፈጠረው ሀሳብም በተለያዩ ዘይቤዎች፣ ፈሊጣዊና ምሳሌያዊ አነጋገሮች ...ወዘተ. የበለጸገ ሊሆን ይችላል፡፡ ሀሳቡ የተዋቀረባቸው ዐ.ነገሮች የተለያዩ አውዳዊ ፍቺዎችን የሚገልጹ ሆነው ሊመሰረቱ ይችላሉ፡፡ በመሆኑም የመልዕክቱ ፍቺ በቀላሉ አይገኝም፤የመራምራል፡፡ የሀሳቡን ምንነት ለመረዳት ከብዙ አቅጣጫ እንዲመለከቱት ያስገድዳል፡፡ በዚህ ሂደት የሚደረገው ጥረትም በርካታ የቋንቋ መዋቅራዊ ህጎችንና ክሂሎችን ለመማር ይረዳል (ፈቃደ፣ 1991፡ 111)፡፡*

ከዚህ በተጨማሪ በድሉ (1996፡ 7) ይህንኑ ጉዳይ በተመለከተ ተከታዩን ብለዋል፡፡

> *የስነ ጽሑፍ ስራን አስመልክቶ በተማሪዎች መካከል የሚደረግ ውይይት ተማሪዎችን ስለሚስብ የተሳታፊነታቸውን ደረጃ ከፍ ያደርገዋል። ድራማዎችን ሲሰሩ፣ ግጥሞችንና አጫጭር ታሪኮችን ሲያነቡ የመናገርና የማንበብ ክሂላቸው ይዳብራል። ከሁሉም በላይ ደግሞ ስነ ጽሑፍ በባህሪው ሳቢ ስለሆነ ተማሪው በስነ ጽሑፍ ስራ ላይ ተመስርቶ ክሂሎቹን ለማዳበር በሚከናወኑ ልምምዶች ላይ ለመሳተፍ በአብዛኛው ውጫዊ ግፊት አይፈልግም፤ ስለ ስነ ጽሑፍ መናገር ይፈልጋል፤ ስነ ጽሑፍ መፃፍ ይፈልጋል፤ ስነ ጽሑፍን ማዳመጥ ይፈልጋል።*

ከዚህ እንደምንረዳው ስነ ጽሑፋዊ ስራዎች ሳቢና ማራኪ የቋንቋ አጠቃቀም፣ አስደሳች ታሪክ እና ልዩ ልዩ ማህበራዊ ክስተቶችን ያዘሉ በመሆናቸው የተማሪዎችን ፍላጎት ያነሳሳሉ፤ እያዝናኑ የቋንቋ ክሂሎችን ለማዳበርም ከፍተኛ ሚና አላቸው።

ከላይ ከተዘረዘሩት ጠቀሜታዎች በተጨማሪ በድሉ (1996፡ 8-9) ስነ ጽሑፋዊ ስራዎች የታላሚውን ቋንቋ ተናጋሪ ማህበረሰብ ባህል ለማወቅ አይነተኛ መሳሪያዎች በመሆናቸው በስርዓተ ትምህርት ውስጥ መካተት እንዳለባቸው በሚከለተው መልኩ ይገልፃሉ።

> *ባህልን ከቤተሰብ መማር ይቻላል፡፡ ከቤተሰብ የማይገኙት ባህላዊ እሴቶች ደግሞ በማህበራዊ ተራክቦና በመደበኛ ትምህርት ይገኛሉ፡፡ ይሁን እንጂ አንዳንድ ጊዜ ከሶስቱ (ቤተሰብ፣ ህብረተሰብ፣ ትምህርት ቤት) በአንዱ ቦታ ክፍተት ይፈጠራል፡፡... ስነ ጽሑፍ ይህንን ክፍተት ለመሙላት አይነተኛ መሳሪያ ነው፡፡ ተማሪዎች ከቤተሰብ ወይም ከህብረተሰብ የሚያጡትን ባህላዊ እሴት ከስነ ጽሑፍ ያገኙታል፡፡*

እነዚህ ከላይ የቀረቡትን የምሁራን ሀሳቦች መነሻ በማድረግ የዚህ ጥናት የትኩረት አቅጣጫም አማርኛ ቋንቋን በማስተማር ሂደት ግጥምን በምንጭነት መጠቀም ምን አይነት ሚና ሊኖረው እንደሚችል በሙከራ ማረጋገጥ ነው፡፡

አጥኚው ይህንን ጥናት ለማጥናት ካነሳሱት ምክንያቶች መካከል አንደኛው ግጥም አማርኛ ቋንቋን በማስተማር ሂደት ያለውን ሚና በሚመለከት የተሰሩ ጥናቶች አለማግኘቱ ነው፡፡ ይህ ክፍተት መኖሩ ግጥም በአማርኛ የአንብቦ መረዳትና የጽሕፈት ችሎታን ለማዳበር ያለውን ሚና በተግባር፣ በሙከራ የማረጋገጥ ፍላጎቱን ከፍ በማድረግ ጥናቱን እንዲያካሂድ በከፍተኛ ሁኔታ አጥኚውን አነሳስቶታል፡፡

ለዚህ ጥናት እንደሁለተኛ አነሳሽ ምክንያት ሊጠቀስ የሚችለው አጥኚው ‹‹ሥነ-ፅሁፍ አማርኛ ቋንቋን በማስተማር ሂደት ውስጥ›› የሚለውን ኮርስ መማሩ እና በትምህርቱ ሂደትም በጉዳዩ ላይ ሁሉም ተማሪ የተለያዩ ስራዎችን አቅርቦ ሞቅ ያለ ውይይትና ክርክር መደረጉ የነበረውን ዕውቀትና ግንዛቤ እንዲሰፋ ማድረጉ ነው፡፡ በመሆኑም አጥኚው አማርኛ ቋንቋን በማስተማር ሂደት ግጥም ምን ሚና ይኖረዋል፣ አመራረጡ፣ አተገባበሩ … ወዘተ. እንዴት መሆን አለበት፤ የሚሉትን ጉዳዮች ሊጠቁም የሚችል ሙከራዊ ጥናት ለማካሄድ ተነሳሳ፡፡

እነዚህን ነጥቦች መነሻ በማድረግም ይህ ጥናት ተከታዮቹን አንኳር ጥያቄዎች እንደሚመልስ ይጠበቃል፡፡

1. አብዛኛው የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ሀሳብን በጽሑፍ የመግለጽና አንብቦ የመረዳት ችግር ይታይባቸዋል፡፡ ይህ ሀሳብን በጽሑፍ የመግለጽና አንብቦ የመረዳት ችግር መንስኤው ምንድን ነው?
2. እነዚህን በተማሪዎች ላይ የሚታዩ ውስንነቶች ለማቃለል ብሎም ለማስወገድ ስነ ጽሑፍ በተለይም ግጥም ምን ሚና ሊኖረው ይችላል?
3. ግጥምን ተጠቅሞ ቋንቋን ለማስተማር ሲታሰብ ግጥምን እንዴት መምረጥና ማቅረብ ወይም መተግበር ይቻላል?

## 1.2 የጥናቱ አላማ

የዚህ ጥናት ዋነኛ አላማ በደምበጫ ከፍተኛ ትምህርት መሰናዶና አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የሚማሩ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎችን በአማርኛ የአንብቦ መረዳትና የጽሕፈት ችሎታ ለማዳበር ግጥም ያለውን ሚና በሙከራ ማረጋገጥ ነው፡፡ ዝርዝር አላማዎች ደግሞ ተከታዮቹ ናቸው፡፡

1. ተማሪዎች በግጥም አማካይነት በፈጠራዊ ዘዴ አማርኛ ቋንቋን ከተማሩ በኋላ አንብቦ የመረዳት ክሂላቸው ማደግ አለማደጉን ማረጋገጥ፡፡
2. ተማሪዎች በፈጠራዊ ዘዴ በግጥም አማካይነት አማርኛ ቋንቋን ከተማሩ በኋላ የጽሕፈት ክሂላቸው መዳበር አለመዳበሩን ማረጋገጥ፡፡

3. በግጥም አማካይነት በፈጠራዊ ዘዴ አማርኛ ቋንቋን ማስተማር የቃላት ፍቺ መለየትን፣ ዐ.ነገር መመስረትን፣ ድርሰት መጻፍን ለማስተማር ያለውን ሚና በሙከራ ማረጋገጥ፡፡
4. በግጥም አማካይነት አማርኛ ቋንቋን በክፍል ውስጥ እንዴት ማስተማር እንደሚገባ በዝርዝር መግለጽ፡፡
5. ተማሪዎች በግጥም አማካይነት በፈጠራዊ ዘዴ አማርኛ ቋንቋን ከተማሩ በኋላ የቀረበውን ትምህርት፣ የተማሩበትን ስልትና ያካሄዱትን ልምምድ መውደድ አለመውደዳቸውን ማረጋገጥ፡፡
6. በግጥም አማካይነት የአማርኛ ቋንቋን በፈጠራዊ ዘዴ ለማስተማር ሲታቀድ ወይም ሲታሰብ የሚያጋጥሙ መሰናክሎች ካሉ ለይቶ በማውጣት የመፍትሄ ሀሳብ መስጠት፡፡

## 1.3 የጥናቱ ጠቀሜታ

ስነ ጽሑፍ ቋንቋን በማስተማር ረገድ ያለውን ሚና በጥናት (ሙከራ) ማረጋገጥ በመማር ማስተማሩ ሂደት የሚኖረው ድርሻ ላቅ ያለ ነው፡፡ በመሆኑም የዚህ ጥናት ውጤት ተከታዮቹ ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታሰባል፡፡

- የአማርኛ ቋንቋ መርሀ - ትምህርትና መማሪያ መጻሕፍት አዘጋጆች ግጥም ለቋንቋ ትምህርት ያለውን ሚና በሚመለከት ያላቸውን ግንዛቤ እንዲያሰፉና ተገቢውንም ትኩረት እንዲሰጡት ይረዳል፡፡ በዚህም በተመረጡ ግጥሞች የአማርኛ ቋንቋን (አንብቦ መረዳትና ጽሕፈትን) ለማስተማር የሚያስችሉ የአቀራረብ ደረጃዎችን ተከትለው እንዲያዘጋጁ ያግዛል፡፡
- መምህራን ግጥምን በመጠቀም አማርኛ ቋንቋን በማስተማር ሂደት የሚኖራቸውን ሚና ለይተው እንዲገነዘቡና ተግባራዊ እንዲያደርጉ ያስችላል፡፡
- መምህራን ግጥምን በመጠቀም በክፍል ውስጥ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የአቀራረብ ደረጃዎችንና የማስተማር ስልቶችን ተከትለው እንዲያስተምሩ እገዛ ያደርጋል፡፡

➢ በስነ ጽሑፍ ቋንቋን ማስተማርን በተመለከተ ወደፊት ጥናት ማድረግ ለሚፈልጉ አጥኝዎች ለመነሻ የሚሆኑ ሀሳቦችን ያጋራል ተብሎ ይታሰባል፡፡

## 1.4 የጥናቱ ወሰን

በስነ ጽሑፍ ቋንቋን ማስተማርን በተመለከተ ሰፊና ጥልቅ ጥናት ማካሄድ ይቻላል፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ጥናት ባለው የጊዜና የገንዘብ ውሱንነት የተነሳ በዋናነት የሚያተኩረው ግጥም የአማርኛ ቋንቋ አንብቦ መረዳትና ጽሕፈት ክሂሎችን ለማስተማር ያለውን ሚና በሙከራ ማረጋገጥ ላይ ነው፡፡ ስለዚህ ጥናቱ ከስነ ጽሑፍ ዘሮች መካከል ግጥምን፣ ከክሂሎች መካከል ደግሞ አንብቦ መረዳትንና ጽሕፈትን ብቻ የሚመለከት ይሆናል፡፡ ከነዚህ ውጭ ያሉት የስነ ጽሑፍ ዘሮችና የቋንቋ ክሂሎች በዚህ ጥናት ውስጥ አልተካተቱም፡፡ እንዲሁም መሰረታዊ የሆኑ ስነ ጽሑፋዊ ጉዳዮችን ለመነሻነት ከመዳሰስ በስተቀር ይህ ጥናት ዝርዝር ወደሆኑ ስነ ጽሑፋዊ ጉዳዮች ውስጥ አልገባም፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በዚህ ጥናት ውስጥ ተተኳሪ የሆኑት (የታቀፉት) በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በምዕራብ ጎጃም ዞን ውስጥ በሚገኘው ደምበጫ ከፍተኛ ትምህርት መሰናዶና አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ውስጥ በ2005 ዓ.ም. የሚማሩ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ብቻ ናቸው፡፡

## 1.5 የመሰረታዊ ጽንሰ ሀሳቦች ና የቁልፍ ቃላት ብያኔ

1. ስነ ጽሑፍ

ሀ. ስነ ጽሑፍ የምንለው ስለ ሰዎች፣ ለሰዎች፣ በሰዎች በተለያዩ ቅርጾች የሚቀርብ የገጠመኝ ማንጸባረቂያና ህይወትና እውነትን አጣምሮ የሚይዝ፣ በጽሑፍም ሆነ በቃል ህያው የሚሆን የፈጠራ ስራ ነው፡፡ በውስጡም ግጥምን፣ አጭርና ረጅም ልቦለድን፣ ተውኔትን...ወዘተ. አካቶ ይይዛል (ዘሪሁን፣ 1992)፡፡

ለ. ስነ ጽሑፍ የሚባለው ስሜትን ነክቶ ከአእምሮ ጋር በማዋሀድ ሰው የሚኖርበትን ዓለም ከዘወትራዊ አተያይ በማራቅ ሰብዓዊነቱን መርምሮ፣ ስጋና መንፈሱን ህብር ሰጥቶ ይኖር ዘንድ የሚጠቀምበት ጥበብ ነው (ዮናስና ሌሎች፣ 1966)፡፡

ጰ

2. ፈጠራዊ ዘዴ

ፈጠራዊ ዘዴ ማለት የፈጠራ ጽሑፎችን በምንጭነት በመጠቀም የቋንቋ አጠቃቀምን ለማስተማር የሚያገለግልና በባህሪው ተማሪ- መራሽ የሆነ የማስተማር ዘዴ ነው (Ibsen, 1995፡ 143)።

3. አማካይ ውጤት

አማካይ ውጤት ማለት በርካታ በቁጥር የሚወከሉ መረጃዎችን በማጠቃለል መረጃው ስለተሰበሰበበት ጉዳይ በአንድ ነጥብ አማካይነት ባህሪውን ለመወከል የሚረዳ ስታቲስቲክ ነው።...አማካይ ውጤትን ለመወሰን የተሰበሰቡትን ጠቅላላ ነጥቦች በመደመር ለብዛታቸው ማካፈል ነው (ያለው፣ 1998፡ 257)።

4. መደበኛ ልይይት

መደበኛ ልይይት የሚያመለክተው የጥናቱ ተሳታፊዎች ውጤት ከአማካይ ውጤታቸው ምን ያክል በአማካይ እንደሚርቅ ነው።...መደበኛ ልይይት የሚያሳየው የተጠኝዎቹን የውጤት መቀራረብና መራራቅ ሲሆን፣ ከፍተኛ መደበኛ ልይይት የተሳታፊዎችን የባህሪ ልዩነት ሲያመለክት፣ አነስተኛ መደበኛ ልይይት ደግሞ የባህሪ መመሳሰልን ያመለክታል (ያለው፣ 1998፡ 264)።

5. የጉልህነት ደረጃ

የጉልህነት ደረጃ ሲባል ከመቶ እጅ በምን ያክል መጠን አልቦ መላምቱን በስህተት ውድቅ ልናደርገው እንደምንችል የሚያመለክት ነው (ያለው፣ 1998፡ 272)።

6. የነጻነት ደረጃ

የነጻነት ደረጃ ሂሳባዊ እሳቤ ሲሆን መሰረት የሚያደርገው የጥናት ተሳታፊዎችን ብዛት ነው። ሆኖም ከጥናት ተሳታፊዎች ብዛት ጋር እኩል አይደለም። ቢያንስ በአንድ ያንሳል። አገልግሎቱም ከጉልህነት ደረጃው ጋር ሆኖ አልቦ መላምቱን ለመቀበል ወይም ለመጣል የሚያስችል ውሳኔ ላይ ለመድረስ ነው። የነጻነት ደረጃ ከተሰጡን ውጤቶች መካከል ለማቀያየር የሚኖረንን ነጻነት የሚያመለክት ነው (ያለው፣ 1998፡ 273)።

ፃ

7. የቲ- ስንጠረዥ ዋጋ

የቲ- ስንጠረዥ ዋጋ የሚባለው የጉልህነት ደረጃውን፣ የፍተሻውን ዓይነትና የነጻነት ደረጃውን መሰረት አድርጎ በሰንጠረዦች ላይ የሚገኝ ዋጋ ነው፡፡ የተለያዩ የቲ- ሰንጠረዥ ዋጋዎች ያሉ ሲሆን አገልግሎታቸውም ከሚገኙት ዋጋዎች ጋር በማወዳደር የተመቱትን መላምቶች በመቀበል ወይም ውድቅ በማድረግ ውሳኔ ላይ ለመድረስ ነው (ያለው፣ 1998፡ 274)፡፡

8. ቲ- ቴስት

ይህ የመላምት መፈተሻ ዘዴ የሚያገለግለው አንድ ቡድን በሁለት ነጻ ተለዋዋጮች ላይ ወይም ሁለት ቡድኖች በአንድ ነጻ ተለዋዋጭ ላይ የባህሪ ልዩነት ያላቸው መሆኑንና አለመሆኑን ለማሳየት ነው፡፡... ቲ- ቴስት በሶስት መንገድ ሊያገለግል ይችላል፤ ከአንድ የጥናት አካባይ ውስጥ አንድ ናሙና በመምረጥ አንድ ጊዜ መረጃ ሲሰበሰብ፣ ከአንድ ወይም ከሁለት የጥናት አካባዮች ውስጥ ሁለት ናሙናዎች በመምረጥ መረጃ አንድ ጊዜ ሲሰበሰብና ከአንድ የጥናት አካባይ ውስጥ አንድ ናሙና በመምረጥ ከናሙናው ሁለት ጊዜ መረጃ ሲሰበሰብ (ያለው፣ 1998፡ 277)፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# 2. ክለሳ ድርሳናት

## 2.1 ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት

### 2.1.1 የግጥም ምንነት

ግጥም እድሜ ጠገብ የስነ ጽሑፍ ዘር ነው። በቃልም ይሁን እንጂ የሰው ልጅ በቋንቋ መጠቀም ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ግጥም ነበር። ከቃል በተጨማሪ የሰው ልጅ በጽሑፍ መገልገል ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ግጥም ሲጻፍ ኖሯል። ስለዚህ ጽሑፍ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶም ቢሆን ግጥም አለ (ዘሪሁን፣ 1992፡ 73)።

ግጥም በየዘመኑ እንደየትውልዱ የህይወት ፍልስፍና፣ ትውልዱ እንደሚከተለው የስነ ጽሑፍ ፈለግ፣ እንደየ ሀያሲው አመለካከትና ዝንባሌ የተለያዩ ብያኔዎች ተሰጠውታል። በተለያዩ ምሁራን ከተሰጡ በርካታ ብያኔዎች መካከል ጥቂቶችን ቀጥለን እንመልከት።

ግጥም በግጥማዊ ውበትና እውነት ላይ የተመሰረተ የህይወት ሂስ ነው፣ በማለት ግጥም የሰው ልጅ በህይወቱ ውስጥ የሚፈጥራቸውን ወይም የሚያጋጥሙትን እንከኖች ለማስተካከል የሚችልበት መንገድ እንደሆነ ማቲው አርኖልድ ያስረዳሉ ሲሉ (ዘሪሁን፣ 1992፡ 73) ይገልጻሉ። አያይዘውም ግጥም ምት ያለው ምናባዊ የሆነ የብርቱ ስሜት መግለጫ ነው ሲሉ ዊሊያም ወርድስወርዝ ለግጥም ብያኔ እንደሰጡ ይገልጻሉ። ከዚህ ብያኔ እንደምንረዳው ገጣሚ ማለት አንዳች የሚንተከተክ ስሜት ያለው ሰው ነው። ይህን የሚንተከተክ ስሜት በቀላሉ ለመግለጽ ደግሞ ግጥም ተቀዳሚ መንገድ ነው።

ብርሃኑ (1999፡ 6) በበኩላቸው የተለያዩ ምሁራን ስለግጥም ምንነት ያሉትን እንዲህ ይገልጹታል። ፍሊፕ ሰድኒ ግጥም ተናጋሪ ስዕል ነው በማለት ይበይኑታል። እንደሰድኒ አገላለጽ ጥሩ ግጥም በሰዎች ልቦና ውስጥ አንዳች ትዕይንት መፍጠር የሚችል ነው። ኤድዋርድ ሆስማን ግጥምን የተነገረው ነገር ሳይሆን የመናገሪያው መንገድ ነው በማለት ይገልጹታል። ግጥምን የተለየ የሚያደርገው የሚባልበት መንገድ እንደሆነ የሚያስረዳ ብያኔ ነው። ጆን ረስኪን በበኩላቸው ግጥም ለታላላቅ ስሜቶች መሰረት ስለሚሆኑ ጉዳዮች

በምናብ አማካይነት የሚቀርብ አስተያየት ነው ይሉታል፡፡ ኪ.ገዘ ቸስተርተን ደግሞ ማነኛውም ዘይቤ ግጥም ነው በማለት ይገልጹታል ፡፡

የግጥምን ምንነት በሚመለከት የሀገራችን ገጣሚያንም የበኩላቸውን ብያኔ ሰጠዋል፡፡ የተወሰኑትን ቀጥለን እንመልከት፡፡

ጸጋዬ (1966፡ 7) ግጥምን ‹‹በቃሉ ውበት፣ በቃለ ሀይሉ ወይም በድቀቱ ስምረት ለአእምሮ ለልቦናና ለስሜት የሚጥም ባለስልትና ባለድንጋጌ የቋንቋ አደራደር ሁሉ ስነ ግጥም ይባላል›› በማለት ይበይኑታል፡፡ እንደጸጋዬ ብያኔ ግጥም በሶስት ነገሮች ለሶስት ነገሮች ይጥማል፤ በቃለ ውበቱ (ግጥም ለዛ ያለው፣ ውበት ያለው ጥበብ ነው፡፡ በቋንቋ ውበት ለዛና ውበት እንዲኖረው ይሆናል፡፡)፣ በቃለ ኃይሉ (ግጥም ስሜታችንን የመቆጣጠርና አእምሯችንን የመግዛት ሀይል ያለው ነው፡፡ ይህ ሀይል የሚመነጨው ከሀሳቡ ድድርና፤ ይህ የሚመጣው ደግሞ በሚመርጣቸው ቃላት ድድርና ነው፡፡ በግጥም የቀረበው ሀሳብ ከአእምሯችን የማይጠፋው በሀይሉ ነው፡፡) እና በድቀቱ ስምረት (የሁለቱ ስምረት ቃለ ሀይልና ውበት በሚፈጥሩት ውህደት ምክንያት ለሶስት ነገሮች የሚጥም የቋንቋ አደራደር ነው፡፡) ለአእምሮ፣ ለልቦናና ለስሜት ይጥማል፡፡ ከዚህ ባለፈ ግጥም በስንኞች የሚመጠን መሆኑንና ስልት ያለው መሆኑን ለመግለጽ ባለስልትና ባለድንጋጌ የቋንቋ አደራደር ነው ይሉናል፡፡

ሰለሞን (1963፡ 8-9) በበኩላቸው ‹‹የግጥም ፈንታ የሰውን ልጅ ግላዊ መፍጨርጨር…ከዚህ አለም ችላ ባይነት ጋር አያይዞ ማብላላት ይመስለኛል፡፡ ማብላላት፣ ማፋጨት፡፡ እያፋጩ ተቃራኒዎችን ማጣመድ፣ ተመሳሳዮችን ማለያየት፡፡ ከግጭታቸው ለአንዳፍታ እንደበራሪ ኮኮብ የሚታይ ግልጥ መፍትሄ ማዋለድ፡፡›› በማለት ግጥምን ይበይኑታል፡፡ የግጥም ይዘቱ የሰውን ልጅ ህይወት የሚይዝ መሆን አለበት፡፡ ስለዚህ ግጥም የሰውን ልጅ ግላዊ መፍጨርጨር ከህይወት ችላ ባይነት ጋር አዋህዶ የሚይዝና የሚያብላላ የሚያፋጭ ሲሆን በዚህ ጊዜ ደግሞ ተመሳሳዮች ይለያያሉ፣ተቃራኒዎች ይዛመዳሉ የሚል ብያኔ ነው፡፡

ስለግጥም ብያኔ ከሰጡት መካከል አንዱ (አያልነህ፣ 1989:1) ነው። እንደ አያልነህ

> ‹‹ግጥም ጥልቀት ያለው ሀሳብ እጥር ምጥን ባሉ የተዋቡ ቃላት የሚገለጽበት የስነ ጽሑፍ ዘርፍ ነው። ከልቦለድ የሚለየውም ማራኪና ምርጥ በሆኑ ቃላት ምታዊ ድርደራ የሰውን ልጅ ውስጣዊ ስሜት ጠልቆ በመግባት ህልሙንና ሰብዕናውን ለመግለጽ በመቻሉ ነው።ግጥም የእውነት ነጸብራቅ፣ የሕይወት ኃያሲና ተምሳሌትም ነው። የጠራ መንፈስ የሚገለጽበት እስትንፋስም ነው። አልፎ አልፎም ግብታዊ በሆነ ስሜት የሚፈልቁ የሀሳብ ምንጮች የሚፈሱበት የጥበብ ቃሊም ነው።››

በዚህ ብያኔ መሰረት ግጥም በጥቂት ቃላት ብዙና ብርቱ መልዕክት የሚተላለፍበት ጥበብ ነው። ህይወት፣ እውነትና ውበትን አጣምሮ የያዘ በመሆኑም ለሰው ልጅ ስሜት እጅጉን ቅርብ ነው።

በአጠቃላይ እስካሁን ያየናቸው ብያኔዎች የጋራ የሆነ ድምዳሜ ያላቸው ቢሆንም ግጥምን ከተለያየ አቅጣጫ ለመበየን ወይም ለመፈረጅ የሞከሩ ናቸው። አንዳንዶቹ ከቋንቋ አጠቃቀም፣ ሌሎቹ ከምጣኔና ከምቱ፣ ሌሎቹ በአንባቢው ውስጥ ከሚፈጥራቸው ስሜቶች፣ ሌሎቹ ደግሞ በገጣሚው አእምሮ ውስጥ ከሚኖሩ ስሜት አንቂ ስነ ልቦናዎች አንጻር ብያኔ ለመስጠት ሞክረዋል። እያንዳንዳቸው በየራሳቸው መንገድ ስለግጥም ያላቸውን አመለካከት ሲሰነዝሩ ማሳመኛ የሚሏቸውን ሀሳቦች በማስረጃነት ያቀርባሉ። እያንዳንዳቸውም ስለግጥም የሰጡት አስተያየት የራሱ እውነትነት አለው። ይሁንና ለግጥም አንድ ወጥ የሆነና ይህ ቀረህ የማይባል ሁሉንም የሚያስማማ ብያኔ ማግኘት አይቻልም።

### 2.1.2 የግጥም ባህሪያት

ግጥም ከሌሎች የስነ ጽሑፍ ዘሮች ጋር የሚመሳሰል እንዲሁም የሚለይ የጥበብ ውጤት መሆኑን የሚያሳዩ ጉልህ ባህሪያት አሉት። ከነዚህ መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው።

ሀ. ግጥም ተጨባጭ ነው፡- ይህ ሲባል ግጥማዊ ስራ የፈጠራ ስራ ያልሆነ የገሀዱ አለም ቀጥተኛ ዘገባ ነው ማለት አይደለም። ማለትም ገጣሚው ያለውን ስሜትና ሀሳብ በቋንቋ መሳሪያነት የሚያቀርበው ተጨባጭ ነገሮችን በመጠቀምና ያን ምናባዊ የሆነ ጉዳይ ተጨባጭ በማድረግ ነው ማለታችን ነው። ከያኒው በዚህ ዓለም የህይወት ውጣ ውረድ ውስጥ ሲመላለስ የተበተበውንም ሆነ ፈር ሰጥቶ ያሳለፈውን የኑሮ ዘሀ፣ የታዘበውንም

12

ሆነ ያደነቀውን የሰብዓዊ ባህሪ ገጽታ መነሻ አድርጎ አንዳች ስንክናዊ ቅርጽ በቋንቋ አማካይነት ሲያቀርብ እኛ ያላየነው ያልሰማነው ያ የሱ ጉዳይ ይታየንና ይሰማን ዘንድ ተጨባጭ የሆኑ፣ በገሀድ ሁላችን የምናውቃቸው ነገሮችንና ግንኙነታቸውን እየገለጸ ነው የሚያቀርብልን፡፡

ግጥም የሚያቀርበውን ስሜትና ሀሳብ ለመተንተንና ለማብራራት አይሞክርም፡፡ ይልቁንም ጉዳይ ያደረገውን ስሜት ወይም ሀሳብ ለማሳየት አንድ አውድ ይፈጥራል፡፡ በዚያ የህይወት አውድ ውስጥ በገሀዱ ዓለም በህዋሳተ ስጋችን የምናውቃቸው በሱ ፍጥር ስራ ውስጥ ደግሞ በህዋሳተ ልቦናችን የሚደርሱንን ተጨባጭ ነገሮች ያቀናጃል፡፡ በዚህ ጊዜ ታዲያ በሱ የሀሳብ ዓለም ውስጥ ያለ ረቂቅ ጉዳይ ተጨባጭ ሆኖ ይታየንና እኛም በተፈጠረው የህይወት አውድ ውስጥ ተሳታፊ እንሆናለን፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ምላሽም ይኖረናል፡፡ ወይ እንጠላዋለን፣ እንወደዋለን…ወዘተ.፡፡ ተጨባጭ ነገሮችን መሳሪያ አድርጎ የተጨበጠ ስዕል ስለሚፈጥር ምላሽ ለመስጠት እንገደዳለን፡፡ ስለዚህ ተጨባጭነቱን በዚህ መልኩም ማየት እንችላለን፡፡

ግጥም ተጨባጭ ነው ስንል ማነኛውም ግጥም መነሻው ገሀዳዊው ዓለም መሆኑን ማመልከታችን ነው፡፡ ማነኛውም አይነት ከያኒ በምናብ ሀይሉ እገዛ እፊታችን ይዞት የሚቀርበው ምንም አይነት የፈጠራ ስራ ምንም መልክ ይኑረው ምንም ጉዳይ ይዞ ይቅረብ የሚነሳው ከነበረ፣ ካለና ከሚኖር ነገር ላይ ነው፡፡ ግጥም ተጨባጭ ነው ሲባል ከእውነታው ጋር ተመሳክሮ ሊረጋገጥ የሚችል ጉዳይ ይዞ ይቀርባል ማለታችን ግን አይደለም (ብርሀኑ፣1999፡ 11)፡፡

ለ. ግጥም ምናባዊ ነው፡- ይህ ባህሪ የግጥምን የፈጠራ ስራነት የሚያመለክት ነው፡፡ የግጥምን ምናባዊነት በሁለት መልኩ ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ ከገጣሚው አኳያ ከላይ በጠቀስናቸው ምክንያቶች ግጥም ተጨባጭ ነው ቢባልም ገጣሚው ረቂቅ የሆነውን ጉዳይ ስሜትና ሀሳቡን በግጥም የሚያቀርበው ከምንም በላይ ህዋሳተ ልቦናውን እያሰራ እንጂ ህዋሳተ ስጋው የሚቀርባቸውን ነገሮች እፊቱ እየሰደረ አይደለም፡፡ ከተደራሲው አኳያ ተደራሲው በግጥሙ የቀረበለትን ጉዳይ የሚገነዘበው በህዋሳተ ልቦናው መሆኑን ይጠቁማል፡፡ የግጥሙን ስሜት ወይም ሀሳብ የሚያገኘው ህዋሳተ ልቦናው ንቁ ከሆነ ነው፡፡

ከላይ የጠቀስነው ምናባዊነት የሚመጣው በቋንቋ የረቂቅነት ባህሪ ነው፡፡ ግጥም ተደራሲው የረሳውን በአካል የራቀውን ነገር እንዲያስታውስና እንዲቀርበው የማድረግ ሀይል አለው፡፡ በሌላ አነጋገር በህዋሳተ ስጋው ሊያገኛቸው የማይችላቸውን ነገሮች በህዋሳተ ልቦናው አግኝቷቸው አንዳች ስሜት ውስጥ እንዲገባ ያደርገዋል (ብርሀኑ፣ 1999፡ 14)፡፡

ሐ. ግጥም ቁጥብና እምቅ ነው፡- ቁጥብ ነው ሲባል ቃላት ይመርጣል ማለታችን ነው፡፡ በግጥም የሚመረጡት ቃላት ምርጥ ናቸው፡፡ ይህ ሲባል አንድን ጉዳይ ለማለት ወይም ለማቅረብ ከሌሎች የበለጠ የሚመረጥ ቃል ይመርጣል ማለታችን ነው፡፡ እንጂ የማይረቡ ቃላት አሉ ማለት አይደለም፡፡ ግጥም ቃላትን የሚመርጠው ሀሳብም ስለሚመርጥ ነው፡፡ ምክንያቱም ቃላት የሀሳብና የስሜት መግለጫ ስለሆኑ፡፡ ግጥም ሀሳብ በዝርዝር አያቀርብም፡፡ ፍንጭ ሰጪና አንኳር የሆኑትን የአንድ ሀሳብ ክፍሎች መርጦ ነው በጥቆማ መልክ የሚያቀርበው፡፡ እነዚህን አንኳር ጉዳዮች አድምቆ ለማቅረብ ደግሞ ብርቱ፣ ውብና ስኬታማ ቃላትን ይመርጣል፡፡ ይህ የሚሆነው ከሚያነሱት ሀሳብ አውድ ጋር ነው፡፡ ቃላትና ሀሳብን መርጦ የመበጀትና የመጠቀም ሚስጢር ነው - የግጥም ቁጥብነት፡፡

እምቅ ነው ስንል እነዚያው የሚመረጡት ቃላትና አንኳር ጉዳዮች ብዙ ሊሉና ብዙ ሊጠቁሙ የሚችሉ መሆናቸውን ማመላከታችን ነው፡፡ በሌላ አነጋገር አንድ ግጥም የያዘውን ሀሳብ እየበተኑና እየዘረዘሩ ብዙ ማድረግ ይቻላል፡፡ ሰፊ ሀሳብ አምቆ የመያዝ ሀይል አለው፡፡ አንድ ግጥም ያለው ውበት የሚሰርጸው ሲተነተን ነው፡፡ ግጥሙ የያዘውን የታመቀ ሀሳብ እየፈቱና እየመነዘሩ የመተንተኑ፤ ከትንታኔውም አንዳች የህይወት ፍቺ የማዋለድ ድርሻ የተደራሲው ነው፡፡ ተደራሲው ይህን ለማድረግ ተሰጥኦ፣ ትምህርት (የሙያ ስልጠና)፣ ብዙ ልምምድ ያስፈልገዋል (ብርሀኑ፣ 1999፡ 18)፡፡

መ. ግጥም ሙዚቃዊ (ዜማዊ) ነው፡- ግጥም በተፈጥሮው ዜማዊ ነው፡፡ ለመደመጥ የሚበጅ ስንክናዊ ስራ በመሆኑ ዜማዊነት አይቀርም፡፡ ዜማዊነቱ የሚፈጠረውም ከምቱ በሚሰርጸው ስልትና ስርዓታዊነት ነው፡፡ የምቱ ስልትና ስርዓታዊነት እንዲሁም የአንዳንድ ቃላት የተለየ ባህሪ፣ ከሌሎች ቃላት ጋር የሚያደርጉት ግጥሚያ፣ አቀባዊም ሆነ አግድማዊ ድርድራቸው የሚያመጣው ቃና ግጥሙን ሙዚቃዊ (ዜማዊ) ሊያደርገው ይችላል፡፡ መሰረታዊ የዜማ መፈጠሪያውም ምት ነው፡፡ ይህም የተደራሲውን ስሜት

14

ይቀሰቅሳል። አንዳች ሰብዓዊ ስሜት ያጭራል። መደሰት፣ መከፋት፣ ስጋት፣ ራሮት፣ ኃዘኔታ፣ ጭንቀት፣ ቅናት…ወዘተ. (ብርሀኑ፣ 1999፡ 19)።

## 2.1.3 ግጥም አማርኛ ቋንቋን ለማስተማር ያለው ሚና

ስነ ጽሑፍ ቋንቋን በማስተማር ሂደት የጎላ ሚና እንዳለው በምዕራፍ አንድ የጥናቱ ዳራ ላይ ተጠቁሟል። እዚያ ላይ ከቀረበው ሀሳብ በተጨማሪ ግጥም ያለውን ሚና እዚህ ላይ ማንሳት ያስፈለገው የጥናቱ ዋነኛ የትኩረት አቅጣጫ በግጥም ቋንቋን ማስተማር ያለውን ሚና በሙከራ ማረጋገጥ ስለሆነ ነው። ግጥም ለቋንቋ ትምህርት የሚያበረክተውን አስተዋጽኦ ቀጥለን እንመልከት።

- በትምህርቱ ሂደት ተማሪዎችን የማነቃቃት ሀይል አለው።
- ተማሪዎች እየተደሰቱ ሳይሰለቹ ትምህርቱን እንዲከታተሉ ከፍተኛ እገዛ ያደርጋል፡ ፡
- የተለያዩ ልምዶችንና አጋጣሚዎችን በማካፈል የንግግርም ሆነ የጽሑፍ ቋንቋን ለመማርና ለማስተማር ያስችላል (Hill, 1986: 72 እና Lazar, 1993: 71-72)

ከላይ ከቀረቡት የምሁራን ሀሳቦች መገንዘብ እንደሚቻለው ግጥም የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት በማነሳሳት ትምህርቱን በደስታና በፍላጎት እንዲማሩት ማድረግ ያስችላል። እንደዚሁም የክፍል ውስጥ ተሳትፏቸውን በከፍተኛ ደረጃ በመጨመር ውጤታማነታቸውን ለማሳደግም እገዛው ላቅ ያለ ነው።

## 2.1.4 ተማሪዎች ግጥምን በሚያነቡበት ጊዜ ሊያጋጥሟቸው የሚችሉ መሰናክሎች

ቋንቋን በማስተማር ሂደት ስነ ጽሑፍን በመሳሪያነት መጠቀም ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው ቢታወቅም በትክክል ካለመጠቀም የተነሳ ደግሞ ሊፈጠሩ የሚችሉ ችግሮች ይኖራሉ። እዚህ ላይ ለማንሳት የተፈለገው ተማሪዎች ግጥምን በሚያነቡበት ጊዜ ሊያጋጥሟቸው የሚችሉ መሰናክሎችን ነው። ምክንያቱም ጥናቱ የሚያተኩረው ግጥምን በምንጭነት ተጠቅሞ አማርኛ ቋንቋን ማስተማር ያለውን ሚና መለየት ስለሆነ ነው።

*ሀ. የቃላት ክብደት፡-* ብዙ ጊዜ ግጥም ጠጠር ያሉ ቃላትን ይጠቀማል፡፡ ይህ መሆኑ ተማሪዎች የግጥሙን መልዕክት በቀላሉ ለመረዳት በሚያደርጉት ጥረት ላይ እንቅፋት ይሆናል፡፡ ስለሆነም በግጥሙ ውስጥ ያሉትን ቃላት በሙሉ ተማሪዎች ማወቅ ባይችሉም እንኳ የጽሑፉን አጠቃላይ መልዕክት እንዲረዱ የሚያስችሉ ቁልፍ ቃላትን እንዲያውቁ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ለዚህም መዝገበ ቃላትን መጠቀም አንደኛው አማራጭ ሊሆን ይችላል፡፡ መዝገበ ቃላት በሌለበት ሁኔታ ደግሞ ሰዎችን መጠየቅ እንደ አማራጭ ሊወሰድ ይችላል፡፡

*ለ. ያለመነቃቃት ችግር፡-* ይህ ችግር የሚከሰተው የሚቀርበው ግጥም ከተማሪዎች አጠቃላይ ሁኔታ ጋር የማይጣጣም ሲሆን ነው፡፡ ምናልባት ጽሑፉ የማይስብ፣ ለተማሪዎች ደረጃ የማይመጥን፣ ባህላዊ፣ ስነ ልሳናዊ፣ ስነ ጽሑፋዊ ዳራቸውን ያላገናዘበ ወዘተ. ከሆነ ተማሪዎች ለማንበብ፣ መልዕክቱን ለመረዳት የሚኖራቸው ተነሳሽነት ይቀንሳል፡፡

*ሐ. በግንዛቤ ማነስ የሚከሰት ችግር፡-* ይህ በልዩ ልዩ ሰበቦች ሊፈጠር ይችላል፡፡ የቃላትን ፍቺ ባለመገንዘብ፣ የግጥሙን መልዕክት ባለመረዳት፣ የገጣሚውን አላማ ባለማወቅ ወዘተ. ሊከሰት ይችላል፡፡

*መ. አስፈላጊ የንባብ ስልትን ባለመከተል የሚመጣ ችግር፡-* ተማሪዎች ግጥምን በሚያነቡበት ጊዜ የሚያጋጥሟቸውን የተለያዩ ቃላት በአውዳዊ ፍቻቸው ከመረዳት ይልቅ በተናጠል ቃላቱ ያላቸውን ትርጉም ለመረዳት ሲጥሩ ችግር ይከሰታል፣ ግጥሙ ሊያስተላልፍ የፈለገውን መልዕክት ሳያገኙት ይቀራሉ፡፡ ይህም በትምህርቱ ሂደት ላይ ጋሬጣ ይሆናል፡፡

*ሠ. የገጣሚውን የአጻጻፍ ስልት ባለመገንዘብ የሚመጣ ችግር፡-* ገጣሚያን አንዱ ከአንዱ ተለይተው ከሚታወቁባቸው ጉዳዮች መካከል አንዱ የአጻጻፍ ስልታቸው ነው፡፡ ሁሉም ገጣሚ የየራሱን የአጻጻፍ ስልት ተከትሎ ይሄዳል፡፡ እነዚህ የተለያዩ የአጻጻፍ ስልቶች ደግሞ ግጥሙን አንብቦ ለመረዳት አስቸጋሪ ሊያደርጉት ይችላሉ፡፡ ምክንያቱም ገጣሚያን የሚከተሉት የአጻጻፍ ስልት ምናልባት ዘወትራዊ ከሆነው የቋንቋ አጠቃቀም የወጣ፣ ያፈነገጠ፣ ፈጠራዊ ቃላትን በብዛት የሚጠቀም ሊሆን ይችላል፡፡

ረ. የግጥሙን ባህላዊ ወይም ታሪካዊ ዳራ ካለመረዳት የሚፈጠር ችግር፦ አንድ ግጥም ሲገጠም ይዞት የሚነሳው ባህላዊ ጉዳይ፤ የተመሰረተበት ታሪክዊ አጋጣሚ ሊኖር ይችላል። እነዚህን ጉዳዮች ቀደም ብሎ ማወቅ ምናልባት ግጥሙን ለመረዳት ወሳኝ ሊሆን ይችላል። ይህ ባልሆነበት አጋጣሚ ግጥሙን አንብቦ ለመረዳት መሞከር አስቸጋሪ ነው። ስለዚህ እነዚህን ነጥቦች አለማወቅ እንደ አንድ እንቅፋት ሊቆጠር ይችላል።

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት አንኳር ችግሮች ግጥምን በማንበብ ሂደት ሊከሰቱ የሚችሉ ቢሆኑም ችግሮቹን ለማስወገድ የሚያስችሉ በርካታ መፍትሄዎችም አሉ። ከላይ የቀረቡትን ችግሮች ለማቃለል ብሎም ለማስወገድ ከሚያስችሉ ዘዴዎች መካከልም በ2.1.5 ስር የቀረቡት የመምረጫ መስፈርቶች እንዲሁም በ2.1.8 ስር የተዘረዘሩት የመምህሩ ሚና በዋናነት ሊጠቀሱ የሚችሉ ናቸው።

## 2.1.5. የግጥማዊ ስራዎች አመራረጥ

ለቋንቋ ማስተማሪያነት የሚያገለግሉ ስነ ጽሑፋዊ ስራዎችን ስንመርጥ ግምት ውስጥ መግባት ያለባቸው መሰረታዊ መስፈርቶች መረሳት የለባቸውም። ይሁንና መረጣው እጅግ ከባድና ከፍተኛ ጥንቃቄን የሚሻ ተግባር ነው።

ቋንቋን ለማስተማር የሚያገለግሉ ምንባቦችን መምረጥ የመጨረሻው ዋነኛ ተግባር ባይሆንም ትኩረት ከሚያሻቸው ጉዳዮች ውስጥ ግን አንዱ ነው። ይህን በተመለከተ ፈቃደ (1991፡ 109) የሚከተለውን ብለዋል።

> *ለቋንቋ ትምህርት የሚጠቅሙ ምንባቦች መመረጥ የሚገባቸው ተፈላጊውን ክሂል ለማስተማር ያላቸው ተገቢነት ተጠንቶ መሆን አለበት። ቅድሚያ መሰጠት ያለበት ምንባቦቹ ለቋንቋ ትምህርት የሚያደርጉት አስተዋጽኦ እንጂ ለምንባቦቹ ይዘት መሆን የለበትም።*

ከስነ ጽሑፋዊ ስራዎች መካከል አንዱ ግጥም ነው። ስለዚህ ስነ ጽሑፋዊ ስራዎችን ለቋንቋ ማስተማሪያነት ለመምረጥ የሚያስችሉት መስፈርቶች በሙሉ ግጥምንም ለመምረጥ ያገለግላሉ፡ግጥሞችን ለቋንቋ ማስተማሪያነት ስንመርጥ ከግምት ውስጥ መግባት ያለባቸውን መስፈርቶች ከዚህ እንደሚከተለው እንመልከት።

17

*1. የቋንቋ ትምህርቱን አላማ ለማሳካት የሚያስችሉ መሆን አለባቸው፡-*

ግጥሞች ሲመረጡ ቀድሞ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው የተነደፈውን የቋንቋ ትምህርት አላማ ከግብ ለማድረስ ላላቸው አመቺነት ነው፡፡ በቋንቋው ተጽፈው በሚገኙ የፈጠራ ስራዎች ጥናት ውስጥ የሚሰጣቸው ስነ ጽሑፋዊ የብቃት ደረጃ ብቻውን ቋንቋን ለማስተማር አላማ በሚያደርገው ምርጫ በቂ መመዘኛ ላይሆን ይችላል፡፡ ይህ ጉዳይ በቋንቋ ትምህርቱ ሂደት ልናከናውን ካቀድናቸው ዝርዝር አላማዎች ጋር የተያያዘ አንድምታ ያለው ነው (Hill, 1986: 15)፡፡

ይህንን ጉዳይ በመተለከተ Brumfit and Carter (1986፡ 190) እንደሚያስረዱት የሚመረጡት ግጥማዊ ስራዎች የቱንም ያህል ውብና ማራኪ ሆነው የተማሪዎችን ስሜት የሳቡ ቢሆኑም የቋንቋ ትምህርቱን አላማ ከግብ የማያደርሱ ከሆኑ ዋጋ ቢስ ናቸው፡፡

በድሉ (1996፡ 16) በበኩላቸው የሚከተለውን ብለዋል፡፡

> *ለቋንቋ ማስተማሪያነት የሚቀርብ ስነ ጽሑፋዊ ስራ ይዘትን ያገናዘበ መሆን አለበት፡፡ እዚህ ላይ ይዘት ብለን የምናተኩርበት የተመረጠውን የስነ ጽሑፍ ስራ ጭብጥ አይደለም፡፡ በዚህ አውድ ይዘት ስንል ስራው የቀረበበትን ቋንቋ ማለታችን ነው፡፡ ለተወሰነ ደረጃ የሚቀርብ የስነ ጽሑፍ ስራን ከቀረበበት ቋንቋ ይዘት አንፃር በምንመርጥበት ጊዜ ማነፃፀሪያ የሚሆነን ለደረጃው ማስተማሪያ መሳሪያ ይዘትና የተነደፈው የትምህርት አላማ ነው፡፡ ስለዚህ ወደ ምርጫ ከመግባታችን አስቀድመን በትምህርቱ መጨረሻ ተማሪዎች እንዲያዳብሩ የተፈለገው ችሎታ ምንድን ነው? የሚለውን አጠቃላይ ጥያቄ መጠየቅ ያሻል፡፡*

በአጠቃላይ ከላይ ከቀረቡት የምሁራን ሃሳቦች መረዳት እንደሚቻለው አንድ ግጥም ለቋንቋ ማስተማሪያነት ሲመረጥ ሊመዘን የሚገባው ስራው ባለው ውበትና ማራኪነት እንዲሁም የተማሪዎችን ስሜት ቆንጥጦ በመያዙ አይደለም፡፡ የሚመረጠው ስራ ከቋንቋ ትምህርቱ አላማ ጋር ባለው ተጣጥሞ፣ አላማውን ተግባራዊ በማድረግ ሂደት ባለው እገዛ፣ የተማሪዎቹን የክሂልና የእውቀት ዘርፎች በማዳበር ረገድ በሚያበረክተው አስተዋጽኦ ወዘተ. እንጂ፡፡ ምክንያቱም ግጥማዊ ስራዎችን በቋንቋ ትምህርት ውስጥ በምንጭነት የምንጠቀመው ተማሪዎቻችንን ለማዝናናት ብቻ ብለን አይደለም፡፡ የቋንቋ ትምህርት አላማም የክሂልና የእውቀት ዘርፎችን በማዳበር ተማሪዎቹ በቋንቋው እንዲጠቀሙ ማድረግ ነው፡፡ በመሆኑም የምንመርጣቸው ግጥሞች ግባቸው ከማዝናናት በዘለለ ያቀድነውን አላማ የሚያሳኩልን ሊሆኑ ይገባል፡፡

18

*2. ከመርሀ ትምህርቱ አጠቃላይ መንፈስ ጋር የሚሄዱና ለደረጃው የተመረጡትን ይዘቶች ያገናዘቡ ስራዎች መሆን ይገባቸዋል፡-*

የምንመርጣቸው ግጥሞች የቋንቋ ትምህርቱን አላማ የሚያሳኩ ሆነውም ከመርሃ ትምህርቱ ጋር ላይጣጣሙ ይችላሉ። ይህንን በተመለከተ Lazar (1993: 55) የምንመርጣቸው ግጥማዊ ስራዎች ከመርሃ ትምህርቱ ጋር መጣጣም አለመጣጣማቸውን ለማረጋገጥ የሚከተሉትን ሁለት መሠረታዊ ጥያቄዎች መጠየቅና ለጥያቄዎቹም መልስ መስጠት እንደሚያስፈልግ ያስረዳሉ።

1. የምንመርጣቸው ግጥሞች ከመርሃ ትምህርቱ ጋር በምን መልኩ ይገናኛሉ? በጭብጥ?፣ በቃላት ትምህርት?፣ በሰዋስዋዊ ትምህርት?፣ በፈሊጣዊ አነጋገር?፣ በምሳሌያዊ አነጋገር? ወዘተ.፣

2. በመርሃ ትምህርቱ ላይ የተጠቀመውን የማስተማር ስነ ዘዴ ተከትሎ ልዩ ልዩ መልመጃዎችን ማውጣት ይቻላል?

ከዚህ እንደምንረዳው የሚመረጡት ግጥሞች ከተማሪዎች ፍላጎትና ችሎታ፣ ከስራዎቹ ስነ ልሳናዊ ክብደትና ቅለት እንዲሁም ተማሪዎቹ አንብበው ለመረዳት ካላቸው ዳራዊ እውቀት አንፃር ተገቢ ከመሆናቸውም ባለፈ ከመርሃ ትምህርቱ ጋር ሊጣጣሙ ይገባል።

ከዚህ ባሻገር ቋንቋን ለማስተማር የሚመረጡት ግጥሞች የተለያዩ ይዘቶችን (ቃላትን፣ ሀረጋትን፣ ዐ.ነገሮችን፣ ተረትና ምሳሌዎችን፣ ምሳሌያዊ አነጋገሮች ወዘተ.) መያዛቸውና በተፈለገው መጠንና ደረጃ መገኘታቸው ከግምት ውስጥ መግባት አለበት (በድሉ፣ 1996፡ 16 እና Hill, 1986: 17)።

*3. የሚመረጡት ግጥማዊ ስራዎች የሚይዙት ርዕሰ ጉዳይ ቋንቋውን ለሚማሩት ተማሪዎች ተገቢነት ሊኖራቸው ይገባል፡-*

ቋንቋን ለማስተማር የሚመረጡ ስራዎች የተማሪዎችን ስነ ልሳናዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ታሪካዊ ዳራዎች በሚገባ ያጤኑና ሊመጡ የሚችሉ ልዩነቶችን ሊያስተናግዱ የሚችሉ መሆን አለባቸው። ለህፃናት፣ ለወጣቶች ወይም ለጎልማሶች የምናቀርባቸው ግጥማዊ ስራዎች አንድ አይነት ሊሆኑ አይችሉም። ለምሳሌ፡- እንደተረት

አይነቶቹ የስነ ጽሑፍ ስራዎች ለህፃናት ቢቀርቡ ተገቢነት አላቸው። በአንጻሩ ለወጣቶችና ለጎልማሶች ቢቀርቡ ግን ተገቢነት ላይኖራቸው ይችላል። ስለዚህ የምናቀርባቸው ግጥሞች የተማሪዎችን ደረጃ የሚመጥኑና ተገቢ መሆን አለባቸው፤ ከመጠን በላይ ያልከበዱ ከመጠን በታችም ያልቀለሉ ሊሆኑ ይገባል (Hill, 1986: 18)።

በሌላ በኩል የሚመረጡት ስራዎች ተገቢነት ሊኖራቸው ይገባል ስንል የተማሪዎችን የክፍል ደረጃ የሚመጥኑ መሆን አለባቸው ማለታችን ነው። የሚመረጡት ግጥማዊ ስራዎች የተማሪዎችን ዕድሜ፣ የአእምሮ ብስለት፣ በአጠቃላይም በክፍል ደረጃው የሚጠበቀውን ታሳቢ የቋንቋ ችሎታ የሚመጥኑ መሆን ይኖርባቸዋል። እንዲሁም በተማሪዎች ዕውቀት ሊደነቁ የሚችሉ መሆን አለባቸው። ከዚህ ባለፈ የተማሪዎችን ባህላዊ ዳራ ለማሳየት የሚችሉ ቢሆኑ ይመረጣል። ተማሪዎቹ ከተለያዩ አካባቢዎች የመጡና በአንድ ትምህርት ቤት የሚማሩ ሊሆኑ ይችላሉና (Lazar, 1993: 52)።

እንዲሁም የሚመረጡት ስራዎች ከተማሪዎች ስነ ጽሑፋዊ ብቃት አንጻር ተገቢነት ሊኖራቸው ይገባል። በአንድ ክፍል ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች የሚኖራቸው የስነ ጽሑፍ ዳራዊ እውቀት የተለያየ እንደሚሆን መገመት አይከብድም። የተወሰኑ ተማሪዎች ከተለያዩ ስነ ጽሑፋዊ ሥራዎች ጋር ቀደምት ትውውቅ ሊኖራቸው ቀሪዎቹ ደግሞ ላይኖራቸው ይችላል። ስለሆነም ስንመርጥ እነዚህን ጉዳዮች ከግንዛቤ ልናስገባ ይገባል።

ከዚህ በተጨማሪ የሚመረጡት ስራዎች ከተማሪዎች ስነ ልሳናዊ ብቃት አኳያ ተገቢነት ሊኖራቸው ይገባል። ተማሪዎች ካሉበት የትምህርት ደረጃ አኳያ የስነ ልሳን እውቀታቸው ዝቅተኛ ሊሆን ይችላል። ስለዚህ ይህን አይነቱን ችግር ለማስወገድ ተማሪዎች ባሉበት የትምህርት ደረጃ ሊገነዘቧቸው የሚችሉና አቅማቸውን ወይም የስነ ልሳን ችሎታቸውን ግምት ውስጥ ያስገቡ የቃላት፣ የሰዋስው፣ የዐነገር አጠቃቀምና የአገባብ ስርዐት ጠብቀው የተጻፉ ስራዎችን መምረጥ አስፈላጊ ነው (ዘመንፈስ፣ 1991፡ 32)

4. *ሳቢ መሆን አለባቸው፡-*

ለማስተማሪያነት የሚመረጡት ስራዎች የተማሪዎችን ፍላጎትና ስሜት ወጥረው መያዝ የሚችሉ ሳቢ ስራዎች መሆን አለባቸው። ይህ ሲሆን በመማር ማስተማሩ ሂደት ውስጥ የተማሪዎች ግላዊ ተሳትፎ በእጅጉ ያድጋል፣ ይጎለብታል። የተማሪዎች ተሳትፎ

መጨመር ደግሞ የቋንቋ ትምህርቱ አላማ በጥሩ ሁኔታ እንዲሳካ የማይተካ ሚና ይጫወታል (በድሉ፣ 1996፡ 16)፡፡

በአጠቃላይ ለቋንቋ ትምህርት የሚያገለግሉ ግጥማዊ ስራዎችን ስንመርጥ ዋናው ትኩረታችን ተፈላጊውን ክሂል ለማስተማር ካላቸው ተገቢነት አንጻር ሊሆን ይገባል፡፡ ከዚህ ባሻገር በምንመርጣቸው ስራዎች ውስጥ ያሉትን ይዘቶች ተረድተው ያንን በተግባር ለመተርጎም እንዲችሉ ለማድርግ ሳይሆን በስርዓተ ትምህርቱ የተቀመጡትን አላማዎች ተግባራዊ ለማድረግ ነው፡፡ ማለትም አላማችን አራቱን ክሂሎች ተማሪዎች መማር እንዲችሉ ከሆነ የምንመርጣቸው ግጥሞች እነዚህን ተግባራዊ ሊያደርጉ የሚችሉ መሆን አለባቸው፡፡

### 2.1.6 ቋንቋን መሰረት ያደረጉ ስነ ዘዴያዊ አቀራረቦች

ቋንቋን መሰረት ያደረጉ ስነ ዘዴያዊ አቀራረቦች ተከታዮቹ እንደሆኑ (Lazar, 1993፡ 23-27) ያስረዳሉ፡፡ እነዚህም፡-

- አራቱን ክሂሎች በማዳበር ላይ ያተኮረ ስነ ዘዴያዊ አቀራረብ
- ስነ ጽሑፍን እንደጥናት መስክ በማጥናት ላይ ያተኮረ ስነ ዘዴያዊ አቀራረብ
- ስልታዊነት
- የስብዕና እድገት ማበልጸግን መሰረት ያደረገ ስነ ዘዴያዊ አቀራረብ ናቸው፡፡

ከዚህ በመቀጠል የእነዚህን ስነ ዘዴያዊ አቀራረቦች ምንነት ባጭር ባጭሩ እንመልከት፡፡

*ሀ. አራቱን ክሂሎች በማዳበር ላይ ያተኮረ ስነ ዘዴያዊ አቀራረብ*

እንደ Lazar (1993: 27) የዚህ ስነ ዘዴያዊ አቀራረብ ስነ ዘዴያዊ ግምት በስነ ጽሑፍ አሀዶች መሳሪያነት ቋንቋን መማር መርሀ- ትምህርቱን ከቋንቋና ስነ ጽሑፍ ጋር ለማገናኘት ይረዳል የሚል ነው፡፡ ይህ አመለካከት ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ አጠቃላይ የሆነ የቋንቋ እውቀት እንዲኖራቸው ከማድረጉም በላይ በቋንቋው ውስጥ የተለመዱትን ሰዋስዋዊ፣ ቃላዊና ዲስኩራዊ ክፍሎችን በአእምሯቸው ውስጥ ቀርጸው በአስፈላጊው ወቅት ሁሉ ስነ ጽ ሑፍ ላይ ሂስ እንዲሰጡ ያደርጋቸዋል፡፡

21

የቋንቋ ክሂሎችን ለማበልጸግ የሚረዳው ስነ ዘዴያዊ አቀራረብ አብይ ትኩረቱ አንድን ስነ ጽሑፍ ቋንቋን በማስተማር ሂደት እንዴት በመሳሪያነት ወይም በምንጭነት ልንጠቀምበት እንችላለን? የሚለው ላይ ነው፡፡ የፈጠራ ስራዎች የቋንቋ አጠቃቀም ለመዳ ሂደትን ስለሚያፋጥኑ እንደምንጭ ሆነው እንዲያገለግሉ በር ይከፍታል፡፡ ከዚህ ባለፈ ይህ ስነ ዘዴያዊ አቀራረብ ስነ ጽሑፍን እንደጥናት መስክ ማጥናት ላይ፣ ስልታዊ በሆነ መልኩ ባንዳንድ ስነ ልሳናዊ ገጽታዎች ላይ ትንታኔ መስጠት ላይ…ወዘተ. ትኩረት አያደርግም (Lazar, 1993: 28)፡፡

Carter and Long (1991: 7-8) በበኩላቸው ቋንቋን መሰረት ባደረገው ስነ ዘዴያዊ አቀራረብ ላይ ለቋንቋ ክሂሎች ቅድሚያ መስጠት አስፈላጊ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ እንደነሱ አገላለጽ በዚህ ስነ ዘዴያዊ አቀራረብ በስነ ጽሑፍ አማካይነት ቋንቋን ማስተማር እጅግ ጠቃሚ ቢሆንም አፈጻጸሙ መምህር- መራሽ መሆኑ አላስፈላጊ ነው፡፡

በአጠቃላይ ቋንቋን መሰረት ያደረገና ተማሪ-መራሽ የሆነው ስነ ዘዴያዊ አቀራረብ ዋነኛ አላማው ተማሪዎች ከአሀዱ ጋር እንዲተዋወቁና ከዚህ በፊት የሚያውቁትን ልምድም ከፈጠራ ስራዎች ጋር እንዲያዛምዱ ማድረግ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አሀዱ (ጽሑፉ) ያሳደረባቸውን ስሜት ወይም ያገኙትን ግንዛቤ በጽሑፍም ሆነ በንግግር በብቃት መግለጽ እንዲችሉ ማስቻል ነው፡፡ በእንዲህ አይነቱ የመማር ማስተማር ሂደት በቋንቋ አንጻር የሚኖረው ተራክቦ አንድ መንገድን ብቻ የተከተለ አይደለም፡፡ እንደተግባራቱ አይነትና ባህሪ በጥንድ፣ በቡድን፣ በግል ተግባቦት ይካሄዳል፡፡ ይህም የተማሪዎችን የቋንቋ ክህሎት በከፍተኛ ደረጃ ያሳድጋል፡፡

*ለ. ስነ ጽሑፍን እንደጥናት መስክ በማጥናት ላይ ያተኮረ ስነ ዘዴያዊ አቀራረብ*

ይህ አቀራረብ በአብዛኛው ተግባራዊ የሚሆነው በኮሌጅ (ዩኒቨርሲቲ) ደረጃ በሚማሩ ተማሪዎች ላይ ነው፡፡ የስነ ጽሑፍ ታሪኮች፣ የስነ ጽሑፍ ይዘቶች፣ የስነ ጽሑፍ ዘሮች፣ የስነ ጽሑፍ መሰረታዊ ጉዳዮች…ወዘተ. ላይ ትኩረት የሚያደርግ አቀራረብ ነው፡፡

*ሐ. የስልታዊነት አቀራረብ*

ስልታዊነት ድንበር ለይተው የቆሙትን ሁለቱን የትምህርት ዘርፎች ማለትም ስነ ጽሑፋዊ ሂስንና ስነ ልሳንን ለማገናኘት እንደ ድልድይ ሆኖ የሚያገለግል ዘርፍ ነው፡፡

በሁለቱ የትምህርት ዘርፎች ብቻም ሳይሆን በሁለቱ የትምህርት አይነቶች፣ የቋንቋ ትምህርትና የስነ ጽሑፍ ትምህርት መካከልም የቆመ ነው (Widdowson, 1975: 3-4)።

ስነ ልሳን ለስነ ጽሑፋዊ ሂስ የሚያበረክተው የተወሰነ ፋይዳ አለ። እንደዚሁም ስነ ጽሑፋዊ ሂስ ለስነ ልሳን የሚያበረክተው ፋይዳ ይኖረዋል። ስልታዊነት በስነ ልሳንና በስነ ጽሑፍ መካከል የሚገኝ ነው ካልን እንደተነሳንበት አላማ ወደ አንዱ ሊያደላ የሚችልበት አጋጣሚ ይኖራል። ዋና ትኩረቱ ግን ከስነ ልሳናዊ እውነታዎች ጋር በተያያዙ ገለጻዎች ላይ ተመርኩዞ ትርጉምን ወይም ትርጓሜን በተቻለ መጠን ግልጽና ምልዑ በሆነ መንገድ ማቅረብ ነው (Widdowson, 1975: 1 እና Short, 1995: 1-5)።

ስልታዊነት ስነ ጽሑፋዊ ስራን ለመተንተን የሚነሳው ከመሰረታዊ እሳቤ ሲሆን ስነ ልሳናዊ ቅደም ተከተሎችን ተከትለው ትንታኔውን ያቀርባል። የስልታዊነት ባለሙያዎች ስራም ስነ ጽሑፋዊ ስራው እንዴት እንደተዋቀረ ስነ ልሳንን መሰረት በማድረግ መተንተን ነው። ስለዚህም በአንድ ጽሑፍ ውስጥ የሚገኘውን ማንኛውንም ከቋንቋ ጋር ተዛምዶ ያለውን የጽሑፍ አካል ይተነትናል (Carter, 1986: 161) ።

ስነ ጽሑፍ ያለውን አሻሚነት ለመተንተን ብሎም ለመረዳት እንዲሁም ጸሐፊው በቋንቋው እንዴት እንደተገለገለበት ለመገንዘብ ስልታዊነት እጅግ የጎላ ጠቀሜታ አለው (Widdowson, 1975: 10)። ስልታዊነት በባህሪው ራሱን ችሎ እንደማይሰራበት ዊዶውሰን ያስረዳሉ። ይኸውም የስነ ልሳንና የስነ ጽሑፍ ሂስን መሰረት አድርጎ የሚሰራበት ነው። በነዚህ ሁለት ሂሶች መካከል በእርግጥ ልዩነቶች አሉ። ልዩነታቸው የሚመነጨው ለቋንቋ ትንታኔ ከሚሰጡት ጥልቀት አንጻር ነው። ስልታዊነት በዚህ ባህሪውም ቋንቋን ለሚማሩ ተማሪዎች ከሚማሩት ቋንቋ ወይም ስነ ጽሑፍ በመነሳት ቋንቋውን እንዲረዱት ያግዛቸዋል።

*መ. የሰብዕና እድገት ማበልጸግን መሰረት ያደረገ ስነ ዘዴያዊ አቀራረብ*

ግጥም የተማሪዎችን የቋንቋ ክህሎትና ዕውቀት ከማበልጸጉም በላይ የተለያዩ ግላዊ ልምዳቸውን፣ አመለካከታቸውን፣ አስተሳሰባቸውን፣ አላማቸውን እንዲያዳብሩ ላቅ ያለ እገዛ ያደርጋል። ከዚህ ባሻገር ተማሪዎችን በማነቃቃት ለትምህርቱ ትኩረት እንዲሰጡ በማድረግ፣ እውናዊ ከሆነው የቋንቋ አጠቃቀም ጋር እንዲተዋወቁ እድል በመፍጠርም ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው።

## 2.1.7 ፈጠራዊ የቋንቋ ማስተማር ዘዴ

በጥቅሉ ሲታይ የትምህርት አሰጣጥ ዘዴ በጣም ሰፊ ጽንሰ ሀሳብ ነው፡፡ በዚህ ስር የሚካተቱ በርካታ የትምህርት አቀራረቦችና ቴክኒኮች ያሉ ሲሆን እነዚህ ቴክኒኮችና አቀራረቦች በግላቸው የተለያየ አላማን ለማስፈጸም አጋዦች ናቸው፡፡ የትምህርት አሰጣጥ ዘዴ በተማሪዎች ዘንድ ለማምጣት የምናስበውን የባህሪም ሆነ የዕውቀት ለውጥ ለማስገኘት ዋነኛ መሳሪያ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ለማምጣት የምናስባቸውን ለውጦች በአንድ ጊዜ ለማስገኘት የሚያስችል አንድ ወጥ ዘዴ ግን የለም፡፡

ስለትምህርት አቀራረብ ዘዴዎች ለመነሻ ያክል ይህን ካልን በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ከሚጠቀሱት የትምህርት አቀራረብ ዘዴዎች መካከል አንዱ ስለሆነውና በዚህ ጥናትም ልዩ ትኩረት ስለሚሰጠው ፈጠራዊ ዘዴ የተወሰኑ ሀሳቦችን እንመልከት፡፡

እንደ Ibsen (1995: 143) አገላለጽ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ፈጠራዊ ዘዴ ማለት የፈጠራ ጽሑፎችን በምንጭነት በመጠቀም የቋንቋ አጠቃቀምን ለማስተማር የሚያገለግልና በባህሪው ተማሪ- መራሽ የሆነ የማስተማር ዘዴ ነው፡፡ በፈጠራዊ ዘዴ የቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት አሀዱ (text) የክፍሉ የጋራ ተሞክሮ ወይም ልምድ ይሆናል፡፡ በዚህም በክፍሉ ውስጥ የመማር አውድ ይፈጥራል፡፡ በሌላ አገላለጽ ተማሪዎች አሀዱን ካነበቡ በኋላ የሚኖራቸው አመለካከት ወደ አንድ የጋራ አቅጣጫ እንዲያመራ ይረዳል፡፡

ፈጠራዊ ዘዴ ተማሪዎች እንዲያዳብሯቸው የሚጠበቅባቸውን ማናቸውንም ችሎታዎች (የቋንቋ አጠቃቀም፣ የመጻፍ ችሎታ ወዘተ.) በማናቸውም የመማር መስኮችና ሁኔታዎች በማስረጽ ረገድ ውጤታማ ነው፡፡ ስለሆነም በአንድ የማስተማር ጊዜ ተግባቦታዊ ችሎታ፣ ፈጠራዊ ችሎታና ባህላዊ ችሎታ ለማዳበር ሊያገለግል ይችላል፡፡ ፈጠራዊ ዘዴ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የቃላትን ፍቺ በገቡበት አውድ በመፈለግ ረገድ አራቱን ክሂሎች ያጣመረ ነው፡፡ በተጨማሪም የተማሪዎችን ማህበራዊ ክሂሎች በማዳበር ከታላሚው ቋንቋ ማህበራዊ ስርዓት ጋር ተስማምተውና ተግባብተው እንዲኖሩ ይረዳቸዋል (Ibsen, 1995)

ፈጠራዊ ዘዴ ሶስት አበይት ደረጃዎች ያሉት ሲሆን እያንዳንዱ ደረጃም በውስጡ ሁለት ሁለት ንዑሳን ደረጃዎች አሉት፡፡ ተሳትፎ (involvement) የሚባለው አብይ ደረጃ በውስጡ ገፋፊ ሀይል (impetus)ና ግብዓት (input) የሚሉትን ንዑሳን ደረጃዎች የያዘ ሲሆን

24

መስተጋብር (interaction) ደግሞ በውስጡ መለየት (identification)ና የአርምሞ (የዝምታ ጊዜ) (incubation) የሚሉትን ንዑሳን ደረጃዎች ይዟል። እንዲሁም ፍካሬ (interpretation) የሚባለው አብይ ደረጃ በውስጡ ጅማሮ (initiation)ና ማዛመድ (integration) የሚሉትን ንዑሳን ደረጃዎች ይዟል። የንዑሳን ደረጃዎች መነሻ በመሆን የሚያገለግሉት አበይት ደረጃዎች ናቸው። በደረጃ ሲታዩ አንደኛው ለአንደኛው ቅድመ ሁኔታዎች ናቸው። ማለትም የመጀመሪያው ንዑስ ደረጃ ለሁለተኛው፣ የሁለተኛው ለሶስተኛው...ቅድመ ሁኔታዎች ናቸው። ሶስቱ አበይት ደረጃዎች የያንዳንዱን ተማሪ የመማር ሂደት የሚመለከቱ ሲሆን በሁለተኛ ደረጃ የሚታዩት ስድስቱ ንዑሳን ደረጃዎች ደግሞ ስነ ዘዴያዊ ቅድመ ሁኔታዎችና ስነ ዘዴያዊ አቀራረቦችን የሚመለከቱ ናቸው (Ibsen, 1995፡ 145)

የዚህ ስነ ዘዴ አፍላቂ የሆኑት ኢብሰን እነዚህን ደረጃዎች በጥቅል መጠሪያ (the I model) የአይ ሞዴል ብለው ሰይመውታል። የስያሜው መነሻም የስድስቱ ንዑሳን ደረጃዎች ስያሜ የመጀመሪያ ፊደል አይ (I) መሆኑ ነው። ኢብሰን የፈጠሯቸውን የአይ ሞዴል ስድስቱን ደረጃዎች ከዚህ ቀጥለን አንድ በአንድ እንመልከት።

*ሀ. ገፋፊ ሀይል (Impetus)*

ይህ ደረጃ የፈጠራ ስራዎችን ተጠቅሞ ቋንቋን በመማር ማስተማር ሂደት ሀሳብን በመቀበልና በመደራደር የመጀመሪያው ደረጃ ነው። በዚህ ደረጃ የተማሪዎች የመማር ፍላጎት ይነሳሳል፣ ስሜታቸውም ይቀሰቀሳል። ይህም በክፍል ውስጥ ለሚኖረው የነቃ ተሳትፎ ምቹ አጋጣሚን ይፈጥራል። ገፋፊ ሀይል ቅብብሎሻዊ ክሂሎች በማስተማር ረገድ የቅድመ ንባብ፣ የቅድመ ማዳመጥ፣ ወይም የቅድመ ጽሕፈት ደረጃዎችን የሚሸፍን ነው።

*ለ. ግብዓት (Input)*

ይህ ደረጃ በስነ ጽሑፍ አማካይነት ተማሪዎች ቋንቋን ሲማሩ አሀዶችንና ሌሎች ስነ ጽሑፋዊ ስራዎችን የሚያነቡበት ወይም የሚያዳምጡበት ደረጃ ነው፤ ዕውቀትንና ቋንቋን ለማዳበር ዝግጁ የሚሆኑበትም ደረጃ ነው። ቀጣይ የመማር ተግባራትን ለማከናዎን ይቻል ዘንድም የነቃ የመማር ተሳትፎን የሚጠይቅ ደረጃ ነው።

25

*ሐ. ልየታ (Identification)*

ይህ ደረጃ በስነ ጽሑፍ አማካይነት የሚፈጠረው የቋንቋ ተግባቦታዊ ሚና የሚታይበት ነው፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች በስነ ጽሑፋዊ ስራዎች ውስጥ ከሚያገኟቸው ገጸ ባህሪያት፣ ጭብጦች፣ ግጭቶች...ወዘተ. በመነሳት በያንዳንዱ ጉዳይ ላይ ጥቅል ቅኝት እንዲያካሂዱ እድል ይሰጣቸዋል፡፡ ይህም ተማሪዎች ስለአንድ ነገር እንዲያስቡ እንዲያሰላስሉ ያደርጋቸዋል፡፡ በቡድንና በጥንድ እየሆኑም የፈጠራ ስራው ስላጫረባቸው ጉዳይ የሚወያዩበት ወቅት በመሆኑ የተግባቦት ሂደት በጉልህ የሚታይበት ደረጃ ነው፡፡ ከፈጠራ ስራው ውስጥ ያገኙትን ተሞክሮም ራሳቸው ከሚያውቁት ተሞክሮ ጋር እንዲያነጻጽሩ እድል ያገኛሉ፡፡

*መ. የአርምሞ (የዝምታ) ጊዜ (Incubation)*

ይህ ደረጃ ተማሪዎች ከስነ ጽሑፋዊ ስራዎች ያገኙትን ልምድ ተጠቅመው ለመናገር ወይም ለመጻፍ ዝግጅት የሚያደርጉበት ነው፡፡ በዚህ ደረጃ ግላዊ አስተውሎትና መጻፍ እንዲሁም በዚሁ ሳቢያ የሚመነጨውን ሀሳብ በማፍለቅ ውጤት ይታይበታል፡፡

*ሠ. ጅማሮ (Initiative)*

ይህ ደረጃ በፈጠራ ስራዎች አማካይነት የተነሳሱት የተማሪዎች ስሜትና ፍላጎት በተግባር ላይ የሚውሉበት ነው፡፡ ከነዚህ የፈጠራ ስራዎች የተገኙት ልምዶች በተማሪዎች አእምሮ ላይ ያነሳሱት ሀሳብ ተብላልቶ አዲስ የተግባቦት አውድ ይፈጥራል፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች በየግላቸው ያብላሉት ሀሳብ በጋራ ዳብሮ በአንድ ማዕከላዊ ነጥብ ላይ መግባባት ላይ መድረስ ያስችላል፡፡ በዚህ ደረጃ በጽሑፍ የቀረቡትን ሀሳቦች እንደገና በመቃኘት የቃላት፣ የሰዋስው ማስተካከያ ሲደረግበት ተማሪዎች ለተከታዩ ደረጃ ይዘጋጃሉ፡፡

*ረ. ማዛመድ (Integration)*

የፈጠራ ጽሑፎችን በማንበብ የተገኘን እውቀት ቀደም ሲል ከነበረ ግላዊ እውቀት ጋር ለማገናዘብ የሚቻልበት ደረጃ ነው፡፡ ቋንቋንና ስነ ጽሑፍን ማቆራኘትም የፈጠራዊ ዘዴ የመጨረሻ ግብ ነው፡፡ ይህ ደረጃ ተማሪዎች ከተለያዩ የስነ ጽሑፍ አይነቶች ጋር በመተዋወቅ ባንዱ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑት ላይ ትኩረት በማድረግ ጥሩ አንባቢዎች

26

ወይም ጸሐፊዎች ለመሆን የሚያልሙበት ነው፡፡ በስነ ጽሑፍ አማካይነት ሊገኙ የሚችሉ ጠቀሜታዎችን በተመለከተ የተሰነዘሩ አስተያየቶች የሚለኩትም በዚህ ደረጃ ነው፡፡

ኢብሰን ከዘረዘሯቸው ስድስቱ የፈጠራዊ ዘዴ ደረጃዎች በተጨማሪ ሰባተኛ ደረጃ ሊኖር ይችላል፡፡ ይኸውም መተግበር (Implementation) ነው፡፡ በዚህ ደረጃ ተማሪዎች ራሳቸው አመንጭተው ድርሰቶችን መጻፍ እንደሚችሉ መገመት ይቻላል፡፡

እነዚህ የተመለከትናቸው የፈጠራዊ ዘዴ ስነ ዘዴያዊ አቀራረቦች ሊተገበሩ የሚችሉት ተማሪውና መምህሩ በሚኖራቸው የመማር ማስተማር መስተጋብር ነው፡፡ ስነ ዘዴያዊ አቀራረቦቹ ውጤታማ ይሆኑ ዘንድ መምህራን ሊኖራቸው የሚችለውን ሚና ከዚህ ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

### 2.1.8 በፈጠራዊ ዘዴ ግጥምን በምንጭነት ተጠቅሞ ቋንቋን በማስተማር ሂደት የመምህሩ ሚና

ቋንቋን በስነ ጽሑፍ አማካይነት ለማስተማር ሲታቀድ አቀራረቡ እንደየስነ ጽሑፉ አይነት የተለያየ ይሆናል፡፡ ማለትም ልቦለድን፣ ግጥምን፣ ተውኔትን... ወዘተ. ተጠቅመን ለማስተማር በምናስብበት ጊዜ አቀራረባችን እንደየዘውጎቹ የተለያየ ይሆናል፡፡ የአቀራረብ መንገዱ የተለያየ ይሁን እንጂ የቋንቋ ትምህርት አላማ ተማሪዎች የቀረበውን ምንባብ አንብበው እንዲረዱትና ሀሳባቸውን በተለያየ መልኩ መግለጽ እንዲችሉ ማብቃት ነው፡፡ ይህ እንዲሆን ደግሞ በትምህርቱ ሂደት ተማሪዎች ብዙውን ጊዜ እንዲጠቀሙበት መምህሩ ማመቻቸት አለበት፡፡ የመምህሩ ሚና መሆን ያለበት የመምራት፣ አቅጣጫ የመጠቆም ብቻ ነው፡፡ ይህ ሲሆን የትምህርቱ አላማ ግቡን ይመታል (Lazar, 1993: 128፣ William, 1991፡ 88፣ በድሉ፣ 1996፡ 70)፡፡

አንድ መምህር ግጥምን በምንጭነት ተጠቅሞ ቋንቋን ለማስተማር ሲያስብ ሶስት ደረጃዎችን ማለፍ አለበት፡፡ እነዚህ ደረጃዎች በመምህሩ እንዴት ሊተገበሩ ይችላሉ የሚለውን በተመለከተ (Lazar, 1993: 129-131) የሚከተለውን ብለዋል፡፡

1. ቅድመ ንባብ ተግባራት

ይህ ደረጃ ተማሪዎች ስለሚያነቡት የፈጠራ ስራ ፍንጭ የሚያገኙበት ነው፡፡ ይህ ፍንጭ ለተማሪዎች ምን ጉዳይ ላይ ማተኮር እንደሚገባቸው ግንዛቤ ይፈጥርላቸዋል፡፡ የቅድመ

ንባብ ተግባር ተማሪዎች የሚሰጣቸውን የፈጠራ ስራ አንብበው እንዲረዱት በማድረግ ሂደት የስነ ልቦናና የስነ ልሳን ዝግጅት እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡

ግጥምን በመጠቀም ቋንቋን በማስተማር ሂደት ሊከናወኑ የሚገባቸውን የቅድመ ንባብ ተግባራት Lazar (1993: 129) እንዳሰፈሩት ከዚህ እንደሚከተለው እንመልከት፡፡

*ሀ. በአሀዱ ላይ ተማሪዎች ጥሩ ፍላጎት እንዲኖራቸው ለማድረግ የመምህሩ ሚና*

- ስለግጥሙ ጭብጥ አጠቃላይ ግንዛቤ እንዲያገኙና ትምህርቱን እንዲወዱት ስዕሎችን፣ የመጽሐፋን ሽፋን...ወዘተ. ማዘጋጀትና ተማሪዎች እንዲወያዩ ማድረግ፡፡
- ለተማሪዎች ከግጥሙ ውስጥ የተለያየ መስመር (ሀረግ) መስጠትና የግጥሙን ጭብጥ ወይም አብይ መልዕክት እንዲገምቱ ማድረግ፡፡
- ተማሪዎች ከግጥሙ ርዕስ፣ የተወሰኑ ቃላት ወይም ሀረጋት ተነስተው የግጥሙ ጭብጥ ምን እንደሆነ ትንበያ እንዲሰጡ ማድረግ፡፡
- ተማሪዎች በግጥሙ አንድ ተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ ራሳቸውን አስገብተው ምን ሊሰሩ እንደሚችሉና እንዴት ምላሽ ሊሰጡ እንደሚችሉ እንዲናገሩ ማድረግ፡፡

*ለ. አስፈላጊ የሆኑ ታሪካዊ ወይም ባህላዊ ዳራዎችን በመስጠት የመምህሩ ሚና*

- ተማሪዎች የግጥሙን ታሪካዊ ወይም ባህላዊ ዳራ ለመግለጽ እንዲችሉ እንዲያነቡ ወይም እንዲያዳምጡ ማድረግ፡፡
- ተማሪዎች የግጥሙን ጭብጥ በጥልቀት ይረዱት ዘንድ ስለግጥሙ ደራሲ የሕይወት ታሪክ እንዲያነቡ ወይም እንዲያዳምጡ ማድረግ፡፡
- ለተማሪዎች የግጥሙን ርዕስ በመንገር ይዘቱ ምን ሊሆን እንደሚችል እንዲገምቱ ማድረግ፡፡
- ተማሪዎች በባህላቸው ወይም ማህበረሰባቸው ዘንድ ተቀባይነት ስላለው ባህሪ ወይም ስሜት እንዲወያዩ ማድርግ፡፡ ከዚያም ከግጥሙ ታሪክ ጋር እንዲያወዳድሩና እንዲያነጻጽሩ ማድረግ፡፡

ሐ. *ተማሪዎች የግጥሙን ቋንቋ እንዲረዱት ለማድረግ የመምህሩ ሚና*

- ተማሪዎች በግጥሙ ውስጥ ያሉትን ቁልፍ ቃላት፣ ሐረጋት ወይም ሰዋስዋዊ መዋቅሮች እንዲረዷቸው ቅድመ ትምህርት መስጠት፡፡

- ተማሪዎች በግጥሙ ውስጥ ያሉ ዘይቤያዊ ወይም ተምሳሌታዊ ትርጓሜዎችን እንዲረዱ ማገዝ፡፡

- በግጥሙ ውስጥ ያልተለመዱ ወይም አስቸጋሪ ቃላት ካሉ ተማሪዎች በሚያካሂዷቸው ተግባራት ላይ የተለመዱ ቃላትን እንዲጠቀሙ ማድረግ፡፡

2. በንባብ ጊዜ የመምህሩ ሚና

ይህ ደረጃ ተማሪዎች ንቁ ንባብ እያካሄዱ መሆናቸውን መምህራን የሚቆጣጠሩበትና የሚከታተሉበት ነው፡፡ እነዚህ ተግባራት ተከታዮቹን ይመስላሉ (Lazar, 1993: 130)፡፡

- የግጥሙን ፍሬ ሀሳብ መረዳታቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ሁለት ወይም ሶስት ጥያቄዎችን መጠየቅ፡፡

- የግጥሙን የተዘበራረቀ ትርጉም (በመስመር ወይም በስንኝ) መስጠትና መልሰው እንዲያስተካክሉት ማድረግ፡፡

- በግጥሙ ውስጥ የሚገኙ የተወሰኑ ቃላትን ማውጣትና ተማሪዎች በራሳቸው ወይም ከሚሰጣቸው የቃላት ዝርዝር ክፍተቱን እንዲሞሉት ማድረግ፡፡

- ተማሪዎች አንድ ስንኝ እንዲያነቡና ቀጥሎ ምን ሊመጣ እንደሚችል ግምት እንዲሰጡ ማድረግ፡፡

- የቃላቱን ትርጉም በገቡበት አውድ እንዲመልሱ ለማድረግ የምርጫ ጥያቄዎችን ማቅረብ፡፡

- ተማሪዎች ግጥሙን እንዲያነቡ በማድረግ ከባድ ቃላትን ለይተው እንዲያወጡና የመዝገበ ቃላት ፍቺዎቻቸውን እንዲያመጡ ማድረግ፡፡

- ከግጥሙ የተወሰዱ ቃላትን ከሌሎች ቃላት ጋር እንዲያዛምዱ ማድረግ፡፡

3. በድህረ ንባብ ጊዜ የመምህሩ ሚና

ይህ ደረጃ ተማሪዎች ያነበቡትን ጽሑፍ በተመለከተ የሚቀርቡላቸውን የተለያዩ ጥያቄዎች የሚመልሱበት ነው፡፡ የሚና ጨዋታ፣ ማጠቃለያ፣ ውይይት፣ ክርክር… ወዘተ. ተግባራት በዚህ ጊዜ የሚከናወኑ ናቸው፡፡ ክሂሎቹም ተቀናጅተው የሚቀርቡበት ነው፡፡ እንደ Lazar (1993: 130) በድህረ ንባብ ወቅት ግጥምን ተጠቅሞ ቋንቋን በማስተማር ሂደት ተከታዮቹ ተግባራት ከመምህራን ይጠበቃሉ፡፡

- የግጥሙን ጭብጥ መሰረት ያደረጉ ጥያቄዎችን በማቅረብ ተማሪዎች እንዲከራከሩና እንዲወያዩ ማድረግ፡፡
- ተማሪዎች የግጥሙን ጭብጥ መሰረት አድርገው ሁለት ወይም ሶስት ግልጽ ትንታኔዎች እንዲሰጡና የትኛው ይበልጥ ተገቢ እንደሆነ እንዲወስኑ ማድረግ፡፡
- ግጥሙ በጥንታዊ ቋንቋ የተጻፈ ከሆነ ተማሪዎች አሁን ባለው ዘመናዊ ቋንቋ ከተጻፈ ግጥም ጋር እንዲያነጻጽሩት ማድረግ፡፡ የሚመረጠው ግጥም በትርጉምም ሆነ በድምጸት የተቀራረበ መሆን አለበት፡፡
- የግጥሙን ታሪክ በሚና ጨዋታ መልክ በቡድን እንዲያቀርቡት ማድረግ፡፡
- ግጥም ያለውን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ስነ ትምህርታዊ፣ ባህላዊ፣ ፖለቲካዊ…ወዘተ. ፋይዳ አስመልክቶ ሂሳዊ ውይይት እንዲያደርጉ ማበረታታት፡፡
- ተማሪዎች ግጥምን ጮክ ብለው እንዲያነቡ ማለማመድ፡፡
- ተማሪዎች ግጥሙን በገዘርው መልክ እንዲጽፉት ማድረግ፡፡
- የቀረበውን ግጥም እንደመነሻ በማድረግ ተማሪዎች የራሳቸውን ግጥም እንዲጽፉ መገፋፋት፡፡

ከዚህ በላይ ለማቅረብ እንደተሞከረው መምህሩ ስነ ጽሑፍን በምንጭነት ተጠቅሞ ቋንቋን ሲያስተምር የራሱ የሆኑ ሚናዎች አሉት፡፡ እነዚህ ሚናዎች የመምህሩን ሙሉ ጣልቃ ገብነት የሚፈቅዱ መሆን የለባቸውም፡፡ ብዙውን ተግባር ተማሪዎች ሊያከናውኑ ይገባል፡፡ የመምህሩ ሚና ሊሆን የሚገባው አቅጣጫ ማሳየት ነው፡፡ ይህ ሲሆን በስነ ጽሑፍ ቋንቋን

30

በማስተማር ሂደት የሚከሰቱ መሰናክሎች ይቀንሳሉ፡፡ ተማሪዎችም ከመምህሩ ብቻ ጠባቂ እንዳይሆኑ ያደርጋል (Carter and Long, 1991: 14)፡፡

## 2.1.9 ከአንድ አሀድ ውስጥ የሚዘጋጁ መልመጃዎች አይነትና ባህሪያት

### 2.1.9.1 የመልመጃዎች ባህሪያት

Nuttal,C (1982፡ 120) እና Silberstein,S (1994፡ 135) እንደሚያስረዱት አንብቦ መረዳትን ለማዳበር የሚያስችሉ ከአንድ አሀድ ሊወጡ የሚችሉ መልመጃዎች ባህሪያት ከሚባሉት ውስጥ ዋና ዋናዎቹ ተከታዮቹ ናቸው፡፡

ሀ. የቃል በቃል ምላሽ የሚሹ መልመጃዎች

የዚህ አይነት ባህሪ ያላቸው መልመጃዎች ተማሪዎች ከሚያነቡት ጽሑፍ ውስጥ በቀላሉና ብዙም ሳይቸገሩ የሚቀርብላቸውን ጥያቄ ለመመለስ የሚያስችሉ ናቸው፡፡ በነዚህ አይነት መልመጃዎች የሚቀርቡ ጥያቄዎች መልሳቸው ከቀረበው አሀድ ውስጥ በቀጥታና በተሟላ ሁኔታ የሚገኝባቸው ናቸው፡፡ ስለዚህ ተማሪው መልስ ለመስጠት ከአሀዱ ውጭ መሄድ አይጠበቅበትም፡፡

ለ. በራስ አገላለጽ የሚመለሱ መልመጃዎች

የዚህ አይነት ባህሪ ያላቸው መልመጃዎች ከላይኞቹ የተለዩ ናቸው፡፡ እነዚህኞቹ መልመጃዎች የተማሪዎችን የራስ አገላለጽና የቃላት አጠቃቀም የሚጠይቁ ናቸው፡፡ እንደላይኞቹ ቃል በቃል የሚመለሱ አይደሉም፡፡ ስለሆነም የአሀዱን ጭብጥ በሚገባ መረዳት የግድ አስፈላጊ ነው፡፡ እነዚህ አይነት መልመጃዎች አሀዱን መሰረት አድርገው ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ሀሳቡን ሳያዛቡ በራስ አገላለጽ መልስ መስጠትን የሚጠይቁ ናቸው፡፡ በመሆኑም የተማሪዎችን የፈጠራ አቅም በማነሳሳትና አዲስ ሀሳብ እንዲያፈልቁ በማድረግ ረገድ ላቅ ያለ ጠቀሜታ አላቸው፡፡

ሐ. አውዳዊ መልስ የሚሹ መልመጃዎች

የዚህ አይነት ባህሪ ያላቸው መልመጃዎች ተማሪዎች በቃላት፣ በሀረጋትና በዐነገራት መካከል ሊኖር የሚችለውን የሀሳብ ትስስር በውል ተረድተው ምላሽ እንዲሰጡ

31

የሚያደርጉ ጥያቄዎችን የያዙ ናቸው፡፡ መልመጃዎቹ አላማቸውን ይመቱ ዘንድ መምህራን ተከታዮችን ተግባራት ቢያከናውኑ ይመረጣል፡፡

- በአሀዱ ውስጥ ቁልፉ ሀሳብ የያዙ የተወሰኑ ቃላትን አውጥቶ ያልተሟላውን ሀሳብ መሰረት በማድረግ የሚመለሱ አውዳዊ ጥያቄዎችን መስጠት፣
- ከበድ ከበድ ያሉ ቃላት ያሉበት የተሟላ ጽሑፍ ሰጥቶ ጥያቄዎችን (በአውድ) እንዲመልሱ ማድረግ፣
- በሚገቡበት አውድ የትርጉም ለውጥ የሚያመጡ ቃላትን እንዲለዩና ከመዝገበ ቃላዊ ፍቻቸው ጋር እንዲያነጻጽሩ ማገዝ፣
- ከቃላት ባሻገር ሀረጋትንና ዐ.ነገራትን በአገባባቸው መሰረት መፍታት (መተርጎም) እንዲችሉ የሚያስችሉ መልመጃዎችን መስጠት፣ ማሰራት፡፡

መ. ግምገማን የሚሹ መልመጃዎች

ተማሪዎች በመልመጃዎቹ ውስጥ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች መልስ እንዲሰጡ ብቻ ሳይሆን ምንና እንዴት እንደሚመልሱም ጭምር ተረድተው መልሳቸው ላይ ተጨባጭ መረጃዎች እንዲያቀርቡ የሚጠይቁ መልመጃዎች ናቸው፡፡ እንደዚህ አይነት ባህሪ ያላቸው መልመጃዎች የተማሪዎችን የአስተሳሰብ ደረጃ ከፍ እንዲል የሚያደርጉ ናቸው፡፡ የውስብስብነት ባህሪ የሚስተዋልባቸው ናቸው፡፡ ከዚህ ባሻገር ተማሪዎች መልስ ከመስጠታቸው በፊት በአሀዱ ውስጥ የቀረበውን ሀሳብ ከራሳቸው አመለካከት አኳያ መተንተንን ወይም መገምገምን እንዲለማመዱ ያደርጋል፡፡ ምክንያቱም መልመጃዎቹ የተማሪዎችን ሂሳዊ አስተሳሰብ፣ ምናብንና ልምድንም ጭምር የሚጠይቁ መሆናቸው ነው፡፡

ሠ. ግላዊ አስተያየትን የሚሹ መልመጃዎች

ተማሪዎች የተመረጠውን አሀድ ከተለያዩ ተዛማጅ አሀዶች ጋር አገናዝበው፣ ከራሳቸው ገጠመኝ ጋር በማነጻጸርና በማወዳደር የግል አመለካከታቸውን እንዲሰጡ የሚጋብዙ ጥያቄዎችን የሚይዙ መልመጃዎች ናቸው፡፡ አቀራረባቸውም ‹‹ስለዚህ ጉዳይ ያለህ/ሽ አቋም ምን ይመስላል፣ ከዚህ በላይ ስለቀረበው ሀሳብ ምን አስተያየት አለህ/ሽ›› የሚል አይነት ነው፡፡

3~

ረ. የማስታወስ ችሎታን የሚጠይቁ መልመጃዎች

የዚህ አይነት ባህሪ ያላቸው መልመጃዎች ተማሪዎች ቀደም ብለው ያነበቡትን አሀድ መልመጃዎችን ሲሰሩ መለስ ብለው እንዲያስታውሱ በማድረግ አሁን ከገበዩት አዲስ እውቀት ጋር እንዲያገናዝቡ የሚያደርጉ ጥያቄዎችን የያዙ ናቸው፡፡ ለምሳሌ አሁን ካነበብከው/ሽው አሀድ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ሀሳብ ያለው ሌላ አሀድ አንብበህ/ሽ ታውቃለህ/ ታውቂያለሽ፡፡

### 2.1.9.2 የመልመጃዎች አይነት

በስነ ጽሑፍ አማካይነት ቋንቋን ለማስተማር ከተመረጠ አሀድ የሚዘጋጁ መልመጃዎች በሁለት አይነት ይከፈላሉ፤ የቋንቋ መልመጃዎች (Language Exercises) እና ስነ ጽሑፋዊ (የይዘት) መልመጃዎች (Literary or Content Exercises) ተብለው (Waker, 1983: 6-9)፡፡ ዝርዝሩን ቀጥለን እንመልከት፡፡

1. የቋንቋ መልመጃዎች

የቋንቋ መልመጃዎች የተማሪዎችን የቋንቋ ችሎታ የሚያዳብሩና ለሚያጋጥሟቸው ስነ ጽሑፋዊ መልመጃዎች በደንብ የሚያዘጋጇቸው ሆነው ሊዘጋጁ ይገባል፡፡ በቋንቋ መልመጃዎች ውስጥ ተከታዮቹ መልመጃዎች ይካተታሉ፡፡

ሀ. የዐ.ነገር አወቃቀር መልመጃዎች

የነዚህ አይነት መልመጃዎች በቤት ስራ መልክ በጽሑፍ ተዘጋጅተው እንዲቀርቡ ሊደረጉ ይችላሉ፡፡ ወይም በክፍል ውስጥ በጥንድ/ በቡድን ሊሰሩ ይችላሉ፡፡

ለ. የቃላት መልመጃዎች

በአንድ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ሰዎች ከ90% በላይ የሚሆኑ ቃላትን ከአውድ ጋር በተገናኘ መልኩ ይማራሉ፡፡ ይሁን እንጂ በስነ ጽሑፍ ውስጥ የሚገኙትን ቃላት በተራ ንግግር ወይም ጽሑፍ ውስጥ እንደሚገኙ ቃላት በቀላሉ ለመገንዘብ አስቸጋሪ ነው፡፡ ስለሆነም ተማሪዎች የቃላትን አውዳዊ ፍቺ ለመረዳት የሚሰጣቸውን አሀድ በተለያየ አቅጣጫ ሊፈትሹት ግድ ይላል፡፡ ይህን ባደረጉ መጠን የቃላት እውቀታቸው ይጨምራል፣ በስነ ጽሑፋዊ ስራውም የመሳብና የመደሰት ነገር ይመጣል፡፡

ቀጥለው የተዘረዘሩት ፋይዳዎች በስነ ጽሑፍ አውድ ተጠቅሞ ቃላትን ማስተማር የሚያስገኛቸው ናቸው።

- በቀረበላቸው አሀድ ውስጥ የሚገኙ የከባድ ቃላትን ፍቺዎች ለማወቅ አገባባዊ፣ ሰዋስዋዊ፣ ተጠየቃዊ ፍንጮችን ለመጠቀም ያስችላቸዋል፣
- የቃላት እውቀታቸው በከፍተኛ ደረጃ ያድጋል፣
- በአሀዱ ውስጥ የተካተቱ ቁልፍ ቃላትን ለመረዳት ይረዳቸዋል፣
- የቃላትን ትርጓሜ ለማወቅ የሚያደርጉት ዳሰሳ የመማር ፍላጎታቸው ከፍ እንዲል ያደርጋል።

ሐ. ክፍት ቦታዎችን በመሙላት የሚሰሩ መልመጃዎች

በአንድ ጽሑፍ ውስጥ ክፍት ቦታዎችን በመተው ወይም ቃላትን በመግደፍ ተማሪዎች ለቦታው ተስማሚ የሆነውን ቃል መርጠው ወይም ገምተው እንዲሞሉ ለማድረግ የሚያስችሉ መልመጃዎች ክፍት ቦታዎችን በመሙላት የሚሰሩ መልመጃዎች ይባላሉ። እነዚህን አይነት መልመጃዎች መስራት ተከታዮቹን ጠቀሜታዎች ያስገኛል።

- የጽሕፈት ክሂልን ለማጎልበተ ያስችላል፣

- አንድን ጽሑፍ በትኩረት የማንበብ ልምድን ያሳድጋል፣

- የቀረበውን ጽሑፍ ጠንቅቆ የማንበብና የማስታወስ ችሎታን ያጎለብታል፣

- ጽሑፍን በትኩረት የማንበብ ልምድን ስለሚያዳብር በጸሐፊው የተፈጠሩ ችግሮች/ ስህተቶች ካሉ ለይቶ ለማውጣትና ማስተካከያ ለመስጠት ያስችላል።

መ. አንድን ዐ.ነገር በሌላ አቅጣጫ ወይም መንገድ መጻፍን (Paraphrasing) ለመለማመድ የሚያስችሉ መልመጃዎች

የዚህ አይነት መልመጃዎች ተማሪዎች የቀረበውን ጽሑፍ በራሳቸው አገላለጽ በተለየ መንገድ እንዲጽፉ ለማድረግ የሚያስችሉ ናቸው። እነዚህ አይነት መልመጃዎችን ማሰራትም ተከታዮቹን ፋይዳዎች ያስገኛል።

- የተለያዩ የዐ.ነገር አይነቶች (ነጠላ፣ ድርብ/ ውስብስብ) መኖራቸውን ያስገነዝባሉ፣

34

- በዐ.ነገር ውስጥ የሚገኙ መዋቅሮች (መስተዋድድ፣ ተውሳከ ግስ፣ ገላጭ…) በአንድ ዐ.ነገር ውስጥ ያላቸውን ሚና ለማወቅ ያስችላሉ፣

- አንድን ዐ.ነገር በልዩ ልዩ መንገድ መጻፍን/ መናገርን ያስለምዳሉ፡፡

2. የስነ ጽሑፍ (የይዘት) መልመጃዎች

እነዚህ አይነት መልመጃዎች የተለያዩ ትርጓሜዎችን ለመስጠት የሚያስችሉ ክፍት ጥያቄዎችን የሚይዙ ሲሆኑ ለክፍል ውስጥ ውይይትና ክርክር ጥሩ መነሻ በመሆንም ያገለግላሉ፡፡ ይህ ውይይትና ክርክርም የንግግር፣ የጽሕፈት ወዘተ. ክሂሎችንና የእውቀት ዘርፎችን ለማጎልበት ያስችላል፡፡ በነዚህ መልመጃዎች ውስጥ የሚካተቱና የተለያየ ፋይዳ ያላቸው ንዑሳን መልመጃዎች አሉ፡፡ ቀጥለን እንመልከታቸው፡፡

ሀ. መዋቅራዊ መልመጃዎች

መዋቅራዊ መልመጃዎች ሁለት አይነት አቀራረብ አላቸው፡፡ አንደኛው በአዛምድ መልክ የሚቀርብ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ አንድ ጽንሰ ሀሳብ የያዙ ጅምር ዐ.ነገሮችን በመስጠት አሟልተው እንዲጽፉ በመጠየቅ የሚቀርብ ነው፡፡ እንደነዚህ አይነት መልመጃዎች ቀጣዮቹን ጠቀሜታዎች ይለግሳሉ፡፡

- ለአሰሳና አስተውሎት ንባብ ቅድሚያ መስጠትን ያስተምራሉ፣

- ዋና ዋና ሀሳቦችን መሰረት አድርጎ ልዩ ልዩ ማጠቃለያዎች መጻፍን ያለማምዳሉ፣

- የሚነበበውን ክንውን መሰረት በማድረግ አንድን ክንውን/ ተግባር በጽሑፍ ወይም በንግግር ቅደም ተከተልን ተከትሎ ማስፈርን ያስተምራሉ፡፡

ለ. ገጸ-ባህሪያትን መሰረት ያደረጉ መልመጃዎች

እንደነዚህ አይነት መልመጃዎች ተማሪዎች ከገጸ ባህሪያት ጋር እንዲተዋወቁ ለማድረግ፣ የገጸ ባህሪትን አካላዊ ገለጻ መሰረት በማድረግ ገላጭ ድርሰት እንዲጽፉ ለማበረታታት፣ ከተለያዩ የአጻጻፍ ስልቶች ጋር እንዲተዋወቁ ለማድረግ፣ ገጸ ባህሪያትን በባህሪ እንዲገልጹ (የዋህ፣ ደግ፣ ክፉ…) ለማድረግ የሚያስችሉ ናቸው፡፡

ሐ. ክፍት መልመጃዎች

ተማሪዎችን በማወያየትና ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ በማድረግ የቋንቋ ችሎታቸውን ለማዳበር የሚያስችሉ መልመጃዎች ናቸው (Nuttal, 1982: 126)። እንደነዚህ አይነት መልመጃዎች ተከታዮቹ ጠቀሜታዎች አሏቸው።

- በሚደረገው የርስ በርስ ውይይት የቋንቋ ችሎታን በከፍተኛ ደረጃ ያጎለብታሉ፣

- በግል፣ በጥንድ፣ በቡድን መልስ መመለስን ያበረታታሉ፣

- አሀዱ ከተነበበ በኋላ የተገኘውን ግንዛቤ ከሚያውቋቸው ነገሮች ጋር ማገናዘብን ያስተምራሉ።

መ. ሐተታዊ መልመጃዎች

እንደነዚህ አይነት መልመጃዎች ደግሞ በስነ ጽሑፍ አማካይነት ምን እንዴት እንደተባለ ለመገንዘብ ተማሪዎች የተለያዩ ትርጓሜዎችን ያከናውናሉ። በዚህ ሂደትም ተማሪዎች ስነ ጽሑፋዊ ስራውን በንቃት ያነባሉ፤ በትምህርቱ ወቅትም ንቁ ተሳትፎ ያደርጋሉ። ሐተታዊ መልመጃዎች የደራሲው የቋንቋ አጠቃቀም ምን እንደሚመስል ለመመርመር ያስችላሉ፣ደራሲው ያለውን የአጻጻፍ ስልት በመገንዘብ ተማሪዎች የራሳቸውን ችሎታ እንዲያዳብሩ ያስችላሉ።

## 2.2 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

አማርኛ ቋንቋን በማስተማር ረገድ ስነ ጽሑፍ ያለውን ሚና በሚመለከት ብዙ ጥናቶች ተካሂደዋል ብሎ አፍን ሞልቶ መናገር አይቻልም። ይሁን እንጂ የተወሰኑ ጥናቶች በጉዳዩ ላይ ተካሂደዋል። አጥኝው ባደረገው ፍተሻም ወደ አምስት የሚደርሱ ጥናቶች በሁለተኛ ዲግሪ ደረጃ ተካሂደዋል። እነዚህ ጥናቶች ከዚህ ጥናት ጋር በቀጥታም ባይሆን በተዘዋዋሪ ተቀራራቢነት ያላቸው በመሆኑ በዚህ ክፍል እንደሚከተለው ተቃኝተዋል።

በተደረገው ዳሰሳ በጉዳዩ ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ የቀረበው ጥናታዊ ጽሑፍ የዘመንፈስ ባራኪ (1991) ጥናት ነው። የጥናቱ ርዕስ ‹‹በስነ ጽሑፍ አማካይነት አማርኛ ቋንቋን በማስተማር የአጭር ልቦለድ ሚና በ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ጥናት›› የሚል ነው። የጥናቱ ዋነኛ አላማ በአጭር ልቦለድ አማካይነት አማርኛ ቋንቋን በማስተማር

36

ተማሪዎች ሀሳባቸውን በጽሑፍ የመግለጽ ችሎታቸውን ማዳበራቸውን በሙከራ ማረጋገጥ ነው። ጥናቱ በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያነት የቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናንና የጽሑፍ መጠይቅን ተጠቅሟል። መጠናዊ የምርምር ዘዴን በመረጃ መተንተኛነት የተጠቀመ ሲሆን በጥናቱ መሰረት የተገኘው ውጤት እንደሚያመለክተው በሙከራዊ ሁኔታ በአጥኚው የተማሩት ተማሪዎች የተሻለ ውጤት አስመዝግበዋል።

የዘመንፈስ ጥናት ከኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ስነ ጽሑፍን መሰረት አድርጎ አማርኛ ቋንቋን በማስተማር ላይ ያተኮረ መሆኑ ነው። ከዚህ ባሻገር በፈጠራዊ ዘዴ አማርኛ ቋንቋን ስነ ጽሑፍን ተጠቅሞ ማስተማር ውጤታማ መሆን አለመሆኑን በሙከራ ለማረጋገጥ መነሳቱ ያመሳስለዋል።

የዘመንፈስ ጥናት ምንም እንኳ ከኔ ጥናት ጋር የሚመሳሰልባቸው ጉዳዮች ቢኖሩም ጉልህ ልዩነቶችም አሉት። ከልዩነቶቹ መካከል አንደኛው የዘመንፈስ ጥናት በምንጭነት የተጠቀመው አጭር ልቦለድን ሲሆን የኔ ጥናት ግን ግጥምን ነው። እንደዚሁም የዘመንፈስ ጥናት አጭር ልቦለድ የጽሕፈት ክሂልን ለማጎልበት ያለውን ሚና ለማረጋገጥ ታስቦ የተካሄደ ሲሆን የኔ ጥናት ግን ግጥም የአማርኛ ቋንቋ አንብቦ መረዳትና ጽሕፈት ክሂሎችን ለማሳደግ ያለውን ሚና በሙከራ ለማረጋገጥ የተደረገ ነው። በመረጃ መተንተኛነት የተጠቀመውም መጠናዊ ዘዴን ሲሆን የኔ ጥናት ግን ከመጠናዊ ዘዴ በተጨማሪ አይነታዊ ዘዴንም ተጠቅሟል። ከዚህ ባሻገር የዘመንፈስ ጥናት በ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተሞከረ ሲሆን የኔ ጥናት ግን በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተሞከረ ነው። ከቦታና ከዘመን አንጻርም ልዩነቶች አሉት። የዘመንፈስ ጥናት በ1991 ዓ.ም በአዲስ አበባ የካቲት 12 ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ላይ የተካሄደ ሲሆን የኔ ግን በ2005 ዓ.ም በደምበጫ ከፍተኛ ትምህርት መሰናዶና አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ላይ የተካሄደ ነው።

ሌላው የክንፈሚካኤል ሱጋ (1995) ጥናት ነው። የጥናቱ ርዕስ ‹‹ስነ ጽሑፋዊ ይዘቶች የተማሪዎችን የቋንቋ ክሂልና የስነ ጽሑፍ እውቀት ለማሳደግ ያላቸው አገዛ በ1993ና በ1994 ዓ.ም ለ10ኛ እና 11ኛ ክፍል መማሪያነት በተግባር ላይ በዋሉ መጻህፍት›› የሚል ነው። የጥናቱ ዋነኛ አላማ በተጠቀሱት መጻህፍት ውስጥ የተካተቱት ስነ ጽሑፋዊ ይዘቶች የቋንቋ ክሂሎችንና የስነ ጽሑፍ እውቀትን ለማዳበር ያላቸውን ውጤታማነት መፈተሽ ነው። ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች በሰነድ ፍተሻና በጽሑፍ መጠይቅ

ተሰብስበዋል። በጥናቱ መጨረሻ የተገኘው ውጤት እንደሚያመለክተው አራቱን ክሂሎች በማሳደግ ረገድ የስነ ጽሑፍ ይዘቶች የጎላ ጠቀሜታ አላቸው።

የክንፈሚካኤል ጥናት ከኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው የተለያዩ ስነ ጽሑፋዊ ጽንሰ ሀሳቦችን ያካተተ መሆኑ ነው። የሚለየው ደግሞ የክንፈሚካኤል ጥናት በተጠቀሱት መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱትን ሁሉንም የስነ ጽሑፍ ዘሮች የሚመለከት መሆኑ ነው። የኔ ጥናት ግን ግጥም የአማርኛ ቋንቋን በማስተማር ረገድ ያለውን ሚና በሙከራ ለማረጋገጥ የተካሄደ ነው።

በሶስተኛ ደረጃ የሚጠቀሰው ጥናት የጌትነት ታፈረ (1998) ጥናት ነው። የጌትነት ጥናት ‹‹ልቦለድን በመጠቀም በክፍል ውስጥ የአንብቦ መረዳት ትምህርት አቀራረብ ፍተሻ›› የሚል ርዕስ ያለው ነው። ዋነኛ አላማው መምህራን ልቦለድን ተጠቅመው የአንብቦ መረዳት ትምህርትን ሲያስተምሩ የአቀራረብ ሁኔታቸውን መፈተሽ ነው። ጥናቱ በቪዲዮ የታገዘ ምልከታን፣ የጽሑፍ መጠይቅንና ቃለ መጠይቅን በመረጃ መሰብሰቢያነት ተጠቅሟል። በዚህ መሰረት የተገኘው ውጤት እንደሚጠቁመው መምህራኑ የአንብቦ መረዳት ትምህርት አቀራረብ ደረጃዎችን ባግባቡ እንደማይጠቀሙና የአንብቦ መረዳት የማስተማሪያ ስልቶችን በብቃት እንደማይተገብሩ መረዳት ተችሏል።

ይህ ጥናት ከኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ስነ ጽሑፍ በቋንቋ ትምህርት ረገድ የሚያበረክታቸውን ጽንሰ ሀሳባዊ ማብራሪያዎች በማካተቱ ነው። የሚለየው ደግሞ የጌትነት ጥናት ልቦለድን በመጠቀም የክፍል ውስጥ የአንብቦ መረዳት ትምህርት አቀራረብን ለመፈተሽ የተደረገ በመሆኑ ነው። የኔ ጥናት ግን ግጥም የአማርኛ ቋንቋን በማስተማር ረገድ ያለውን ሚና በሙከራ ለማረጋገጥ አልሞ የተነሳ ነው።

ሌላው ጥናት የዳዊት ፍሬሕይወት (2000) ጥናት ነው። ጥናቱ ‹‹በቤኒሻንጉል ጉሙዝና በጋምቤላ ክልሎች ለመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ እርከን (7ኛና 8ኛ ክፍል) ተማሪዎች በተዘጋጁ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱ ስነ ጽሑፋዊ ስራዎች አመራረጥና አደረጃጀት›› የሚል ርዕስ አለው። የጥናቱ ዋነኛ አላማ በተጠቀሱት ክልሎች ለ7ኛ ና 8ኛ ክፍል ተማሪዎች በተዘጋጁ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የሰፈሩት የስነ ጽሑፍ ስራዎች እንዴት እንደተመረጡና እንደተደራጁ መመርመር ነው። ጥናቱ የሰነድ ፍተሻን፣ የጽሑፍ መጠይቅን ና ቃለ መጠይቅን በመረጃ መሰብሰቢያነት

ተጠቅሟል፡፡ በዚህ መሰረት የጥናቱ ውጤት እንደሚያመለክተው የተመረጡት ብዙዎቹ ስነ ጽሑፋዊ ይዘቶች የርዝማኔ ችግር የሚስተዋልባቸው፣ የተማሪዎችን እድሜ ያላገናዘቡ፣ ከቀላል ወደ ከባድ ያልተደራጁ፣ ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት የሌላቸው ወዘተ. ሆነው ተገኝተዋል፡፡

የዳዊት ጥናት ከኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው እንደሌሎቹ ሁሉ ስነ ጽሑፋዊ ጽንሰ ሀሳቦችን ማንሳቱ ወይም ስነ ጽሑፍ ላይ ማተኮሩ ነው፡፡ የዳዊት ጥናት በመጻሕፍት ውስጥ የተካተቱ ስነ ጽሑፋዊ ይዘቶችን እንዴት እንደተመረጡና እንደተደራጁ ለመፈተሽ የተደረገ ሲሆን የኔ ግን ግጥም የአማርኛ ቋንቋን ለማስተማር ያለውን ሚና በሙከራ ማረጋገጥ ላይ ያተኮረ ነው፡፡

የመጨረሻው የጌትነት አዲስ (2001) ጥናት ነው፡፡ የጥናቱ ርዕስ ‹‹ በረጅም ልቦለድ ቅንጫቢ አማርኛ ቋንቋን ማስተማር ያለው ውጤታማነት በተመረጠ አንድ የምስራቅ ጎጃም ዞን ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ጥናት›› የሚል ነው፡፡ የጥናቱ አብይ አላማ በረጅም ልቦለድ ቅንጫቢ አማካይነት በፈጠራዊ ዘዴ አማርኛ ቋንቋን ማሰተማር ጽሕፈትን፣አንብቦ መረዳትን፣ የቃላት ፍቺ መለየትን፣ ዐ.ነገሮችን በሌላ አባባል መጻፍን፣ በአያያዥ ቃላት ባዶ ቦታዎችን መሙላትን ወዘተ. ለማስተማር ያለውን ውጤታማነትና ተተግባሪነት በሙከራ ማረጋገጥ ነው፡፡ ጥናቱ የቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናንና የጽሑፍ መጠይቅን በመረጃ መሰብሰቢያነት ተጠቅሟል፡፡ መጠናዊ የምርምር ዘዴንም በመተንተኛ ዘዴነት ተጠቅሟል፡፡ በዚህ መሰረት የጥናቱ ውጤት እንደሚጠቁመው በስነ ጽሑፍ (ረጅም ልቦለድ) አማካይነት የአማርኛ ቋንቋን ማስተማር ውጤታማ ነው፡፡

የጌትነት ጥናት ከኔ ጥናት ጋር የሚመሳሰለው ስነ ጽሑፍን ተጠቅሞ አማርኛ ቋንቋን ማስተማር ውጤታማ መሆን አለመሆኑን በሙከራ ለማረጋገጥ አልሞ መነሳቱና በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ማተኮሩ ነው፡፡

የጌትነት ጥናት ከዚህ በላይ በተጠቀሱት ነጥቦች ከኔ ጥናት ጋር የሚመሳሰል ቢሆንም ልዩነቶችም ግን አሉት፡፡ ከነዚህ መካከል አንደኛው የጌትነት ጥናት ረጅም ልቦለድን በምንጭነት የተጠቀመ ሲሆን የኔ ጥናት ግን ግጥምን በምንጭነት የተጠቀመ መሆኑ ነው፡፡ ከዚህ ባሻገር የጌትነት ጥናት በመረጃ መተንተኛነት የተጠቀመው መጠናዊ ዘዴን

ሲሆን የኔ ጥናት ግን ከመጠናዊ ዘዴ በተጨማሪ አይነታዊ ዘዴንም ተጠቅሟል፡፡ እንዲሁም ጥናቶቹ ከተከናወኑበት ጊዜና ቦታ አንጻርም ልዩነት አላቸው፡፡ የጌትነት ጥናት በ2001 በጎጃም በር ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ላይ የተካሄደ ሲሆን የኔ ግን በ2005 በደምበጫ ከፍተኛ ትምህርት መሰናዶና አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ላይ የተደረገ ነው፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

# 3. የጥናቱ ዘዴ

ይህ ጥናት የተከተለው የአጠናን ዘዴ በዋናነት መጠናዊ ዘዴን ነው፡፡ በአጋዥነት ደግሞ አይነታዊ ዘዴን ተጠቅሟል፡፡ ከዚህ በመነሳትም በስታትስቲካዊ የመረጃ መተንተኛ በመጠቀም በሙከራ የታገዘ ምርምር ተካሂዷል፡፡ ስለዚህ የጥናቱን ውጤት በቁጥር ለመግለጽ ያመች ዘንድ የቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተና በተግባር ላይ ውሏል፡፡ ይህ ዘዴ ሁለት ተጠኝ ቡድኖች ምንም ሳይማሩና በተለያየ ዘዴና ሁኔታ ከተማሩ በኋላ ባስመዘገቧቸው የፈተና ውጤቶች አማካይነት ያሳዩትን የችሎታ ልዩነት ለመመዘን የሚያስችል ነው ( Hatch and Farhaday, 1982: 22፣ Dyer, 1995: 205፣ ያለው፣ 1998: 194)፡፡ የጥናቱን አስተማማኝነት ይበልጥ ከፍ ለማድረግም የአይነታዊ ምርምር አካል በሆነው የጽሑፍ መጠይቅ እንዲታገዝ ተደርጓል፡፡ ከዚህ ባሻገር ኢ- መደበኛ በሆነ መልኩ በትምህርቱ ሂደት ተማሪዎች ስለትምህርት አሰጣጡና ስለ ማስተማሪያ ዘዴው አስተያየታቸውን እንዲሰጡ ለማድረግ ተሞክሯል፡፡

## 3.1 የት/ቤትና የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ

### 3.1.1 የት/ቤት አመራረጥ

የዚህ ጥናት አብይ ትኩረት ፈጠራዊ ዘዴን በመጠቀም የአማርኛ ቋንቋን አንብቦ መረዳትና ጽሕፈት ክሂሎች ለማስተማር ግጥም ምን ያክል ሚና እንዳለው በሙከራ ማረጋገጥ መሆኑ ቀደም ሲል ተጠቅሷል፡፡ ይህንን ሙከራዊ ጥናት ለማድረግ ደግሞ ሰፊ ጊዜ ይጠይቃል፡፡ ስለዚህ ለጥናቱ የሚመረጠው ትምህርት ቤት ፈቃደኛ ሆኖ መገኘት አለበት፡፡ በዚሁ መሰረት ለዚህ ጥናት ፈቃደኛ ሆኖ የተገኘው የደምበጫ ከፍተኛ ትምህርት መሰናዶና አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት በአመቺ የናሙና ዘዴ ተመርጧል፡፡

### 3.1.2 የተማሪዎች አመራረጥ

ለዚህ ጥናት የተመረጡት በደምበጫ ከፍተኛ ትምህርት መሰናዶና አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ውስጥ የሚማሩ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ሲሆኑ የተመረጡበት ምክንያትም አጥኝው ለዚህ ጥናት መረጃ ለመሰብሰብ ባሰበበት ጊዜ በትምህርት ላይ ስለሚገኙ በቂ ጊዜ እንዲኖረው ስለሚያስችል ነው፡፡ ከዚህ ባሻገር 9ኛ ክፍል የ2ኛ ደረጃ ትምህርት

የሚጀምርበት በመሆኑ ችግሮች ካሉ ከስሩ ጀምሮ ለመለወጥ ጥረት በማድረግ ለቀጣዮቹ የክፍል ደረጃዎች አመቺ ሁኔታ ለመፍጠር የሚያስችል በመሆኑ ነው። የክፍል ደረጃው የተመረጠበትን ምክንያት እንዲህ ከገለጽን ቀጥሎ ደግሞ ተማሪዎች እንዴት እንደሚመረጡ እንመልከት። 9ኛ ክፍል ከሚማሩ ተማሪዎች መካከል የተመረጡት በተመሳሳይ ፈረቃ የሚማሩ ተማሪዎች ናቸው። የተመረጡትም በነሲብ የናሙና ዘዴ ነው። ምድቦቹ በውጤታቸው ዝቅተኛነትና ከፍተኛነት ተለያይተው እንዳልተመደቡ ከት/ቤቱ የመዘክር ክፍል ለማረጋገጥ ተችሏል። በመሆኑም በተለያየ ፈረቃ ከሚማሩ ምድቦች መካከል በጠዋት ፈረቃ የሚማሩት ከ$9^{25}$ — $9^{31}$ ክፍል ድረስ የተመደቡት በጥናቱ ታቅፈዋል። ከነዚህ ክፍሎች መካከል $9^{31}$ የዳሰሳ ጥናቱ (Pilot Study) የተካሄደበት በመሆኑ ከእጣው ውጭ ተደረጎ የተቀሩት በእጣው ውስጥ እንዲካተቱ ተደረገ። ከዚያም በእጣ የናሙና ዘዴ $9^{25}$ እና $9^{29}$ ምድቦች ተመረጡ። ከነዚህ ሁለት ምድቦች መካከልም በቁጥጥር ሁኔታ (controlled condition) እና በተጠኝነት ሁኔታ (experimental condition) የሚጠኑትን ለመለየት እጣ እንዲወጣ ተደረገ። በዚህም መሰረት በቁጥጥር ሁኔታ $9^{25}$ እንዲሁም በተጠኝነት ሁኔታ $9^{29}$ ተመረጡ። በመሆኑም አጥኝው በተጠኝነት የተመረጠውን ምድብ $9^{29}$ን ይዞ በፈጠራዊ ዘዴ አማካይነት አስር ክፍለ ጊዜ ያስተማረ ሲሆን ለጥናቱ ተባባሪ የሆኑት መምህርት ደግሞ በቁጥጥር የተያዙትን የ$9^{25}$ ክፍል ተማሪዎች በመያዝ በተለመደው ወይም በነባሩ ዘዴ እንዲያስተምሩ ተደረገ።

## 3.2 የግጥሞች አመራረጥ፣ የፈተናዎችና የመልመጃዎች አዘገጃጀት

### 3.2.1 የግጥሞች አመራረጥ

ይህ ጥናት ይዞት የተነሳው ዋነኛ አላማ ግጥም የአማርኛ ቋንቋ አንብቦ መረዳትና ጽህፈት ክሂሎችን ለማስተማር ያለውን ሚና በሙከራ ማረጋገጥ የሚለው ነው። ይህንን ሙከራ ለማካሄድም በዋናነት ግጥሞችን መምረጥ ያስፈልጋል። ስለሆነም ፈተናዎችንና መልመጃዎችን ለማዘጋጀት የሚሆኑ ስድስት ግጥሞች ተመረጡ። የተመረጡትን ግጥሞችም በምዕራፍ ሁለት ከቀረቡት የመምረጫ መስፈርቶች አኳያ ለመፈተሽ ጥረት ተደርጓል። የተመረጡት ግጥሞችም ‹‹ስርጾ ያልገባ እውቀት›› (ማን ይሆን የበላ፣ 1989) ከአያልነህ ሙላት፣ ‹‹ለካስ›› እና ‹‹መምህር ሊቁ›› (እናትና ልጅ፣ 1996) ከውዳላት ገዳሙ፣ ‹‹ከዛፍ የተቀሰመ ዜማ›› (ኗሪ አልባ ጎጆዎች፣ 1995) ከበዕውቀቱ ስዩም፣

‹‹ዘላለማዊ ነሽ›› (እውቀትን ፍለጋ፣ 2004) ከጌትነት እንየው፣ ‹‹በዩ. ተረት ንገሪኝ›› (እውነት ማለት የኔ ልጅ፣ 2004) ከበድሉ ዋቅጅራ ናቸው። ከዚያም እነዚህን ግጥሞች በዳሰሳ ጥናቱ ለተሳተፉት ተማሪዎች በመስጠት ከስድስቱ ውስጥ አራቱን እንዲመርጡ ተደረገ። በዚህም መሰረት በርካታ ተማሪዎች ‹‹ሰርጾ ያልገባ እውቀት››፣ ‹‹ለካስ››፣‹‹ከዛፍ የተቀሰመ ዜማ›› እና ‹‹ዘላለማዊ ነሽ›› የሚሉትን ግጥሞች መረጡ። ይህን የተማሪዎች ምርጫ በመያዝም በት/ቤቱ ውስጥ የአማርኛ መምህር ለሆኑ መምህራን ግጥሞችን አንብበው አስተያየት እንዲሰጡባቸው አደረግሁ። በዚሁ መሰረት ተማሪዎቹ የመረጧቸውን ግጥሞች መምህራንም መረጡ። የመረጡበትን ምክንያት ሲያስረዱም ግጥሞቹ የቋንቋ አጠቃቀማቸው ለተማሪዎች ደረጃ የሚመጥን ነው፣ ሳቢና ማራኪ ናቸው፣ የሚያስተላልፉት መልዕክትም ጥሩ ነው ብለዋል። በመጨረሻም ግጥሞቹ በአማካሪዬ ዘንድ ተቀባይነት ካገኙ በኋላ በጥናቱ እንዲካተቱ ተደርጓል።

### 3.2.2 የመልመጃዎችና የፈተናዎች አዘገጃጀት

ከላይ በቀረበው መልኩ ግጥሞች ከተመረጡ በኋላ ከግጥሞቹ ውስጥ ቋንቋን ለማስተማር የሚያስችሉ መልመጃዎችና ፈተናዎች ተዘጋጅተዋል። በዚህ መሰረትም ‹‹ለካስ›› እና ‹‹ዘላለማዊ ነሽ›› የሚሉት ግጥሞች ለቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናዎች የሚሆኑ ጥያቄዎችን ለማውጣት ያገለገሉ ሲሆን ‹‹ከዛፍ የተቀሰመ ዜማ›› እና ‹‹ሰርጾ ያልገባ እውቀት›› የሚሉት ደግሞ በክፍል ውስጥ ለተደረገው ልምምድ ያገለገሉ መልመጃዎችን ለማዘጋጀት ጠቅመዋል።

ከግጥሞቹ የወጡትን መልመጃዎችና ፈተናዎች በዳሰሳ ጥናቱ ከተሳተፉት ተማሪዎች አስተያየት በመነሳት ለማስተካከል ጥረት ተደርጓል። ከዚህ ባሻገር መልመጃዎችና ፈተናዎች ለጥናቱ ከመቅረባቸው በፊት በቋንቋ መምህራን እንዲገመገሙ ተደርጓል። በዚህ ግምገማ ላይም በተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች ሲያስተምሩ የነበሩና አሁን ‹‹TeAm›› በመማር ላይ የሚገኙ ተማሪዎች ተሳትፈዋል። እንደ Davies (1988: 5) እና ተስፋዬ፣ 1981፡ 121) ገለጻ ፈተናዎች ሲዘጋጁ ተማሪዎች ከተማሩት ሊሆን ይገባል። በዚህ መሰረትም ፈተናዎቹ ተማሪዎች ከተማሩት በመነሳት ተዘጋጅተዋል። በመጨረሻም የአማካሪዬን ይሁንታ ስላገኙ ለጥናቱ በመረጃ መሰብሰቢያነት አገልግለዋል።

### 3.3 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

ለዚህ ጥናት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ሁለት መሳሪያዎች በዋናነት አገልግሎት ላይ ውለዋል፡፡ እነዚህም ለተተኳሪ ቡድኖች ቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተና መስጠትና ውጤቶችን መመዝገብ፣ እንዲሁም በተጠኝነት የተያዙት የ9[29] ተማሪዎች በአዲሱ ዘዴ ከተማሩ በኋላ ያላቸውን አስተያየት ለመረዳት የጽሑፍ መጠይቅ ማስሞላትና መመዝገብ ናቸው፡፡ ከዚህ ባሻገር በትምህርቱ ሂደት ተማሪዎች ያላቸውን አስተያየትም ኢ መደበኛ በሆነ መልኩ በቃለ መጠይቅ ለመሰብሰብ ተሞክሯል፡፡

#### 3.3.1 የፈተና አሰጣጥ

በተጠኝነት ሁኔታ የተያዙት የ9[29] ክፍል ተማሪዎች ለጥናቱ መነሻ የሚሆን የቅድመ ትምህርት ፈተና እንደሚወስዱ በአጥኝው በኩል በትውውቁ ጊዜ ተነገራቸው፡፡ በጥብቅነት ሁኔታ የተመረጡ የ9[25] ምድቦች ደግሞ በአስተማሪያቸው በኩል እንዲነገራቸው ተደረገ፡፡ ከዚያም ተማሪዎቹ ፈቃደኝነታቸውን ካሳዩ በኋላ ፈተናውን እንዲፈተኑ ተደርጓል፡፡ ትምህርቱን ከተከታተሉ በኋላም የድህረ ትምህርት ፈተና ለሁለቱም ቡድኖች ተሰጧል፡፡ ፈተናዎቹም በተመሳሳይ ሰዓት እንዲሰጡ ነው የተደረገው፡፡ ፈተናዎቹንም እንዲፈትኑ የተደረጉት በት/ቤቱ ውስጥ በአፈታተናቸው የተመሰገኑ መምህራን ናቸው፡፡ አጥኚውም በተወሰነ ደቂቃ ልዩነት እየተዘዋወረ ቁጥጥርና ክትትል አድርጓል፡፡

#### 3.3.2 የፈተና አስተራረም

በጥናቱ ለታቀፉት ሁለቱም ቡድኖች በተሰጡት የቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናዎች መካከል ሰፊ ልዩነት መኖርና አለመኖሩን ለማረጋገጥ ፈተናዎቹን በትክክል ማረም እንዲሁም ውጤቶቹን መገምገምና ማነጻጸር አስፈላጊ ነው፡፡ ስለሆነም በፈተናው ውስጥ በተካተቱት የጻፍ ጥያቄዎች ላይ ሊከሰት የሚችለውን የህሊናዊነት (subjectivity) ችግር ለመቅረፍ ሶስት የ‹‹TeAm›› ተማሪዎች በማረም እንዲሳተፉ ተደርጓል፡፡ እነዚህን ድርሰት ነክ ጥያቄዎች ለማረም ያስችላቸው ዘንድም የነ Atkins (1996, 14) ድርሰት ለማረም የሚያስችል የነጥብ አሰጣጥ መግለጫ ተሰጧቸዋል፡፡ እያንዳንዱ ተማሪ ያገኘው ውጤት የታወቀውም አራሚዎቹ የሰጡት ውጤት ተደምሮ ለሶስት ሲካፈል ነው፡፡ (አባሪ ስምንት ከገጽ 111 — 112 ይመልከቱ)

### 3.3.3 የጽሑፍ መጠይቅ

በተጠኝነት ሁኔታ የተያዙት የ$9^{29}$ ክፍል ተማሪዎች የቀረበላቸውን የቋንቋ ትምህርትና የማስተማሪያ ዘዴ መውደድና አለመውደዳቸውን ለማረጋገጥ መሞከር የዚህ ጥናት አንደኛው አላማ ነው። ስለሆነም ይህንን ሁኔታ ለማረጋገጥ በተጠኝነት ምድብ ውስጥ ለተያዙ ተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ ቀርቦ እንዲሞሉ ተደርጓል። መጠይቁ ሶስት ክፍሎች ያሉት ሲሆን የመጀመሪያው ክፍል የተማሪዎችን ዳራ ለማወቅ የቀረቡ ጥያቄዎችን የያዘ ነው። ሁለተኛው ክፍል ደግሞ 14 ጥያቄዎችን የያዘ ሲሆን የጥያቄዎቹ ትኩረትም ተማሪዎቹ ከስነ ጽሑፍ ስራዎች ጋር ስለነበራቸው ቅርበት፣ ግጥሞችን አንብበው በሚወያዩበት ወቅት ስላጋጠማቸው ነገር፣ ከተማሩበት ዘዴ ስላገኙት ጠቀሜታ፣ ግጥም ለቋንቋ ትምህርት ስላለው አስተዋጽኦ እንዲሁም ስለመምህሩና ተማሪው ተግባር ነበር። ከነዚህ 14 ጥያቄዎች መካከል አስራ አንዱ አዎንታዊ ሲሆኑ ሶስቱ ደግሞ አሉታዊ ይዘት አላቸው። እነዚህ ጥያቄዎች በሊከርት የመመዘኛ እስኬል (likert rating scale) አማካይነት የተዘጋጁ ናቸው። ተማሪዎቹ መልስ ሲሰጡም በጣም እስማማለሁ፣ እስማማለሁ፣ አልስማማም፣ በጣም አልስማማም በሚል እንዲሆን ተደርጓል። ሶስተኛው ክፍል ደግሞ ተማሪዎች ሀሳባቸውን በነጻነት እንዲሰጡ ለማድረግ ታስቦ የቀረቡ ጥያቄዎችን የያዘ ነው። ይህ የጽሑፍ መጠይቅም በ$9^{29}$ ክፍል ለሚገኙ 58 ተማሪዎች ቀርቦ መረጃዎች ተሰብስበዋል።

## 3.4 የመረጃ አተናተን ስልት

በቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናዎችና በጽሑፍ መጠይቅ ከተሰበሰቡ መረጃዎች በመነሳት በምዕራፍ አራት ላይ ትንታኔ ተሰጧል። በቅድመ ትምህርት እና በድህረ ትምህርት ፈተናው ጊዜ ፈተናውን የተፈተኑት የ$9^{25}$ ተማሪዎች ቁጥር 58 ሲሆን በተመሳሳይ የ$9^{29}$ ክፍል ተማሪዎች ቁጥርም 58 ነበር። በድህረ ትምህርት ፈተናው ወቅት እንዲፈተኑ የተደረጉት የቅድመ ትምህርት ፈተናውን የተፈተኑና ትምህርቱን የተከታተሉት ናቸው። የጽሑፍ መጠይቁን እንዲሞሉ የተደረጉት ደግሞ በተጠኝነት ሁኔታ የተያዙት ተማሪዎች ናቸው። በአጠቃላይ በቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተና የተገኙ ውጤቶች በስታትስቲካዊ ዘዴ ተተንትነው የቀረቡ ሲሆን ከጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ደግሞ ሰንጠረዥና ገለጻ ስልትን በመጠቀም ተተንትነው ቀርበዋል።

# ምዕራፍ አራት

# 4. የማስተማር ሂደትና የመረጃዎች ትንተና

## 4.1. የማስተማር ሂደት

ግጥም የአማርኛ ቋንቋ አንብቦ መረዳትና ጽሕፈት ክሂልን ለማስተማር ያለውን ሚና ለማረጋገጥ በተካሄደው ጥናት ውስጥ ከተተገበሩ ተግባራት መካከል አንዱ በክፍል ውስጥ ተገኝቶ ማስተማር ነበር፡፡ ይህንን ተግባር ለማከናዎንም ከመጋቢት 4/2005 እስከ ሚያዚያ 4/2005 ዓ.ም. ድረስ ‹‹የ9[29]›› ክፍል ተማሪዎችን ለተከታታይ አራት ሳምንታት አስር ክፍለ ጊዜያትን ለማስተማር ሙከራ ተደርጓል፡፡

ይህ የማስተማር ክንውን የተካሄደበት አብይ አላማም ከተመረጡት ሁለት ግጥሞች የተዘጋጁትን መልመጃዎች በማስተማር ግጥም ለአማርኛ ቋንቋ አንብቦ መረዳትና ጽሕፈት ክሂል እድገት ያለውን ሚና ለማረጋገጥ ነው፡፡

በመቀጠል ለአራት ሳምንታት የተካሄደው የማስተማር ሂደት እንደሚከተለው ይቀርባል፡፡

ቀን፡- 04/07/05

ሰዓት፡- 2፡00

ክ/ጊዜ፡- 1ኛ

አንድ ጥናት ከመካሄዱ በፊት ጥናቱ የሚያካትታቸው ተጠኚዎች ስለጉዳዩ ማወቅና መስማማት ይኖርባቸዋል፡፡ በዚህ መሰረት ት/ቤቱ ፈቃደኛ መሆኑን ካረጋገጥሁና የማስተምራቸውን ተማሪዎች ከለየሁ በኋላ ተከታዩ ተግባር ያደረግሁት ለተማሪዎች ስለጥናቱ ምንነት፣ አላማ፣ አይነት፣ ሁኔታ…ወዘተ. ማብራሪያ መስጠት ነበር፡፡ የቀረበው ማብራሪያም የሚከተለውን ይመስላል፡፡

በዕለቱ መደበኛዋ መምህርት ለጥናቱ ወደተመረጡት ተማሪዎች ክፍል ይዘውኝ በመግባት ከተማሪዎቹ ጋር እንድተዋወቅ አደረጉ፡፡ ለቀጣዮቹ አራት ሳምንታትም ከእኔ ጋር ቆይታ እንደሚያደርጉ ነግረዋቸው ክፍሉን ለቀው ወጡ፡፡ መምህርቷ ክፍሉን ለቀው ከወጡ በኋላ ተከታዩን ማብራሪያ ለተማሪዎች አቀረብኩ፡፡

የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አላማ ተማሪዎች ሀሳባቸውን በንግግርም ሆነ በጽሑፍ በአግባቡ እንዲገልጹና እንዲያስተላልፉ መሆኑን ነገር ግን አብዛኛው ተማሪ ይህን ለማድረግ ሲቸገር እንደሚታይ አስረዳኋቸው፡፡ ስለዚህ ይህንን ችግር ለማስወገድ ግጥም የአማርኛ ቋንቋ አንብቦ መረዳትና ጽሕፈት ክሂልን ለማስተማር ያለውን ሚና ለማረጋገጥ አስቤ ይህን ሙከራዊ ጥናት ለማካሄድ እንደተነሳሁ ገለጽኩላቸው፡፡ በምንቆይባቸው ሳምንታት የምንከተለው የማስተማር ዘዴም ‹‹ፈጠራዊ ዘዴ›› እንደሚባል በመንገር ስለምንነቱ ሰፋ ያለ ማብራሪያ አቀረብኩላቸው፡፡ በቆይታችን ወቅትም ለትምህርቱ የሚያገለግሉ ጽሑፎችን፣ ወረቀቶችንና ሌሎች አስፈላጊ ግብአቶችን እኔ እንደማቀርብ ነገርኳቸው፡፡ ይህ ጥናት በሚገባ ከተከናወነ ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት እድገት የበኩሉን አስተዋጽኦ እንደሚያበረክትና እነሱም በትምህርቱ ሂደት ንቁ ተሳትፎ ቢያደርጉ አዳዲስ ትምህርቶችን ስለሚያገኙ ተጠቃሚዎች እንደሚሆኑ አስረዳኋቸው፡፡

ፈጠራዊ ቋንቋን የማስተማር ዘዴ ተማሪ- መራሽ በመሆኑ አብዛኛው ስራ በተማሪዎች በጋራ እንደሚከናወን፣ ይህ በመሆኑም በአንድ ተማሪ ላይ ጫና እንደማይፈጠር፣ የሁሉም ተማሪ ችሎታ የተለያየ ስለሚሆን እርስ በርስ እንዲረዳዱ፣ ውይይቶች ሲካሄዱም ከመጠን ያለፈ ጫጫታ እንዳይፈጠር ድምጻቸውን ቀነስ አድርገው እንዲወያዩ፣ በት/ቤቱ ተግባራዊ በሆነው የአንድ ለአምስት አደረጃጀት መሰረት የቡድን ስራዎችን እንዲሰሩ አሳሰብኳቸው፡፡ በመጨረሻም ለዚህ ጥናት ፈቃደኛ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ስጠይቃቸው ሁሉም ተማሪዎች ፈቃደኛ መሆናቸውን በአንድ ድምጽ አረጋገጡልኝ፡፡

በማስከተልም ለጥናቱ መነሻ የሚሆን የቅድመ ትምህርት ፈተና እንደምሰጣቸው ነገርኳቸው፡፡ የፈተናው ቀንም በ06/07/05 ዓ.ም. በሁለት ሰዓት መሆኑን ነገርኳቸው፡፡ ፈተናው 1፡30 ሊወስድ ስለሚችል ከ1ኛው እስከ 3ኛው ክ/ጊዜ ድረስ የተፈቀደልኝ መሆኑን አስረዳኋቸው፡፡ የመፈተኛ ወረቀትም ከእኔ እንደሚያገኙ ገለጽኩላቸው፡፡ በመጨረሻም በተጠቀሰው ቀንና ሰዓት እንዲገኙ በማሳሰብ ተማሪዎችን ተሰናብቼ ወጣሁ፡፡

ቀን፡- 06/07/05

ሰዓት፡- 2:00

ክ/ጊዜ፡- 1ኛ

በዚህ እለት አስቀድሜ ፈተናውን እንዲፈትኑልኝ የት/ቤቱን ሁለት መምህራን በመያዝ ወደ መማሪያ ክፍሎች አመራን፡፡ የተመረጡት መምህራን አንድ ወንድና አንድ ደግሞ ሴት ሲሆኑ በአፈታተናቸው የተመሰገኑ ናቸው፡፡ አንደኛው መምህር በቁጥጥር ሁኔታ የተያዙትን ተማሪዎች የፈተኑ ሲሆን መምህርቷ ደግሞ በተጠኚነት ሁኔታ የተያዙትን ተማሪዎች ፈተኑ፡፡ በመቀጠል ተማሪዎች በአንድ ወንበር ሁለት ሁለት ሆነው እንዲቀመጡ አደረግን፡፡ በፈተናውም ሁሉም ተማሪዎች ተገኝተው ነበር፡፡ ልክ 2:10 ሲል የፈተና ወረቀቱን ከነመልስ መስጫው ለሁሉም ተማሪዎች ማደል ጀመርን፡፡ ይህን እንደጨረስን 2:15 ሲል ፈተናውን መስራት እንዲጀምሩና የተሰጣቸው ሰዓት 1:30 መሆኑን ነገርናቸው፡፡ በፈተናው ወቅት ግልጽ አልሆነልንም ለሚሉ ተማሪዎች ማብራሪያ በመስጠት ችግሩን ለማስወገድ ጥረት ተደርጓል፡፡ ከዚህ ባለፈ ሁለቱም ፈታኞች ተማሪዎች እንዳይቀዳዱ ብርቱ ቁጥጥር ሲያደርጉ በምዘዋወርበት ወቅት ለማስተዋል ችያለሁ፡፡ 3:30 አካባቢ የተወሰኑ ተማሪዎች ፈተናውን እየጨረሱ መውጣት ጀመሩ፡፡ የቀራቸው ጊዜ አነስተኛ በመሆኑ ፈጠን ብለው እንዲያጠናቅቁ ለቀሩት ተማሪዎች መልዕክት አስተላለፍን፡፡ 3:45 ሲል አብዛኛው ተማሪ እያጠናቀቀ የወጣ ቢሆንም የተወሰኑ ተማሪዎች ባለመጨረሳቸው ተጨማሪ 10 ደቂቃ ሰጠናቸው፡፡ ልክ 3:55 ሲል ሁሉም ተማሪ ጨርሶ ወጣ፡፡ በዚህም የቅድመ ትምህርት ፈተናው ተጠናቀቀ፡፡ ከዚያም የፈተና ወረቀቶችን በመቁጠር ትክክለኛ መሆናቸውን አረጋገጥን፡፡ እኔም በፈታኝነት የተባበሩኝን ሁለት መምህራን በማመስገን ተለያየን፡፡

ቀን፡- 09/07/05

ሰዓት፡- 6:30

ክ/ጊዜ፡- 1ኛ

ክፍለ ጊዜው ከመድረሱ በፊት ነበር የመጀመሪያውን የሙከራ ትምህርት ለመጀመር ወደ ክፍል ያመራሁት፤ ‹‹ሰርጾ ያልገባ እውቀት›› የሚል ርዕስ ያለውን ግጥም 58 ቅጅዎች

በመያዝ፡፡ ጊዜው ደርሶ ክፍል ውስጥ የነበሩት መምህር ሲወጡ እኔ ገባሁ፡፡ እንደገባሁም ስም ስጠራ 56 ተማሪዎችን አገኘሁ፡፡ በማስከተልም የያዝኳቸውን የግጥም ቅጅዎች ለተማሪዎች በነፍስ ወከፍ ለሁሉም ሰጠሁ፡፡

በመቀጠል ትምህርቱን ተማሪዎች በንቃት ይከታተሉ ዘንድ ስለ ጸሐፊ ተውኔት አያልነህ ሙላት የሚያውቁትን እንዲነግሩኝ ጠየቋቸው፡፡ በዚህ ጊዜ ‹‹አያልነህ ሙላትን የሚያውቅ አለ?›› ብዬ ጠየኩ፡፡ ሆኖም የአንድም ተማሪ እጅ አልታየኝም፡፡ በመሆኑም አያልነህ ሙላት ማን እንደሆነና ምን ምን ስራዎችን እንደሰራ የሚያውቅ ተማሪ እንደሌለ ተረዳሁ፡ ፡ ይህንን ከተረዳሁ በኋላ ስለ ደራሲው ማንነትና ስለ ስራዎቹ አጭር ገለጻ አቀረብኩላቸው፡፡ አያልነህ ሙላት ተወልዶ ያደገው ጎጃም ውስጥ እንደሆነ፣ የከፍተኛ ትምህርቱንም እስከ ራሺያ ድረስ ሄዶ እንደተከታተለ፣ በተለይም በተውኔት ጸሐፊነቱ ይበልጥ እንደሚታወቅ አስረዳኋቸው፡፡ ከስራቸው ስራዎች መካከልም ‹‹ማን ይሆን የበላ?››፣ ‹‹ከድጡ ወደ ማጡ››፣ ‹‹አይ አንቺ አገር››፣ ‹‹ጥገት ላም›› የሚባሉ የግጥም መጻሕፍት፤ ‹‹ሾተላይ››፣ ‹‹የደም ጋብቻ››፣ ‹‹ደህ አደግ›› የሚባሉ የተውኔት ስራዎች እንደሚገኙበት ገለጽኩላቸው፡፡ ይህ አሁን የሰጠኋቸው ‹‹ስርጸ ያልገባ እውቀት›› የሚለው ግጥምም ‹‹ማን ይሆን የበላ?›› ከሚለው የግጥም መጽሐፉ የተወሰደ መሆኑን ነገርኳቸው፡፡ የሱን ስራዎች የማግኘት እድሉ ካጋጠማቸውም እንዲያነቧቸው ጋበዝኳቸው፡ ፡

ከላይ የተደረገው ገለጻ አላማ ተማሪዎች እንዲነቃቁ ለማድረግ ሲባል ነበር (Lazar, 1993፡ 84)፡፡ ተማሪዎች እንዲህ ከተነቃቁ በኋላ የተሰጣቸውን ግጥም በለሆሳስ እንዲያነቡ አዘዝኩ፡፡ በዚህ መሀል የቃላትን አውዳዊ ፍቺ እንዲፈልጉ በማሰብ ተከታዮቹን ቃላት በጥቁር ሰሌዳው ላይ ጻፍኩላቸው፡፡

| | |
|---|---|
| ሀ. ስርጸ | ሠ. ብልጭልጭ |
| ለ. ጥበብ | ረ. ዶቃ |
| ሐ. ህሊና | ሰ. ባህል |
| መ. ጠንብዞ | ሸ. አሻራ |

ከተወሰኑ ደቂቃዎች በኋላ አንብበው በመጨረሳቸው ቀና ቀና ብለው ተመለከትኳቸው። አንብበው መጨረሳቸውን ካረጋገጥኩ በኋላ በአንድ ለአምስት አደረጃጀታቸው ሆነው በቃላቱ አውዳዊ ፍቺ ላይ ከመወያየታቸው በፊት ‹‹አውዳዊ ፍቺ›› ምን ማለት እንደሆነ ገለጻ አደረግሁላቸው። በዚህ መሰረትም አውዳዊ ፍቺ ማለት ቃላት በዐ.ነገር ውስጥ በገቡበት ሁኔታ የሚኖራቸው ወይም የሚይዙት ትርጉም እንደሆነ ነገርኳቸው። ይህን እያስረዳሁ እያለ ክፍለ ጊዜው ማለቁን የሚጠቁመው ደወል በመደወሉ ክፍሉን ለቅቄ ወጣሁ።

ቀን፡- 11/07/05

ሰዓት፡- 10፡45

ክ/ጊዜ፡- 7ኛ

በእለቱ ስም ስጠራ ሁሉም ተማሪዎች ተገኝተው ነበር። ተማሪዎቹ ክፍለ ጊዜው አማርኛ መሆኑን ስላወቁ የተሰጣቸውን ምንባብ ይዘው ሲጠባበቁ ነበር። እኔም ባለፈው ክፍለ ጊዜ ካቆምንበት እንደምንቀጥል በመግለጽ በጥቁር ሰሌዳው ላይ ጽፌላቸው የነበሩትን ቃላት በድጋሜ ጻፍኩላቸው። ከዚያም ለነዚህ ቃላት አውዳዊ ፍቻቸውን እንዲፈልጉላቸው አዘዝኳቸው። ይህንንም በአንድ ለአምስት አደረጃጀታቸው ሆነው እንዲሰሩ ነገርኳቸው። ተማሪዎቹም በየአደረጃጀታቸው ሆነው ሞቅ ያለ ውይይት ማካሄድ ጀመሩ። እኔም ሁሉንም ቡድን እየተዟዟርሁ እከታተል ነበር። ሁሉም ቡድን የቃላቱን አውዳዊ ፍቺ በሚገባ ሲሰራ ማስተዋልም ችያለሁ። በዚህ መሀል አንድ ተማሪ ‹‹ቮልቮ›› የሚል ቃል ግጥሙ ውስጥ አለ፤ ምን ማለት ነው ሲል ጠየቀኝ። እኔም ምን ማለት እንደሆነ ሌሎች ቡድኖች እንዲሞክሩ እድሉን ሰጠኋቸው። አንድ ተማሪ እጁን አውጥቶ ‹‹የመኪና ስም ነው›› ሲል መለሰ። የተማሪው መልስ ትክክለኛ መሆኑን እኔም አረጋገጥኩላቸው። ሌላ ተማሪም እንደዚሁ ‹‹አስፕሪን›› ምን ማለት ነው ሲል አያይዞ ጠየቀ። እኔም እንዲሞክሩት እድሉን ለተማሪዎች ሰጠሁ። እጁን ያወጣ ተማሪ ባለማየቱ የሚዋጥ የመድኃኒት አይነት መሆኑን አስረዳኋቸው። በመቀጠልም እነዚህን ቃላት ያልሰጠኋቸው የእንግሊዝኛ ቋንቋ ቃላት በመሆናቸው መሆኑን አስረዳቻው።

በዚህ ክፍለ ጊዜ መታዘብ እንደቻልኩት ተማሪዎች ግጥሙን አንብበው በቃላቱ አውዳዊ ፍቺ ላይ በቡድን መወያየት ያለባቸው በዚያው ክፍለ ጊዜ ነው። ምክንያቱም በአንደኛው

ክፍለ ጊዜ ቃላቱ ተሰጧቸው በቀጣዩ ክፍለ ጊዜ የቃላቱን አውዳዊ ፍቺ ስሩ ቢባሉ በአውዱ መሰረት ለመስራት ሊቸገሩ ይችላሉ፡፡ በመሆኑም ይህ በሰዓት እጥረት ምክንያት የተፈጠረው ችግር በድጋሜ እንዳይከሰት በቀጣዮቹ ክፍለ ጊዜያት ብርቱ ጥንቃቄ አድርጌያለሁ፡፡

በመጨረሻም ‹‹ስራ›› በሚል ርዕስ በግላቸው ከ50 ባልበለጡ ቃላት ድርሰት ጽፈው እንዲመጡ፤ የሚችል ካለም ግጥም ጽፎ እንዲያመጣ አዘዝኩ፡፡ ክፍለ ጊዜው በመጠናቀቁ ተማሪዎችን ተሰናብቼ ክፍሉን ለቅቄ ወጣሁ፡፡

ቀን፡- 14/07/05

ሰዓት፡- 2፡00

ክ/ጊዜ፡- 1ኛ

ወደክፍል ገብቼ ስም ስጠራ 55 ተማሪዎችን አገኘሁ፡፡ ቀጥዬም ባለፈው ክፍለ ጊዜ የሰጠኋቸውን የቤት ስራ ሰርተው መምጣታቸውን ጠየቅሁ፡፡ ሁሉም ተማሪዎች ሞክረው መምጣታቸውን ተናገሩ፡፡ እኔም ተማሪዎችን በማመስገን በቤት ስራ መልክ የጻፉትን ድርሰት መሰብሰብ ጀመርኩ፡፡ ሰብስቤ ከጨረስኩ በኋላ የተሰጡ ቃላትንና ሀረጋትን መነሻ በማድረግ ዐ.ነገር መስራትን ለማለማመድ በማሰብ ጥያቄዎችን ጥቁር ሰሌዳው ላይ ጻፍኩላቸው፡፡ ከቀረቡት ጥያቄዎች መካከልም የሚከተሉት ይገኙበታል፡፡

- አሻራ/ አይደለም
- ውሃ/ ነው
- ዓመት/ እየበረረ
- ባህል/ እየቀረ

በመቀጠልም ዐ.ነገሮችን በየአደረጃጀታቸው ሆነው እንዲሰሩ አዘዝኳቸው፡፡ ተማሪዎቹም ሞቅ ባለ የቡድን ውይይት መስራት ጀመሩ፡፡ እኔም እየተዘዋወርኩ መከታተሌን ቀጠልኩ፡፡ ከዚያም በየቡድኑ የተሰሩትን የተወሰኑ ዐ.ነገሮች ለክፍሉ በሙሉ እንዲነበቡ አደረግሁ፤ ትምህርቱም ወደ ጠቅላላ ውይይት ተለወጠ፡፡ በአብዛኛው ጥያቄዎች ላይ የተሰጡ መልሶች ትክክልና የጎላ ልዩነት ያልነበራቸው ነበሩ፡፡ ነገር ግን ‹‹አሻራ/ አይደለም›› በሚለው ጥያቄ ላይ የተለያዩ ምላሾች ከተለያዩ ቡድኖች ተሰጡ፡፡ ከነዚህ መካከል ‹‹አሻራ ተመሳሳይ

አይደለም››፣ ‹‹አሻራህ አይደለም››፣ ‹‹የሁሉም ሰው አሻራ ተመሳሳይ አይደለም››፣ ‹‹አሻራ መገለጫ አይደለም››፣ ‹‹አሻራ አለመስጠት ተገቢ አይደለም›› የሚሉት ይገኙበታል፡፡ ከነዚህ መካከል ‹‹የሁሉም ሰው አሻራ ተመሳሳይ አይደለም›› የሚለው ዐ.ነገር የተሻለ መሆኑን እያስረዳኋቸው እያለ ደወሉ በመደወሉ ክፍሉን ለቅቄ ወጣሁ፡፡

ቀን፡- 16/07/05

ሰዓት፡- 4:55

ክ/ጊዜ፡- 5ኛ

በዕለቱ ለጥቂት ቀናት ሲሰጥ ስለነበረው ትምህርት የተማሪዎችን አስተያየት ለመስማት ስለፈለግሁ ወደ ክፍል የሄድኩት ከአማርኛ ክፍለ ጊዜ በፊት የነበሩትን የሒሳብ መምህር በማስፈቀድ ነበር፡፡ በወቅቱም 57 ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ተገኝተው ነበር፡፡

ስለትምህርቱ አሰጣጥ ያላቸውን አስተያየት እንዲሰጡኝ ጠየቋቸው፡፡ በርከት ያሉ ተማሪዎችም አስተያየታቸውን ሰጥተውኛል፡፡ ከተሰጡት አስተያየቶች መካከልም፤ ትምህርቱ አያሰለችም፣ መልመጃዎችን እየተወያየን ስለምንሰራ አይከብደንም፣ እርስ በርስ ስለምንወያይ አንዱ ከሌላው ትምህርት ያገኛል፣ በስራችን ላይ አንተ ጣልቃ ስለማትገባ በራሳችን አቅም የመስራት ድፍረትን አግኝተናል...ወዘተ. የሚሉት ይገኙበታል፡፡ ከዚህ ባሻገር በማስተማሪያ ስነ ዘዴው ላይ ያዩትን ደካማ ጎን እንዲነግሩኝ እድል ሰጠኋቸው፡፡ አብዛኛው ተማሪ የሰጠው አስተያየት ‹‹ስራው በጋራ ውይይት የሚካሄድ በመሆኑ ጫጫታ እንዲከሰት ያደርጋል፤ ይህም ይረብሻል›› የሚል ነበር፡፡ የሰጡት አስተያየት ትክክል እንደሆነ በመግለጽ ድምጽን ዝቅ አድርጎ በመወያየት ግን ችግሩን ማስወገድ እንደሚቻል አስረዳኋቸው፡፡ የቀረ የሚሉት አስተያየት ካላቸው እንዲነግሩኝ እድል ሰጠኋቸው፡፡ ሆኖም የቀረ አስተያየት እንደሌላቸው በዝምታቸው ገለጹልኝ፡፡ በዚሁ የሒሳብ ክፍለ ጊዜ በመጠናቀቁ ወደ መደበኛው የአማርኛ ክፍለ ጊዜ ገባን፡፡

ከአስተያየቱ በኋላ ያመራነው ባለፈው ክፍለ ጊዜ ሰርተው ያመጡትን ድርሰት ወደ መመለስ ነበር፡፡ ከዚያም የሁሉም ተማሪዎች ሙከራ ጥሩ እንደነበር በመንገር ለናሙናነት ይሆናሉ ያልኳቸውን ስራዎች ለተማሪዎች አነበብኩላቸው፡፡

ከዚህ በመቀጠል ያልተሟሉ ዐ.ነገሮችን በተሰጡ ቃላት ዘሮች ማሟላት የሚለውን መልመጃ እንዲሰሩ በማሰብ ጥያቄዎችን በጥቁር ሰሌዳው ላይ ጻፍኩላቸው፡፡ የበለጠ ግልጽ እንዲሆንላቸውም ተከታዩን ምሳሌ ሰጠኋቸው፡፡

ምሳሌ፡- (ሊቅ)     በሀገራችን በርካታ __________አሉ፡፡ (የተሰጠ ጥያቄ)

በሀገራችን በርካታ ሊቃውንት አሉ፡፡ (የተሰጠ መልስ)

ከዚያም እንደተለመደው በተደራጁበት ቡድን ሆነው ጥያቄዎቹን እየተወያዩ እንዲሰሩ አዘዝኳቸው፡፡ ሞቅ ባለ ውይይትም ተማሪዎች ስራቸውን ጀመሩ፡፡ እኔም እየተዟዟርኩ የየቡድኖችን ስራ መከታተል ቀጠልኩ፡፡ ሁሉም ቡድኖች በጥሩ መልኩ የቀረቡትን ጥያቄዎች ሲሰሩም መታዘብ ችያለሁ፡፡ ከዚያም ምናልባት ያልተስማሙበት ጉዳይ ካለ ብዬ ጥያቄ አነሳሁ፡፡ ነገር ግን ያልተስማሙበት ጉዳይ አለመኖሩን ነገሩኝ፡፡

ከዚህ በማስከተል ‹‹ሰርጾ ያልገባ እውቀት›› በሚል ርዕስ የቀረበውን ግጥም መሰረት አድርገው የተዘጋጁት መልመጃዎች መጠናቀቃቸውን ተናግሬ መልመጃዎችን አስመልክቶ ጥያቄ ካላቸው እንዲያነሱ እድል ሰጠኋቸው፡፡ ሆኖም ምንም ጥያቄ እንደሌላቸው ነገሩኝ፡፡ በመሆኑም በሚቀጥለው ክፍለ ጊዜ ‹‹ከዛፍ የተቀሰመ ዜማ›› የሚል ርዕስ ያለውን ግጥም እንደምንጀምር በመግለጽ ስለ በዕውቀቱ ስዩም ማንነትና ስራዎቹ አንብበው ወይም ጠይቀው እንዲመጡ ትእዛዝ አስተላለፍኩ፡፡ ከዚያም ክፍለ ጊዜው በመጠናቀቁ ተማሪዎችን ተሰናብቼ ወጣሁ፡፡

ቀን፡- 20/07/05

ሰዓት፡- 10፡05

ክ/ጊዜ፡- 6ኛ

በእለቱ የአማርኛ ክፍለ ጊዜ ባለመኖሩ ወደ ክፍል የሄድሁት የእንግሊዝኛ መምህሩን በማስፈቀድ በእንግሊዝኛ ክፍለ ጊዜ ነው፡፡ ክፍል ገብቼ ስም ስጠራ 55 ተማሪዎች ክፍል ውስጥ ተገኝተው ነበር፡፡ ትምህርቱን ከመጀመራችን በፊትም በባለፈው ክፍል ጊዜ ስለ በዕውቀቱ ስዩም አንብበው ወይም ጠይቀው እንዲመጡ ነግሬያቸው እንደነበር በማስታወስ ጥያቄውን በድጋሚ አነሳሁላቸው፡፡ በዚህ ጊዜ በርከት ያሉ ተማሪዎች እጃቸውን አወጡ፡፡

ለአንደኛው ተማሪ እድሉን ሰጠሁት፡፡ እሱም ‹‹ጦር አውርድ›› የሚል ድርሰት ጽፏል ሲል መለሰ፡፡ እኔም ሙከራውን በማድነቅና ትክክል እንደሆነ በመግለጽ ለሌሎች ተማሪዎችም እድሉን ሰጠሁ፡፡ ሌላኛዋ ተማሪ ደግሞ በዕውቀቱ ስዩም ጎጃም እንደተወለደ፣ ከስራዎቹ መካከልም ‹‹ሳገባነው›› እና ‹‹ጦር አውርድ› የሚሉትን እንደምታውቅ ተናገረች፡፡ ሌሎች ተማሪዎችም ተመሳሳይ የሆኑ መልሶችን ሰጡ፡፡ እኔም ተማሪዎቹ ያደረጉትን ተሳትፎና ሙከራ በማድነቅ ስለ በዕውቀቱ ስዩም ተከታዩን ‹‹እንቅልፍና እድሜ›› ከሚለው መጽሐፉ ጀርባ ያገኘሁትን አነበብኩላቸው፡፡

> በዕውቀቱ ስዩም በጎጃም፣ የፍቅር እስከ መቃብሩ በዛብህ በስለት በተገኘበት ማንኩሳ በ1972 ዓ.ም. ተወለደ፡፡ ደብረ ማርቆስም ተምሮ በ1993 ዓ.ም. ከአ.አ.ዩ. የመጀመሪያ ዲግሪውን በስነ አእምሮ ጥናት ተቀበለ፡፡ በዚህ ሙያም ለተወሰነ ጊዜ ካገለገለ በኋላ በ1995 በጽሑፍ ስራ መተዳደር ጀመረ፡፡
>
> በኔሽን፣ አዲስ አድማስና መዝናኛ ጋዜጦች ጽሑፎቹን ከማቅረብ ባሻገር ኗሪ አልባ ጎጆዎች (1995)፣ በራሪ ቅጠሎች (1996) እና የእሳት ዳር ሀሳቦች (2000) የተባሉ መጻሕፍትን በግል፣ ክንፋም ህልሞች (1996) እና ወንዞች እስኪሞሉ (1998) የተባሉ መጻሕፍትን ደግሞ በጋርዮሽ አበርክቷል፡፡
>
> በአሁኑ ጊዜም የአጫጭር ታሪክ ስብስቦቹን፣ በስነ ጽሑፍ ባህሪ ላይ ያተኩሩ መጣጥፎቹንና አዳዲስ የልቦለድ ድርሰቶቹን ለህትመት በማሰናዳት ላይ ይገኛል፡፡
>
> ምንጭ፡- (በዕውቀቱ ስዩም፣ 1998)

ከዚህ ባሻገር በዕውቀቱ ‹‹ስብስብ ግጥሞች›› የሚል የግጥም መጻሕፍ፣ ‹‹እንቅልፍና እድሜ››፣ ‹‹መግባትና መውጣት›› የሚሉ ልቦለዶችን ለህትመት እንዳበቃ ሰፋ ያለ ማብራሪያ አቀረብኩላቸው፡፡ ከዚያም ዛሬ የምንጀምረው ‹‹ከዛፍ የተቀሰመ ዜማ›› የሚለው ግጥም ‹‹ኗሪ አልባ ጎጆዎች›› ከሚለው መጽሐፉ እንደተወሰደ በመንገር የያዝኳቸውን ቅጅዎች ለተማሪዎች በነፍስ ወከፍ ሰጠሁ፡፡ በመቀጠልም የተሰጣቸውን ግጥም በለሆሳስ እንዲያነቡ ነገርኳቸው፡፡ ከተወሰነ ደቂቃ በኋላ አብዛኛው ተማሪ ንባቡን ጨርሶ ቀና ቀና ማለት ጀመረ፡፡ ሁሉም ተማሪ አንብቦ መጨረሱን እንዳረጋገጥኩ ወደሚቀጥለው ትምህርት ልሸጋገር ስል በተማሪዎች ላይ የድካምና የመሰላቸት ስሜት ስላስተዋልኩ በቀጣዩ ክፍለ ጊዜ ከምንባቡ የወጡ ቃላትን አውዳዊ ፍቺ እንደምንሰራ በመንገር የእለቱን ትምህርት አጠናቅቄ ወጣሁ፡፡

ቀን፡- 24/07/05

ሰዓት፡- 2፡00

ክ/ጊዜ፡-1ኛ

እንደተለመደው ወደ ክፍል ያመራሁት ትንሽ ቀደም ብዬ ነበር፡፡ ክፍለ ጊዜው አልቆ ክፍል ውስጥ የነበሩት መምህር ሲወጡ እኔ ገባሁ፡፡ እንደገባሁም ስም ስጠራ 56 ተማሪዎች ክፍል ውስጥ ነበሩ፡፡ ከዚያ ወደእለቱ ትምህርት አመራሁ፡፡ መልመጃዎቹ ተማሪዎች በተደራጁበት ቡድን የሚሰሩ ሲሆን የቀረቡት ጥያቄዎችም ተከታዬቹ ነበሩ፡፡

| | |
|---|---|
| ሀ. የተቀሰመ | ረ. ሙሾዋን |
| ለ. ተዝለፍልፎ | ሰ. ልቦናው |
| ሐ. ሲሽልል | ሸ. ለውሶ |
| መ. ብላቴና | ቀ. ቀመረ |
| ሠ. ራደች | |

እነዚህን ቃላት በጥቁር ሰሌዳው ላይ ከጻፍኩ በኋላ በጋራ እየተወያዩ አውዳዊ ፍቻቸውን እንዲፈልጉላቸው ነገርኳቸው፡፡ እኔም እየተዘዋወርኩ የተማሪዎችን ውይይት እከታተል ነበር፡፡ ሁሉም ቡድን ውስጥ ያሉ ተማሪዎች ሞቅ ያለ ውይይት እያደረጉ በጥሩ መልኩ ጥያቄዎቹን ሲሰሩ ለመታዘብም ችያለሁ፡፡ ውይይታቸውን እንደጨረሱ በተሰጡ ጥያቄዎች ላይ ያልተግባቡበት ጉዳይ ካለ ብዬ ጥያቄ አንስቼ ነበር፡፡ ሆኖም አንድም እጅ ስላላየሁ ሁሉም እንደተግባቡ ተረዳሁ፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ ክፍለ ጊዜው ማብቃቱን የሚጠቁመው ደወል ተደወለ፡፡ እኔም ከመውጣቴ በፊት ስልጣኔን በሚመለከት ከ50 ባልበለጡ ቃላት ድርሰት ጽፈው ለሚቀጥለው ክፍለ ጊዜ እንዲመጡ የቤት ስራ ሰጠኋቸው፡፡ ከዚያም ክፍሉን ለቅቄ ወጣሁ፡፡

ቀን፡- 26/07/05

ሰዓት፡- 5፡35

ክ/ጊዜ፡- 6ኛ

በእለቱ ወደክፍል ከገባሁ በኋላ በባለፈው ክፍለ ጊዜ በቤት ስራ መልክ ጽፈው እንዲመጡ ያዘዝኳቸውን ድርሰት ይዘው መጠው እንደሆነ ጠየቅሁ፡፡ አብዛኛው ተማሪ ይዞ እንደመጣ በአንድ ድምጽ ገለጹልኝ፡፡ እኔም ወረቀቶችን መሰብሰብ ጀመርኩ፡፡ በዚህ ጊዜ ሁለት ተማሪዎች ሰርተው እንዳልመጡ ነገሩኝ፡፡ ለምን እንዳልጻፉ ስጠይቃቸው በባለፈው ክፍለ ጊዜ በችግር ምክንያት ስላልመጡ መሆኑን ነገሩኝ፡፡ እኔም ከክፍል መቅረት እንደሌለባቸው፣ ከአቅም በላይ በሆነ ችግር ምክንያት ቢቀሩም እንኳ ከጓደኞቻቸው ጠይቀው የተሰጡ ስራዎች ካሉ ሰርተው መምጣት እንዳለባቸው አስረዳኋቸው፡፡ እነሱም ምክሩን በእሽታ ተቀበሉ፡፡ በመቀጠልም ወደ እለቱ ትምህርት አመራን፡፡ በእለቱ የሰጠኋቸው መልመጃ ያልተሟሉ ዐ.ነገሮችን በሚሰጡ ቃላት ዘሮች ማሟላት የሚል ነበር፡፡ ጥያቄዎቹን በጥቁር ሰሌዳው ላይ ከጻፍኩላቸው በኋላ ግልጽ እንዲሆንላቸው በማሰብ ተከታዩን ምሳሌ ሰጠኋቸው፡፡

ምሳሌ፡- (ተስማማ) ጉባኤው በቀረበው አጀንዳ ላይ ____________ ይኖርበታል፡፡ (የተሰጠ ጥያቄ)

ጉባኤው በቀረበው አጀንዳ ላይ <u>መስማማት</u> ይኖርበታል፡፡ (የተሰጠ መልስ)

ከዚህ በኋላ ተማሪዎቹ በተደራጁበት ቡድን ሆነው የሞቀ ውይይት ማካሄድ ጀመሩ፡፡ እንደተለመደው እኔም እየተዘዋወርኩ መመልከቴን ቀጠልኩ፡፡ ሁሉም ቡድኖች በጥሩ መልኩ ጥያቄዎችን ሲሰሩም ለማስተዋል ችያለሁ፡፡ ውይይታቸውን እንዳጠናቀቁም ያልተስማሙበት ጉዳይ ካለ በሚል ጥያቄ አቀረብኩላቸው፡፡ ነገር ግን ያልተስማሙበት ጉዳይ እንደሌለ እየነገሩኝ እንዳለ ደወል በመደወሉ ክፍሉን ለቅቄ ተማሪዎችን ተሰናብቼ ወጣሁ፡፡

ቀን፡- 29/07/05

ሰዓት፡- 6:30

ክ/ጊዜ፡- 1ኛ

በእለቱ ወደክፍል ገብቼ ስም ስጠራ ሁሉም ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ተገኝተው ነበር። በመቀጠል በባለፈው ክፍለ ጊዜ የሰበሰብኩትን ድርሰት አርሜ አምጥቼው ስለነበር ለተማሪዎች መለስኩላቸው። ለአብነት ይሆሉ ብዬ ያሰብኳቸውን ሁለት ድርሰቶች ግን ለተማሪዎች አነበብኩላቸው። በማስከተልም ያደረጉት ሙከራ መልካም እንደነበር ነገርኳቸው። ከዚያም ወደ እለቱ ትምህርት ገባን። የእለቱ ትምህርታችን ደግሞ በእዝባር ተለያይተው የቀረቡ ቃላት ላይ ከግጥሙ ውጭ የሆኑ ቃላትን ወይም ሀረጋትን በመጨመር የተሟላ ዐ.ነገር እንዲሰሩ የሚጠይቅ ነበር። ከተሰጧቸው ቃላት መካከልም ተከታዬቹ ይገኙበታል።

- ዜማ/ ሰማ
- ያሬድ/ ነው
- ሰባት/ ሲሄድ

በተሰጣቸው ጥያቄ ላይ ተማሪዎች ሞቅ ያለ ውይይት ሲያደርጉ እኔም እየተዘዋወርኩ ምልከታየን ቀጠልኩ። ሁሉም ቡድኖች ስራቸውን በሚገባ እየሰሩም ለማስተዋል ችያለሁ። በአብዛኛው ጥያቄዎች ላይ ተማሪዎች ተቀራራቢና ትክክለኛ ምላሽ እየሰሩ ነበር። ሆኖም ‹‹ሰባት/ ሲሄድ›› በሚለው ጥያቄ ላይ ግን ልዩነቶችን ስላስተዋልኩ ጥያቄውን ለክፍሉ በማቅረብ ወደ  አጠቃላይ ውይይት እንዲቀየር አደረግሁ። የተለያዩ ምላሾችም ይሰሙ ጀመር። ከምላሾቹ መካከል ‹‹ሰባት ሰዎች ሲሄዱ ነበር››፣ ‹‹እኔ ሰባት ጊዜ ስሄድ ዋልኩ››፣ ‹‹አበበ ሰባት በጎችን ይዞ ወደ ሜዳ ሲሄድ አየሁት››፣ ‹‹ት/ቤት ሰባቴ ስሄድ ነበር›› የሚሉት ይገኙበታል። እኔም ሁሉም ምላሾች ትክክል እንደሆኑ በማስረዳት ላይ እንዳለሁ ክፍል ጊዜው መጠናቀቁን የሚጠቁመው ደወል በመደወሉ ተማሪዎችን ተሰናብቼ ወጣሁ።

ቀን፡- 04/08/05

ሰዓት፡- 2፡00

ክ/ጊዜ፡- 1ኛ

ይህ እለት የመጨረሻውን የሙከራ ትምህርት የምሰጥበት ቀን ነበር። ወደ ክፍል ያመራሁትም እንደተለመደው ቀደም ብዬ ነበር። ሰዓቱ ሲደርስም ወደ ክፍል በመግባት ስም ጠራሁ። ሁሉም ተማሪ በክፍል ውስጥ ተገኝቶ ነበር። ከዚህ በመቀጠል ከግጥሙ የወጡ ጥያቄዎችን በጥቁር ሰሌዳው ላይ በመጻፍ በተደራጁበት ቡድን ሆነው ውይይት እንዲያደርጉ አዘዝኩ። ከቀረቡት ጥያቄዎች መካከል ተከታዬቹ ይገኙበታል።

- ስለ ቅዱስ ያሬድ ምን ታውቃላችሁ?
- ቅጠሊቱ የራደችው ምን ስለሰማች ይመስላችኋል?
- ቅዱስ ያሬድ ዜማውን የቀመረው እንዴት ነው?
- ግጥሙን አንብባችሁ ስትጨርሱ ምን አይነት ስሜት ተሰማችሁ?

ተማሪዎቹም በየቡድናቸው ሆነው የሞቀ ውይይት ማካሄዳቸውን ቀጠሉ። እኔም ምን ያክል እየሰሩ እንደሆነ ለመታዘብ እየተዘዋወርኩ ምልከታዬን ቀጠልኩ። ሁሉም ቡድኖች በሚገባ እየተወያዩ ሲሰሩም ለማስተዋል ችያለሁ። ከቡድኖቹ መካከል አንደኛው ግን ያልተስማሙበት ጥያቄ እንዳለ ጠርተው ነገሩኝ። እኔም ጠጋ ብዬ ያልተስማሙበት የትኛው ጥያቄ እንደሆነ ጠየቅኋቸው። እነሱም ‹‹ቅዱስ ያሬድ ዜማውን የቀመረው እንዴት ነው?›› የሚለው ላይ እንደሆነ ነገሩኝ። እኔም ጥያቄውን ለክፍሉ በሙሉ በማቅረብ ሁሉም ተማሪ እንዲወያይበት አደረግሁ። አብዛኞቹ ተማሪዎችም የትሉን ፉከራና የቅጠሏን ለቅሶ በመለወስ ነው ዜማውን የቀመረው ሲሉ፤ የተወሰኑቱ ደግሞ ከዛፍ ቀስሞ ነው የሚል ምላሽ ሰጡ። እኔም የሁሉንም ተማሪዎች ሙከራ በማድነቅ ዜማውን የቀመረው የትሉን ፉከራና የቅጠሏን ለቅሶ በአንድ ላይ በመቀላቀል እንደሆነ አስረዳኋቸው።

ከዚህ በመቀጠል በሁለቱ ግጥሞች ከተማሩት ትምህርት ውስጥ ግልጽ ያልሆነላቸው ነገር ካለ እንዲጠይቁኝ ነገርኳቸው። እጁን ያወጣ ተማሪ ባለማየቴ ጥያቄ እንደሌላቸው ተረዳሁ። እኔም በአጠቃላይ በሁለቱ ግጥሞች ላይ ተመስርተን የአማርኛ ቋንቋ የአንብቦ

መረዳትና የጽሕፈት ክሂል የተማርንበት የአስር ክፍለ ጊዜያት የመማር ማስተማር ሂደት እዚህ ላይ መጠናቀቁን ነገርኳቸው፡፡ ከዚህ በኋላ የሚቀረን የድህረ ትምህርት ፈተና መሆኑንና የፈተናው ቀንም በ07/08/05 ዓ.ም. ከ8፡30 ጀምሮ እንደሆነ ገለጽኩላቸው፡፡ በእለቱም ሁሉም ተማሪ እንዳይቀር ከአደራ ጋር አሳሰብኩ፡፡ ከዚህ ባሻገር ለመደበኛዋ መምህርት እሳቸው የሚያስተምሯቸው በቁጥጥር ሁኔታ የተያዙ የ9[25] ክፍል ተማሪዎችን በፈተናው እለት እንዲገኙ ይነግሩልኝ ዘንድ ጠየቅኋቸው፡፡ መምህርቷም እንደሚነግሩልኝ ቃል ገቡልኝ፡፡ እኔም ስለትብብራቸው አመስግኜ ተለያየን፡፡

በአጠቃላይ ከመጋቢት 04/2005 እስከ ሚያዚያ 04/2005 ዓ.ም. ድረስ ለአራት ተከታታይ ሳምንታት (በሳምንት ሁለት ክፍለ ጊዜ) ለአስር ክፍለ ጊዜያት የተካሄደው በግጥም አማካይነት የአማርኛ ቋንቋ አንብቦ መረዳትና ጽሕፈት ክሂልን የማስተማር ሂደት በእንደዚህ አይነት መልኩ ተጠናቀቀ፡፡ በሂደቱም ተማሪዎች አንብቦ መረዳትን፣ የቃላትን አውዳዊ ፍቺ መፈለግን፣ ሐሳባቸውን በአግባቡ መግለጽን፣ መነሻ ቃላት ወይም ሀረጋትን መሰረት በማድረግ ዐ.ነገር መጻፍን፣ በዕዝባር ተለያይተው በተሰጡት ቃላትና ሀረጋት ላይ ከግጥሙ ውጭ የሆኑ ቃላትን ወይም ሀረጋትን ተጠቅሞ ዐ.ነገር መመስረትን፣ ድርሰት መጻፍን እና የመሳሰሉትን ተግባራት በሚገባ ተለማምደዋል፡፡ በአጠቃላይም ሂደቱ ቋንቋን በሚገባ ለማስተማር የሚያስችል ነበር፡፡ ለዚህ ዋነኛው ምክንያት ደግሞ በትምህርቱ ሂደት ተግባራዊ የሆነው የማስተማሪያ ዘዴ ፈጠራዊ ዘዴ መሆኑ ነው፡፡ ዘዴው ተማሪ- ተኮር በመሆኑ አብዛኞቹ ስራዎች በተማሪዎች በጋራ የተሰሩ ነበሩ፡፡ ይህ በመሆኑም ተማሪዎች በቡድን ሆነው የሞቀ ውይይትና ክርክር እንዲያደርጉ፣ ሐሳባቸውን በድፍረት ማስረዳት እንዲችሉ፣ አንዱ ከሌላው እንዲማማሩ እድል ፈጥሮላቸዋል፡፡ ከዚህ ባሻገር ድርሰት ለመጻፍ ባደረጉት ጥረትም በቅድመ ትምህርት ፈተናው ከጻፏቸው ድርሰቶች የተሻሉ ድርሰቶችን ለመጻፍ ችለዋል፡፡ ለዚህ ማስረጃ ይሆኑ ዘንድም ተማሪዎች የጻፏቸው ድርሰቶች በአባሪ መልክ ተያይዘው ቀርበዋል፡፡ (አባሪ አስር ‹‹ሀ›› እና ‹‹ለ›› ገጽ 114 እና 115 ይመልከቱ)

ከዚህ በላይ በተጠኝነት ሁኔታ በአጥኚው ስር ሆነው የተማሩ ተማሪዎችን የመማር ማስተማር ሂደት በአጭሩ ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡ በመደበኛዋ መምህርት በቁጥጥር ሁኔታ የተማሩ ተማሪዎች የተማሩበትን ሁኔታ ለመረዳት ደግሞ በአባሪ ሁለት ከገጽ 94 — 98 ድረስ የቀረቡ ማስረጃዎችን መመልከት ይቻላል፡፡

## 4.2. የመረጃዎች ትንተና

በዚህ ክፍል ከቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናዎች፤ እንዲሁም ከጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ተተንትነው ቀርበዋል። ማለትም በቁጥጥር ሁኔታና በተጠኝነት ሁኔታ የተጠኑት የሁለቱ ቡድኖች የቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናዎች ውጤት ከተወዳደረ በኋላ የተጠኝ ቡድኖች ውጤት በቁጥጥር ሁኔታ ከተጠኑት ቡድኖች የተሻለ መሆን አለመሆኑ በስታስቲካዊ ዘዴ ይረጋገጣል። በዚህም የጥናቱ አላማዎች ግባቸውን መምታት አለመምታታቸው ይረጋገጣል።

ለአተናተን እንዲሁም ለአቀራረብ ያመች ዘንድም መረጃዎቹ ለሁለት ተከፍለው ትንተና ተካሂዶባቸዋል። የመጀመሪያው ክፍል የቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናዎች ትንተና የሚቀርብበት ሲሆን ሁለተኛው ክፍል ደግሞ በተጠኝነት የተያዙት ተማሪዎች ትምህርቱን ከተከታተሉ በኋላ ስለተማሩበት አዲስ ዘዴ፣ ስለትምህርቱ ሂደት እንዲሁም ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ያላቸውን አመለካከት የገለጹበት የጽሑፍ መጠይቅ የሚተነተንበት ነው።

### 4.2.1. የቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናዎች ውጤት ትንተና

በዚህ ንዑስ ርዕስ ተማሪዎች ከመማራቸው በፊትና ከተማሩ በኋላ ያስመዘገቧቸው የፈተና ውጤቶች እንደየቅደም ተከተላቸው ተተንትነው ቀርበዋል። (የቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናውን ለማየት አባሪ አንድ ከገጽ 87 — 93 ይመልከቱ)

#### 4.2.1.1. የቅድመ ትምህርት ፈተና ውጤት ትንተና

በምዕራፍ ሶስት ላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በቁጥጥርና በተጠኝነት ሁኔታ የተያዙት ቡድኖች ከሙከራ ጥናቱ በፊት የነበራቸው የቋንቋ ክህሎትና በተመሳሳይ ይዘት፣ በተለያዩ ዘዴዎችና መምህራን ከተማሩ በኋላ የሚያሳዩትን ለውጥ ለመፈተሽ የቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናዎችን መስጠት አንዱ መንገድ ነው። በዚህ መሰረትም የሁለቱ ቡድኖች የቅድመ ትምህርት ፈተና በሶስት አራሚዎች ከታረመ በኋላ የሰጡት አማካይ ውጤት (mean) እና መደበኛ ልይይት (standard deviation) ተሰልቶ እንደሚከተለው ተተንትኖ ቀርቧል። ለሁለቱም ቡድኖች በሶስቱም አራሚዎች ለእያንዳንዱ ተማሪ የተሰጠው የቅድመ ትምህርት ፈተና ውጤት ከሙቶ በአባሪ አራትና አምስት ከገጽ 103 — 106 ይገኛል።

ሰንጠረዥ 1፡- በሶስት አራሚዎች ለሁለቱም ቡድኖች የተሰጡ የቅድመ ትምህርት ፈተና ውጤቶች አማካይና መደበኛ ልይይት

| የፈተናው አይነት | ምድብ | ውጤት | አራሚዎች | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | 1 | 2 | 3 |
| ቅድመ ትምህርት | $9^{25}$ | አማካይ | 37.8103 | 37.00 | 36.8793 |
| | | መደበኛ ልይይት | 14.54269 | 13.72921 | 13.54924 |
| | $9^{29}$ | አማካይ | 37.7931 | 37.6897 | 38.2241 |
| | | መደበኛ ልይይት | 13.98089 | 13.73203 | 14.10119 |

ከሰንጠረዡ መረዳት እንደሚቻለው በየቡድኑ ፈተናውን የወሰዱ ተማሪዎች ለቅድመ ትምህርት ፈተናው የሰጡት መልስ በሶስት አራሚዎች ከታረመ በኋላ እያንዳንዱ አራሚ በየቡድኑ ለእያንዳንዱ ተማሪ ፈተና የሰጠው ውጤት ተደምሮ ለክፍሉ ተፈታኝ ተማሪዎች ብዛት ሲካፈል የየቡድኑን አማካይ ውጤት ይሰጣል፡፡ እንዲሁም የተገኘውን አማካይ ውጤት ከእያንዳንዱ ተማሪ ውጤት ላይ በመቀነስና ለክፍሉ ተፈታኝ ተማሪዎች ብዛት በማካፈል የሚገኘው ውጤት ፖዘቲቭ ካሬ ዘር መደበኛ ልይይት ይሰጣል፡፡ ይህም የተፈታኝ ተማሪዎች ውጤት ከአማካይ ውጤታቸው ምን ያክል በአማካይ እንደሚርቅ ያመለክታል፡፡ በመሆኑም አራሚ አንድ ለ‹‹$9^{25}$›› የሰጠው አማካይ ውጤት 37.8103 ሲሆን መደበኛ ልይይቱ 14.54269 ነው፡፡ ለ‹‹$9^{29}$›› ደግሞ 37.7931 አማካይ ውጤት ሲሰጥ መደበኛ ልይይቱ 13.98089 ሆኗል፡፡ አራሚ ሁለት ለ‹‹$9^{25}$›› 37.00 አማካይ ውጤት ሲሰጥ መደበኛ ልይይቱ 13.72921 ነው፡፡ ለ‹‹$9^{29}$›› ደግሞ 37.6897 አማካይ ውጤት ሰጧል፡፡ መደበኛ ልይይቱ 13.73203 ሆኗል፡፡ አራሚ ሶስት በበኩሉ ለ‹‹$9^{25}$›› የሰጠው አማካይ ውጤት 36.8793 ሲሆን መደበኛ ልይይቱ 13.54924 ነው፡፡ ለ‹‹$9^{29}$›› ደግሞ 38.2241 ሰጧል፡፡ መደበኛ ልይይቱ 14.10119 ሆኗል፡፡

ከዚህ ቀጥሎ ሶስቱ አራሚዎች ለሁለቱም ቡድኖች የሰጡትን ውጤት አማካይና መደበኛ ልይይት በማስላት ውጤቱን በቲ- ቴስት ቀመር ለማረጋገጥ ተሞክሯል፡፡ በዚህ መሰረትም የተገኘው ውጤት ተከታዩን ይመስላል፡፡

ሰንጠረዥ 2፡- የሁለቱ ቡድኖች የቅድመ ትምህርት ፈተና ውጤት በቲ- ቴስት ቀመር ሲሰላ

| የፈተናው አይነት | ምድብ | አማካይ | መደበኛ ልይይት | የነጻነት ደረጃ | የቲ-ስሌት | የቲ-ሰንጠረዥ | የጉልህነት ደረጃ | ጉልህ ልዩነት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ቅድመ ትምህርት | $9^{25}$ | 37.229 | 13.9403 | 114 | 0.310 | 1.6645 | 0.05 | የለም |
| | $9^{29}$ | 37.9023 | 13.9380 | | | | | |

ከሰንጠረዡ ለመገንዘብ እንደሚቻለው ተማሪዎች ያገኙት የቅድመ ትምህርት ፈተና ውጤት በሶስት አራሚዎች ታረመ፡፡ ቀጥሎ የእንዳንዱ ተማሪ ውጤት ተደምሮ በየቡድኑ ላሉት ተፈታኞች ሲካፈል እያንዳንዱ አራሚ ለየቡድኖቹ የሰጠውን ውጤት አማካይ አስገኘ፡፡ በሶስቱ አራሚዎች የተገኙት አማካይ ውጤቶች ተደምረው ለሶስት ሲካፈሉ ደግሞ የየቡድኖችን አማካይ ውጤት አስገኘ፡፡ በዚህ መሰረትም ‹‹$9^{25}$›› 37.229 አማካይ ውጤት ሲያገኝ ‹‹$9^{29}$›› ደግሞ 37.9023 አማካይ ውጤት አገኘ፡፡ እንዲሁም የተገኘውን አማካይ ውጤት ከእያንዳንዱ ተማሪ ውጤት ላይ በመቀነስና ለክፍሉ ተፈታኝ ተማሪዎች ብዛት በማካፈል የተገኘው ውጤት ፖዘቲቭ ካሬ ዘር መደበኛ ልይይት አስገኘ፡፡ በዚህ መሰረትም ‹‹$9^{25}$›› መደበኛ ልይይቱ 13.9403 ሲሆን ‹‹$9^{29}$›› ደግሞ 13.9380 ነው፡፡

በመቀጠል በቅድመ ትምህርት ፈተናው የተገኘውን የየቡድኖችን አማካይ ውጤት ና መደበኛ ልይይት በመያዝ ውጤቱን በቲ- ቴስት ቀመር ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በተደረገው የቲ- ቴስት ስሌት መሰረት የቲ-ስሌት ዋጋው 0.310 ሲሆን በ0.05 የጉልህነት ደረጃ በ114 የነጻነት ደረጃ የቲ-ሰንጠረዥ ዋጋ 1.6645 ሆኗል፡፡ ስለዚህ የተገኘው የቲ- ዋጋ (0.310) ከቲ-ሰንጠረዥ ዋጋ (1.6645) በማነሱ በተማሪዎች የቅድመ ትምህርት ፈተና ውጤት መካከል የጎላ ልዩነት አለመኖሩን ያመለክታል፡፡ ከዚህ ባሻገር የሁሉም ተማሪዎች ውጤት ተወስዶ በተደረገው ስሌት የጎላ የውጤት ልዩነት አለመታየቱ በሶስቱ አራሚዎች መካከል ተቀራራቢነት እንዳለ ያመላክታል፡፡

### 4.2.1.2. የድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት ትንተና

የሁለቱም ቡድን የቅድመ ትምህርት ፈተና ውጤት ከተመዘገበ በኋላ ተከታዩ ተግባር ከመጋቢት 04/2005 እስከ ሚያዚያ 04/2005 ዓ.ም. ድረስ ተጠኚ ተማሪዎችን በክፍል በመገኘት ማስተማር ነበር፡፡ ቀደም ሲል በምዕራፍ ሶስት ላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው

የ‹‹$9^{25}$›› ክፍል ተማሪዎች በተለመደው ዘዴ በመደበኛዋ መምህርት፣ የ‹‹$9^{29}$›› ክፍል ተማሪዎች ደግሞ በአዲስ ዘዴ በአጥኝው ለአራት ተከታታይ ሳምንታት እንዲማሩ ተደረገ፡ ፡ ከዚያም የድህረ ትምህርት ፈተና ተሰጣቸው። የተማሪዎች የድህረ ትምህርት ፈተናም በሶስት አራሚዎች እንዲታረም ከተደረገ በኋላ እያንዳንዱ አራሚ ለእያንዳንዱ ቡድን የሰጠው አማካይ ውጤትና መደበኛ ልይይት በሚከተለው መልኩ ቀርቧል። ለሁለቱም ቡድኖች በሶስቱም አራሚዎች ለእያንዳንዱ ተማሪ የተሰጠው የድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት ከመቶ በአባሪ ስድስትና ሰባት ከገጽ 107 — 110 ይገኛል።

ሰንጠረዥ 3፡- በሶስት አራሚዎች ለሁለቱም ቡድኖች የተሰጡ የድህረ ትምህርት ፈተና ውጤቶች አማካይና መደበኛ ልይይት

| የፈተናው አይነት | ምድብ | ውጤት | አራሚዎች | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | 1 | 2 | 3 |
| ድህረ ትምህርት | $9^{25}$ | አማካይ | 51.4310 | 51.8621 | 51.5690 |
| | | መደበኛ ልይይት | 13.88058 | 13.93021 | 13.89827 |
| | $9^{29}$ | አማካይ | 79.6897 | 80.4138 | 80.1724 |
| | | መደበኛ ልይይት | 8.43178 | 8.26965 | 8.17139 |

ከሰንጠረዡ ለመረዳት እንደሚቻለው የተማሪዎች የድህረ ትምህርት ፈተና በሶስት አራሚዎች ታርሞ እያንዳንዱ አራሚ በያንዳንዱ ቡድን ላይ ለእያንዳንዱ ተማሪ የሰጠው ውጤት ተደምሮ ለየቡድኑ ተማሪ ብዛት ሲካፈል የየቡድኑን አማካይ ውጤት አስገኘ። እንዲሁም የተገኘውን አማካይ ውጤት ከእያንዳንዱ ተማሪ ውጤት ላይ በመቀነስና ለክፍሉ ተፈታኝ ተማሪዎች ብዛት በማካፈል የሚገኘው ውጤት ፖዘቲቭ ካሬ ዘር የየቡድኑን መደበኛ ልይይት አስገኘ። በዚህ መሰረትም የመጀመሪያው አራሚ ለ‹‹$9^{25}$›› 51.4310 አማካይ ውጤት ሲሰጥ መደበኛ ልይይቱ 13.88058 ሆኗል። ለ‹‹$9^{29}$›› ደግሞ 79.6897 አማካይ ውጤት ሲሰጥ መደበኛ ልይይቱ 8.43178 ነው። ሁለተኛው አራሚ ለ‹‹$9^{25}$›› የሰጠው አማካይ ውጤት 51.8621 ሲሆን መደበኛ ልይይቱ 13.93021 ሆኗል። ለ‹‹$9^{29}$›› ደግሞ 80.4138 አማካይ ውጤት ሲሰጥ መደበኛ ልይይቱ 8.26965 ነው። እንዲሁም ሶስተኛው አራሚ ለ‹‹$9^{25}$›› 51.5690 አማካይ ውጤት ሲሰጥ መደበኛ ልይይቱ 13.89827 ሆኗል። ለ‹‹$9^{29}$›› ደግሞ የሰጠው አማካይ ውጤት 80.1724 ሲሆን መደበኛ ልይይቱ 8.17139 ነው።

ከዚህ በማስከተል በሶስቱ አራሚዎች የተሰጡትን የድህረ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤትና መደበኛ ልይይት በማስላት ውጤቱን በቲ- ቴስት ቀመር በሚከተለው መልኩ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ሰንጠረዥ 4፡- የሁለቱ ቡድኖች የድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት በቲ- ቴስት ቀመር ሲሰላ

| የፈተናው አይነት | ምድብ | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | የነጻነት ደረጃ | የቲ- ስሌት | የቲ- ሰንጠረዥ | የጉልህነት ደረጃ | ጉልህ ልዩነት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ድህረ ትምህርት | $9^{25}$ | 51.6207 | 13.90302 | 114 | 12.900 | 1.6645 | 0.05 | አለ |
| | $9^{29}$ | 80.0919 | 8.29094 | | | | | |

ከሰንጠረዡ ለመገንዘብ እንደሚቻለው የ‹‹$9^{25}$›› አማካይ ውጤት 51.6270 ሲሆን መደበኛ ልይይቱ 13.90302 ነው፡፡ የ‹‹$9^{29}$›› አማካይ ውጤት ደግሞ 80.0919 ሲሆን መደበኛ ልይይቱ 8.29094 ነው፡፡ በመቀጠል በተደረገው የቲ- ቴስት ስሌት መሰረት የቲ- ስሌት ዋጋው 12.900 ሆኖ ሲገኝ በ0.05 የጉልህነት ደረጃ በ114 የነጻነት ደረጃ የቲ- ሰንጠረዥ ዋጋ 1.6645 ሆኗል፡፡ ይህ የተገኘው የቲ- ስሌት (12.900) ውጤት ከቲ- ሰንጠረዥ ዋጋው (1.6645) በእጅጉ የበለጠ በመሆኑ በድህረ ትምህርት ፈተናው ውጤት ላይ በሁለቱ ቡድኖች መካከል ሰፊ ልዩነት መኖሩን ያሳየናል፡፡

ስለሆነም ከዚህ በላይ ከተገኙት ውጤቶች መገንዘብ የምንችለው በቅድመ ትምህርት ፈተናው ተቀራራቢ ውጤት የነበራቸው ሁለቱ ቡድኖች በግጥም አማካይነት በተለያየ ዘዴ ከተማሩ በኋላ በአዲሱ ዘዴ የተማሩት ተማሪዎች የተሻለ ውጤት ማስመዝገባቸውን ነው፡፡ እነዚህ የተሻለ ውጤት ያመጡት ተማሪዎች ውጤቱን ለማምጣት የቻሉት በድንገት ሳይሆን በነጻ ተላውጦ ማለትም በግጥም አማካይነት የአማርኛ ቋንቋ አንብቦ መረዳትና ጽሕፈት ክሂልን ስለተማሩ ነው፡፡ ይህ ውጤትም ከጥናቱ አብይ አላማ ጋር በደንብ የሚስማማ መሆኑን ያሳያል፡፡ ማለትም በግጥም አማካይነት የአማርኛ ቋንቋን አንብቦ መረዳትና ጽሕፈት ክሂልን ማስተማር ውጤታማ መሆኑን በሚገባ አረጋግጧል፡፡ ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ የጽሑፍ መጠይቅ መረጃዎች ይተነተናሉ፡፡

## 4.2.2. የጽሑፍ መጠይቅ መረጃዎች ትንተና

በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር ከጽሑፍ መጠይቅ የተሰበሰቡ መረጃዎች ትንተና ተደርጎባቸዋል፡፡ የጽሑፍ መጠይቁ የመጀመሪያ ክፍል በስሩ የያዛቸው ጥያቄዎች የተማሪዎችን ዳራ ለማወቅ የቀረቡ ነበሩ፡፡ መጠይቁን ከሞሉት 58 ተማሪዎችም ተከታዩቹ መረጃዎች ተገኝተዋል፡፡ (የጽሑፍ መጠይቁን ለማየት አባሪ ሶስት ከገጽ 99 — 102 ይመልከቱ)

ሰንጠረዥ 5፡- የተማሪዎችን ዳራ የሚያሳይ

| | 1.ጾታ | | | 2.እድሜ | | | 3. የአፍ መፍቻ ቋንቋ | | | 4.በሚኒ ሚዲያ፣ በስነ ጽሑፍ እና ድራማ ክበቦች ተሳትፎ ታደርጋለህ/ ታደርጊያለሽ? | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ወንድ | ሴት | ድምር | 14-18 | ከ18 በላይ | ድምር | አማርኛ | ሌላ | ድምር | አዎ | አላደርግም | ድምር |
| በቁጥር | 28 | 30 | 58 | 58 | --- | 58 | 58 | --- | 58 | 22 | 36 | 58 |
| በመቶኛ | 48.275 % | 51.724 % | 100 % | 100 % | --- | 100 % | 100 % | --- | 100 % | 37.9317 % | 62.068 % | 100 % |

ከሰንጠረዡ መረዳት እንደሚቻለው መጠይቁን ከሞሉት ተማሪ መካከል 28 (48.275%) ወንዶች፣ 30 (51.724) ያክሉ ደግሞ ሴቶች ናቸው፡፡ ይህም የወንዶችና የሴቶች መጠን ተቀራራቢነት ያለው መሆኑን አመላካች ነው፡፡ በዚህ ጥናት ተሳታፊ የሆኑት የ9[29] ተማሪዎች በሙሉ ማለትም 58 (100%) ዕድሜያቸው ከ14-18 የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኝ ነው፡፡

የአፍ መፍቻ ቋንቋቸውን በተመለከተ የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው 58 (100%) ሁሉም በአማርኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ የቅድመ ትምህርት ፈተና ውጤቱ እንደሚያመለክተው በተማሪዎቹ ላይ ከፍተኛ የሆነ አንብቦ የመረዳትና የጽሕፈት ችሎታ ድክመት ይታይባቸው ነበር፡፡ ሆኖም በፈጠራዊ ዘዴ በግጥም አማካይነት ከተማሩ በኋላ ግን የተሻሉ ዐነገሮችንና ድርሰቶችን የመጻፍ እንዲሁም አንብቦ የመረዳት አቅማቸው አድጓል፡፡ ይህንንም በልምምዱ ወቅት የጻፏቸውን ድርሰቶች በማየት ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ (አባሪ አስራአንድ ‹‹ሀ›› እና ‹‹ለ››ን ገጽ 116 እና 117 ላይ ይመልከቱ)

መጠይቁን የሞሉት ተማሪዎች ከትምህርታቸው ጎነ ለጎን የቋንቋ ችሎታቸውን ሊያጎለብቱ በሚችሉ ክበባት ውስጥ ተሳትፎ ያደርጉ እንደሆነ ለማወቅ ተፈልጎ ለቀረበላቸው ጥያቄ 36 (62.068%) ያህሉ ተማሪ እንደማይሳተፍ ሲገልጹ 22 (37.9317%) ያክሉ ደግሞ

ተሳትፎ እንደሚያደርጉ ገልጸዋል። ስለዚህ ተማሪዎች በስነ ጽሑፍ ነክ ክበባት ውስጥ አለመሳተፋቸው ሐሳባቸውን በንግግርም ሆነ በጽሑፍ የመግለጽና የማስተላለፍ አቅማቸው እንዳያድግ የራሱን አስተዋጽኦ ማበርከቱን መገመት ይቻላል።

በጽሑፍ መጠይቁ ሁለተኛ ክፍል የቀረቡት ጥያቄዎች ደግሞ ተማሪዎች በፈጠራዊ ዘዴ በግጥም አማካይነት አማርኛ ቋንቋን ከመማራቸው በፊት የነበራቸውን ስነ ጽሑፋዊ እውቀት ለማወቅ ታስበው የቀረቡ ናቸው።

ሰንጠረዥ 6፡- ተማሪዎች ከትምህርቱ በፊት የነበራቸውን ስነ ጽሑፋዊ እውቀት ለማወቅ የቀረበ

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | የስምምነት ምርጫዎች (በቁጥርና በመቶኛ) | | | | ያለመስማማት ምርጫዎች (በቁጥርና በመቶኛ) | | | የሚጠበቀው አዎንታዊ(+) ወይም አሉታዊ(-) መልስ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ሀ | ለ | ድምር | ሐ | መ | ድምር | |
| 1 | ከዚህ በፊት በትርፍ ጊዜዬ የተለያዩ የፈጠራ ጽሑፎችን ማለትም አጭር ልቦለድ፣ ረጅም ልቦለድ፣ ግጥም፣ ተውኔት…ወዘተ. አንብቤ ወይም ተከታትዬ አውቃለሁ። | ቁጥር | 19 | 22 | 41. | 11 | 6 | 17 | + |
| | | መቶኛ | 32.758 % | 37.931 % | 70.689 % | 18.965 % | 10.344 % | 29.309 % | |
| 2 | ቀደም ሲል የተለያዩ ልቦለዶችን፣ ግጥሞችን…ወዘተ. የማነበው ማርክ ወይም ውጤት ለማግኘት ስል ነበር። | ቁጥር | 17 | 11 | 28 | 16 | 14 | 30 | - |
| | | መቶኛ | 29.310 % | 18.965 % | 48.275 % | 27.586 % | 24.137 % | 51.723 % | |
| 3 | የፈጠራ ጽሑፎችን አንብቤ በመረዳት ከነሱ የሚዘጋጁትን መልመጃዎች ለመመለስ የሚያስችል በቂ የሆነ ትምህርት ከ9ኛ ክፍል በፊት ተምሬያለሁ። | ቁጥር | 6 | 14 | 20 | 21 | 17 | 38 | - |
| | | መቶኛ | 10.344 % | 24.137 % | 34.481 % | 36.206 % | 29.310 % | 65.516 % | |

የሚጠበቅ አዎንታዊ (+) መልስ ነው ሲባል ለአማራጮች የሚሰጠው ነጥብ ሀ=4፣ ለ=3፣ ሐ=2፣ መ=1 ነው። የሚጠበቀው መልስ አሉታዊ (-) ነው ሲባል ደግሞ ሀ=1፣ ለ=2፣ ሐ=3፣ መ=4 ነጥብ ይሰጣቸዋል።

በሰንጠረዠ ውስጥ የቀረቡት መስማማትና አለመስማማትን የሚወክሉ አራት ምርጫዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

ሀ. በጣም እስማማለሁ

ለ. እስማማለሁ

ሐ. አልስማማም

መ. በጣም አልስማማም

ከላይ ከቀረበው ሰንጠረዥ 6 ለመረዳት እንደሚቻለው በተ.ቁ አንድ ላይ ለቀረበው ጥያቄ መጠይቁን ከሞሉት 58 ተማሪዎች መካከል 41 (70.689%) ስምምነታቸውን ገልጸዋል፡፡ በሌላ በኩል ‹‹ቀደም ሲል የተለያዩ ልቦለዶችን፣ ግጥሞችን...ወዘተ. የማነበው ማርክ ወይም ውጤት ለማግኘት ስል ነበር፡፡›› በሚል ለቀረበው የተ.ቁ ሁለት ጥያቄ 30 (51.723%) የሚሆኑት መላሾች አለመስማማታቸውን ገልጸዋል፡፡ ይህም በተ.ቁ አንድ ላይ ለቀረበላቸው ጥያቄ ከሰጡት መልስ ጋር የሚስማማ ነው፡፡ ምክንያቱም የፈጠራ ጽሑፎችን የሚያነቡት ውጤት ለማግኘት ሳይሆን በፍላጎታቸው መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

ሌላው ለተጠኝ ተማሪዎች በተራ ቁጥር ሶስት ላይ ለቀረበው ጥያቄ 38 (65.516%) የሚሆኑት ተማሪዎች አለመስማማታቸውን ገልጸዋል፡፡ ለዚህ አለመስማማታቸውም ጥያቄ ቁጥር 17 ላይ የሰጡት መልስ ምክንያት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህንን ጉዳይ በደንብ ያስረዳልን ዘንድም የሁለት ተማሪዎችን አስተያየት በናሙናነት እንመልከት፡፡

አንደኛው ተማሪ እንዲህ ይላል፤ ‹‹ከ9ኛ ክፍል በፊት ተመሳሳይ የሆኑ የቃላት፣ የሰዋስው፣ የምሳሌያዊ ንግግር...ወዘተ. መልመጃዎችን ብቻ ነበር የምንሰራው፡፡ አሁን ግን ከዚህ ለየት ያለ ስለሆነ ወድጀዋለሁ፡፡›› ሌላኛው ተማሪ ደግሞ የሚከተለውን ሀሳብ ሰንዝሯል፤ ‹‹ከዚህ በፊት መልመጃዎችን የምሰራው ማርክ ለማግኘትና መምህሬ እንዳይቆጣኝ በመፍራት ነበር፡፡ አሁን ግን ደስ እያለኝ ሳይሰለቸኝ ከጓደኞቼ ጋር መልመጃዎችን ሰርቻለሁ፡፡››

ከላይ ለናሙናነት ከቀረቡት የሁለቱ ተማሪዎች ምላሾች መረዳት እንደሚቻለው በግጥም አማካይነት ቋንቋን በማስተማር ሂደት የሚዘጋጁ መልመጃዎችን በብቃት ለመመለስ ከነባሩ ዘዴ ይልቅ ፈጠራዊ ዘዴ የተሻለ ነው፡፡ ቋንቋን ለመማር ተብሎ ከስነ ጽሑፍ ስራዎች ውስጥ የሚዘጋጁ መልመጃዎች በተማሪዎች ዘንድ የሚወደዱ እንዲሁም የቋንቋ

ክሂሎቻቸውን የሚያጎለብቱ መሆን ይገባቸዋል (Waker, 1983፡ 7-8)፡፡ የተማሪዎች ምላሾችም ከዚሁ ጋር የሚጣጣሙ ናቸው፡፡

ከላይ ከቀረበው ትንታኔ ለመገንዘብ እንደሚቻለው ተማሪዎች ከዚህ በፊት በፈጠራዊ ዘዴ አማካይነት አማርኛ ቋንቋን ተምረው የሚያውቁ አይመስልም፡፡ ስለዚህ ቀጣዩ ጉዳይ የሚሆነው በግጥም አማካይነት በፈጠራዊ ዘዴ አማርኛን ከተማሩ በኋላ የቋንቋ ችሎታቸው ምን ያክል አድጓል? የሚለው ይሆናል፡፡ ለዚህ ጥያቄ ምላሽ ያስገኛሉ በሚል የተዘጋጁት ጥያቄዎች በክፍል ሁለት ስር ከተ.ቁ. 4 - 7 ሰፍረዋል፡፡ ከነዚህ ጥያቄዎች የተገኙ ምላሾች ከዚህ እንደሚከተለው በቅደም ተከተል ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

ሰንጠረዥ 7፡- ተማሪዎች ግጥሞችን አንብበው በሚወያዩበት ወቅት የተሰማቸውን ስሜት ለማወቅ የቀረበ

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | | የስምምነት ምርጫዎች (በቁጥርና በመቶኛ) | | | ያለመስማማት ምርጫዎች (በቁጥርና በመቶኛ) | | | የሚጠበቀው አዎንታዊ(+) ወይም አሉታዊ(-) መልስ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ሀ | ለ | ድምር | ሐ | መ | ድምር | |
| 4 | የፈጠራ ጽሑፎችን አንብበን እርስ በርስ በመወያየትና በመተጋገዝ መማራችን የቋንቋ ክሂሎችንን ለማጎልበት ይረዳናል ብዬ አስባለሁ፡፡ | ቁጥር | 43 | 8 | 51 | 4 | 3 | 7 | + |
| | | መቶኛ | 74.137 % | 13.793% | 87.93 % | 6.896 % | 5.172 % | 12.068 % | |
| 5 | የቀረቡልንን ግጥሞች ካነበብን በኋላ በጋራ በመወያየት እንድንሰራቸው በሚሰጡን መልመጃዎች ላይ ስንወያይ የቡድን አባላት የምንሰነዝረው ሀሳብ እርስ በርሱ የሚደጋገፍ ነበር፡፡ | ቁጥር | 24 | 18 | 42 | 13 | 3 | 16 | + |
| | | መቶኛ | 41.379 % | 31.034 % | 72.413 % | 22.413% | 5.172 % | 27.585 % | |
| 6 | ግጥሞችን ካነበብን በኋላ ስንወያይ በመካከላችን የሀሳብ ልዩነት ይፈጠር ስለነበር ሳንግባባ እንቀር ነበር፡፡ | ቁጥር | 6 | 14 | 20 | 13 | 25 | 38 | - |
| | | መቶኛ | 10.344 % | 24.137% | 34.482 % | 22.413% | 43.103 % | 65.516 % | |
| 7 | ግጥሞችን ካነበብን በኋላ የምናደርገው ውይይት በመካከላችን የሀሳብ ልዩነት ቢፈጥርም ከምናነሳቸው የማሳመኛ ነጥቦች የተነሳ ወደ አንድ ሀሳብ ለመምጣት አያቅተንም ነበር፡፡ | ቁጥር | 24 | 20 | 44 | 8 | 6 | 14 | + |
| | | መቶኛ | 41.379 % | 34.482% | 75.861 % | 13.793% | 10.344 % | 24.137 % | |

የተለያዩ የመስኩ ምሁራን እንደሚገልጹት የስነ ጽሑፍ አንደኛው ባህሪ አሻሚነቱ ነው፡፡ ይህ በመሆኑም በውይይት ጊዜ የጽሑፉን ይዘት በመደገፍ ወይም በመቃወም በሚፈጠረው ውይይት ተግባቦት እንዲፈጠር ያደርጋል (McRae, 1991፡ 59)፡፡ በመሆኑም ከላይ በቀረበው ሰንጠረዥ ውስጥ የተካተቱት ጥያቄዎች ለተማሪዎች የቀረቡት ይህንን እውነታ ለማረጋገጥ ሲባል ነው፡፡

በሰንጠረዥ ተ.ቁ አራት ላይ ለቀረበው ጥያቄ 51 (87.93%) የሚሆኑ መልስ ሰጪዎች አዎንታዊ መልስ ሰጥተዋል፡፡ ይህ ምላሽም የተማሪዎች የቋንቋ ክሂል አማርኛን በግጥም አማካይነት በመማራቸው ማደጉን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ እንዲሁም በተ.ቁ. አምስት ላይ ለቀረበው ጥያቄ 42 (72.413%) ያክል መላሾች መስማማታቸውን ገልጸዋል፡፡ ከዚህ ምላሽ መገንዘብ እንደሚቻለው በትምህርቱ ወቅት የቀረቡት መልመጃዎች የሚያወያዩ፣ የሚያከራክሩ ስለነበሩ በተማሪዎች መካከል ጥሩ መግባባትን ፈጥረው እንደነበር ነው፡፡

በሌላ በኩል በተ.ቁ. ስድስት ላይ ለቀረበው ጥያቄ 38 (65.516%) የሚሆኑ መልስ ሰጪዎች አለመስማማታቸውን ሲገልጹ 20 (34.482%) የሚሆኑት ደግሞ መስማማታቸውን ገልጸዋል፡፡ ከዚህ እንደምንረዳው በርካታ መላሾች አለመስማማታቸውን ስለገለጹ የሰጡት ምላሽ ከጥያቄ አምስት ጋር የሚጣጣም መሆኑን ነው፡፡ ማለትም በሚወያዩበት ወቅት የመግባባት ችግር እንደሌለባቸው ያስረዳል፡፡ ነገር ግን ለጥያቄ ቁጥር ስድስት ጥቂት የማይባሉ መላሾች መስማማታቸውን ስለገለጹ ምላሻቸው ከሌሎች መላሾች ሀሳብ ጋር የሚቃረን ነው፡፡ ይሁን እንጂ ‹‹ሳንግባባ እንቀር ነበር›› ሲሉ አንዱ የሌላውን ሀሳብ በመቀበል አለማመኑን ለመግለጽ እንጂ በመካከላቸው ተግባቦት እንዳልነበር ለመግለጽ ፈልገው አይደለም፡፡ ምክንያቱም ውይይት ሲደርጉ አንዱ አንዱን ለማሳመን ሲሉ ከፍ ያለ ክርክር በማድረግ ሀሳብ ለሀሳብ ሲለዋወጡ ታይቷልና፡፡ አንዱ አንዱን ለማሳመን ያልቻሉትም ስነ ጽሑፍ በባህሪው አሻሚ በመሆኑ አንዱ የተረዳበት መንገድ ከሌላኛው ስለሚለያይ ነው፡፡

ከዚህ በላይ የቀረበውን ሀሳብ ሊያጠናክር የሚችል ምላሽም ከተ.ቁ. ሰባት ጥያቄ ተገኝቷል፡፡ ለዚህ ጥያቄ 44 (75.861%) ያክል መላሾች መስማማታቸውን ሲገልጹ 14 (24.137%) የሚሆኑት ደግሞ አለመስማማታቸውን አስረድተዋል፡፡ ስለዚህ አብዛኞቹ መላሾች በውይይታቸው ወቅት ጥሩ ተግባቦት እንደነበራቸው እንረዳለን፡፡ በማስተማር ክንውኑ ላይ የተገለጸውም ይህንኑ የሚያጠናክር ነው፡፡

ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ ተጠኝ ተማሪዎች በግጥም አማካይነት አማርኛ ቋንቋን ሲማሩ ያገኙትን ጠቀሜታ በሚመለከት የሰጡትን ምላሽ እንመልከት፡፡ ከጥናቱ አላማዎች አንዱም ተማሪዎች በግጥም አማካይነት ቋንቋን ሲማሩ ምን ጠቀሜታ እንዳገኙ ማረጋገጥ ነው፡፡

ሰንጠረዥ 8፡- በግጥም አማካይነት አማርኛ ቋንቋን በመማራቸው ስላገኟቸው ጠቀሜታዎች ለማወቅ የቀረበ

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | | የስምምነት ምርጫዎች (በቁጥርና በመቶኛ) | | | ያለመስማማት ምርጫዎች (በቁጥርና በመቶኛ) | | | የሚጠበቀው አዎንታዊ(+) ወይም አሉታዊ(-) መልስ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ሀ | ለ | ድምር | ሐ | መ | ድምር | |
| 8 | የክፍልም ሆነ የቤት ስራ እንድሰራ መደረጉ በትምህርቱ ወቅት ራሴን ችዬ የመስራት ልምድ እንዳዳብር አግዞኛል ብዬ አምናለሁ፡፡ | ቁጥር | 41 | 9 | 50 | 5 | 3 | 8 | + |
| | | መቶኛ | 70.689 % | 15.517% | 86.206 % | 8.620% | 5.172 % | 13.792% | |
| 10 | አሁን በተማርኩበት ዘዴ መሰረት የቃላትን አውዳዊ ፍቺ የመለየት፣ ዐ.ነገርን በሌላ መንገድ የመጻፍ፣ ድርሰት የመጻፍ ወዘተ. መልመጃዎችን መለማመድ የቋንቋ ችሎታዬን ለማጎልበት ይጠቅመኛል፡፡ | ቁጥር | 39 | 13 | 52 | 2 | 4 | 6 | + |
| | | መቶኛ | 67.241 % | 22.413% | 89.654 % | 3.448% | 6.896 % | 10.344% | |
| 12 | በአዲስ (ፈጠራዊ) ዘዴ ቋንቋን መማር ከጀመርኩ ወዲህ የተለያዩ የፈጠራ ጽሑፎችን በጥልቀት ማንበብና መገንዘብ ችያለሁ፡፡ | ቁጥር | 27 | 20 | 47 | 10 | 1 | 11 | + |
| | | መቶኛ | 46.551 % | 34.482% | 81.033 % | 17.241 % | 1.724 % | 18.965% | |
| 13 | በዚህ አይነት ዘዴ አማርኛ ቋንቋን መማሬን ወድጄዋለሁ፡፡ | ቁጥር | 41 | 13 | 54 | 3 | 1 | 4 | + |
| | | መቶኛ | 70.689 % | 22.413% | 93.102 % | 5.172% | 1.724 % | 6.896 % | |

በስነ ጽሑፍ አማካይነት ቋንቋን መማር ተማሪዎች ሊያገኙ ከሚችሉት የቋንቋ ክሂሎች እድገት በተጨማሪ በአጠቃላይ የመማር ማስተማሩ ሂደት አያሌ ጠቀሜታዎችን ሊያገኙ ይችላሉ፡፡ እንዲሁም ተማሪዎች በመምህሩ ላይ ጥገኛ ሳይሆኑ እርስ በርስ በመወያየት ብቻ የቋንቋ ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ ያስችላል (Carter and Long, 1991, 24-25 እና Lazar, 1993, 27)፡፡ ከዚህ አኳያ ተማሪዎች ምን አመለካከት እንዳላቸው ለመረዳት የሚያስችሉ ጥያቄዎች ቀርቦላቸዋል፡፡

በዚህ መሰረትም ለጥያቄ ቁጥር ስምንት ምላሽ ከሰጡ ተማሪዎች መካከል 50 (86.206%) ያክሉ እንደሚስማሙ ገልጸዋል፡፡ እንዲሁም ለጥያቄ ቁጥር አስር 52 (89.654%) የሚሆኑ መላሾች እንደሚስማሙ አስረድተዋል፡፡ ሌላው ለጥያቄ ቁጥር አስራ ሁለት ምላሽ ከሰጡ ተማሪዎች መካከል 47 (81.033%) ያክሉ መላሾች ስምምነታቸውን አስረድተዋል፡፡ ከዚህ ባሻገር በዚህ ጥናት ለማረጋገጥ ከተፈለጉት ጉዳዮች መካከል አንዱ ‹‹ተማሪዎች በግጥም አማካይነት አማርኛ ቋንቋን ከተማሩ በኋላ የተማሩበትን ስልት መውደድ አለመውደዳቸውን ማረጋገጥ›› የሚለው ነው፡፡ ለዚህም በጥያቄ ቁጥር አስራ ሶስት ላይ ለቀረበው ጥያቄ 54 (93.102%) ያክል መላሾች መስማማታቸውን ገልጸዋል፡፡ ዘዴውን የወደዱበትን ምክንያት ለማወቅም በጥያቄ ቁጥር አስራ አምስት ላይ ‹‹ለጥያቄ ‹‹13›› የሰጠኸው/ሽው መልስ ‹‹ሀ›› ወይም ‹‹ለ›› ከሆነ ምክንያቱ ምንድነው ብለህ/ሽ ታስባለህ/ታስቢያለሽ፡፡›› በሚል ለቀረበላቸው ጥያቄ ከተሰጡት አማራጮች መካከል የሚከተለውን መልሰዋል፡፡

ሰንጠረዥ 9፡- ለመጠይቅ ጥያቄ ቁጥር 15 የተሰጠ ምላሽ

| ተ.ቁ | ለመልስ የቀረቡ አማራጮች | የመላሾች ብዛት | |
|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በመቶኛ |
| 1 | ሀ.እርስ በርስ እየተዝናናንና እየተረዳዳን እንድንማማር የሚያደርግ በመሆኑ | 19 | 32.758% |
| 2 | ለ. የመማር ማስተማር ሂደቱ በአብዛኛው በእኛ የሚከናዎን በመሆኑ | 16 | 27.586% |
| 3 | ሐ. የመማር ማስተማር ሂደቱ ባብዛኛው በመምህሩ የሚከናዎን በመሆኑ | --- | --- |
| 4 | መ. ተማሪው ትምህርቱን በስርዓት እንዲከታተል ስለሚያግዘው በክፍል ውስጥ ሊኖር የሚችለውን ረብሻና ጫጫታ የሚቀንስ በመሆኑ | 8 | 17.241% |
| 5 | ሠ. የመማር ማስተማር ዘዴው ለኛ አዲስ በመሆኑ | 10 | 22.413% |

ከሰንጠረዡ መረዳት እንደሚቻለው ተማሪዎች አዲሱን የማስተማር ዘዴ የወደዱበትን ምክንያት ሲያስረዱ ‹‹ሀ›› በማለት ምላሽ የሰጡት 19 (32.758%) ያክል ናቸው፡፡ ‹‹ለ›› በማለት ምላሽ የሰጡት 16 (27.586%) ያክል ሲሆኑ 8 (17.241%) ያክል መላሾች ደግሞ ‹‹መ›› በማለት ምላሻቸውን ሰጠዋል፡፡ እንዲሁም 10 (22.413%) የሚሆኑት መላሾች ‹‹ሠ›› የሚለውን መልስ መርጠዋል፡፡ ከዚህ በላይ ከቀረቡት የተማሪዎች ምለሾች መገንዘብ እንደሚቻለው ተማሪዎች ያለማንም ጣልቃ ገብነት በራሳቸው ተሳትፎ ቢማሩ ደስተኛ እንደሚሆኑ ነው፡፡

በሰንጠረዥ 8 ተማሪዎች ከሰጡት ምላሽ አኳያም ተማሪዎች በግጥም አማካይነት አማርኛ ቋንቋን ከተማሩ በኋላ የሰጡት ምላሽ በአላማው 5ኛ ተ.ቁ. ላይ የተጠቀሰው ንዑስ አላማ ግቡን መምታቱን የሚያረጋግጥ ነው፡፡

ሰንጠረዥ 10፡- ተጠኝ ተማሪዎች በግልም ሆነ በቡድን በግጥም አማካይነት አማርኛ ቋንቋን ሲማሩ ያልተደሰቱበት ነገር ካለ ለማወቅ ከቀረቡ ጥያቄዎች የተገኙ ምላሾች

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | | የስምምነት ምርጫዎች (በቁጥር በመቶኛ) | | | ያለመስማማት ምርጫዎች (በቁጥርና በመቶኛ) | | | የሚጠበቀው አዎንታዊ(+) ወይም አሉታዊ(-) መልስ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ሀ | ለ | ድምር | ሐ | መ | ድምር | |
| 9 | የግልም ሆነ የቡድን ስራ ተሰጥቶኝ የቃላትን አውዳዊ ፍቺ ስፈልግ፣ ዐ.ነገርን በሌላ መንገድ ስጽፍ ወዘተ. ይከብደኝ ነበር፡፡ | ቁጥር | 5 | 16 | 21 | 24 | 13 | 37 | - |
| | | መቶኛ | 8.620 % | 27.586 % | 36.206 % | 41.379 % | 22.413 % | 63.792 % | |
| 11 | እኛ እርስ በርስ እየተወያየን ከምንማማር ይልቅ ሁሉንም ትምህርት መምህሩ ቢያስተምረን የተሻለ ነው ብዬ አምናለሁ፡፡ | ቁጥር | 6 | 8 | 14 | 16 | 28 | 44 | - |
| | | መቶኛ | 10.344 % | 13.793 % | 24.137 % | 27.586 % | 48.275 % | 75.861 % | |
| 14 | አሁን በተማርኩበት ዘዴ አማካይነት በገቡበት አውድ የቃላትን ፍቺ እንድፈልግ፣ ድርሰት እንድጽፍ ወዘተ. በሚደረግበት ጊዜ ደስተኛ አልነበርኩም፡፡ | ቁጥር | 4 | 6 | 10 | 20 | 28 | 48 | - |
| | | መቶኛ | 6.896 % | 10.344 % | 17.24 % | 34.482 % | 48.275 % | 82.727 % | |

ከሰንጠረዡ ለመረዳት እንደሚቻለው ለጥያቄ ቁጥር ዘጠኝ 21 (36.206%) ያክል ተማሪዎች ስምምነታቸውን ሲገልጹ 37 (63.792%) የሚሆኑት ደግሞ አልተስማሙም። 21 (36.206%) ያክል ተማሪዎች የትምህርቱ ሂደት ይከብዳቸው እንደነበር ገልጸዋል። ይህም ቀላል የሚባል ቁጥር አይደለም። ምናልባት ይህ የሆነው ተማሪዎች ለብዙ ጊዜ ሲማሩበት ከነበረው መምህር-ተኮር ዘዴ በአንድ ጊዜ ወደ ተማሪ- ተኮር ዘዴ በመግባታቸው ሊሆን ይችላል። ይህንን ጉዳይ በሚመለከት Byren (1988፡ 4) እንደሚያስረዱት በተለይ ድርሰት መጻፍ ከስነ ልቦና፣ ከስነ ልሳንና ከአእምሯዊ ጉዳዮች ጋር ስለሚያያዝ ተግባሩ ከባድ ሊሆን ይችላል። ሆኖም ተማሪዎች ለብዙ ጊዜ የቃላት አውዳዊ ፍች መፈለግን፣ ድርሰት መጻፍን...ወዘተ. ከተለማመዱ ይህንን ችግር በቀላሉ ማስወግድ ይቻላል። በዚህ ረገድ ተጠኝ ተማሪዎችም ያረጋገጡት ይህንን ነው። ምክንያቱም በቅድመ ትምህርት ፈተናው የነበራቸው ደካማ የድርሰት መጻፍ ችሎታ በትምህርቱ ሂደት ግን መሻሻል በማሳየት ጥሩ ድርሰቶችን መጻፍ ችለዋልና። ከዚህ ባሻገር በአጠቃላይ መማር ማስተማሩን አስመልክቶ ጥያቄ ቁጥር 17 ላይ ለቀረበላቸው ጥያቄ ተማሪዎች የሰጡት አስተያየት ከላይ ለቀረበው ሀሳብ ደጋፊ ነው። ተማሪዎች ከሰጡት አስተያየት መካከል የአንዱን ቀጥለን እንመልከት። ‹‹በመጀመሪያ በዚህ መልኩ አማርኛን ስንማር ግራ ገብቶኝ ነበር። ለመልመድም እኔ ተቸግሬ ነበር። በኋላ ብዙ እየተለማመድን በሄድን ቁጥር ግን በጣም እየወደድኩት መጣሁ። ስለዚህ ጥሩ ዘዴ ነው ወድጀዋለሁ።›› ስለዚህ የተማሪዎችን ለዘዴው አዲስ መሆን በተደጋጋሚ እንዲለማመዱ በማድረግ ማስወገድ እንደሚቻል ከአስተያየቱ መገንዘብ ይቻላል።

ከዚህ ሌላ ለጥያቄ ቁጥር አስራ አራት 10 (17.24%) የሚሆኑ መላሾች አለመስማማታቸውን ገልጸዋል። 48 (82.727%) ያክሉ ደግሞ ስምምነታቸውን አስረድተዋል። መስማማታቸውን ለገለጹት ተጠኝዎች ደግሞ በጥያቄ ቁጥር አስራ ስድስት ላይ ‹‹ለጥያቄ ተ.ቁ ‹‹14›› የሰጠኸው/ሽ መልስ ‹‹ሀ›› ወይም ‹‹ለ›› ከሆነ ምክንያቱ ምንድን ነው ብለህ/ሽ ታስባለህ/ታስቢያለሽ።›› የሚል ጥያቄ ቀርቦላቸው ነበር። ለዚህም የሰጡት ምላሽ ተከታዩን ይመስላል።

ሰንጠረዥ 11፡- ለመጠይቅ ጥያቄ ‹‹16›› የተሰጠ ምላሽ

| ተ.ቁ | ለመልስ የቀረቡ አማራጮች | የመላሾች ብዛት | |
|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በመቶኛ |
| 1 | ሀ. የትምህርቱ ሂደት ባብዛኛው በመምህሩ የሚመራ በመሆኑ | --- | --- |
| 2 | ለ. የትምህርቱ ሂደት ተማሪውን የሚያሳትፍ በመሆኑ | --- | --- |
| 3 | ሐ. ቀደም ሲል የምማርበት የትምህርት ሂደት ሁሉም ነገር በመምህሩ መሪነት የሚከናዎን በመሆኑ | 10 | 13.488% |
| 4 | መ. በቡድንም ሆነ ክፍሉ በሙሉ በሚያደርገው ውይይት የተነሳ የክፍሉ ጸጥታ የሚደፈርስ በመሆኑ | 14 | 18.883% |

ከዚህ ሰንጠረዥ መረዳት እንደሚቻለው ለጥያቄው መልስ የሰጡት 24 (32.371%) ያክሉ ብቻ ናቸው፡፡ ከነዚህ መካከልም 14 (18.883%) ያክሉ ‹‹መ››ን መርጠዋል፡፡ ይህንን በሚመለከት ትምህርቱ ከመጀመሩ በፊት በነበረው የትውውቅ ወቅት ትምህርቱ በአብዛኛው በጋራ ውይይት የሚካሄድ በመሆኑ ድምጻቸውን ዝቅ አድርገው በመወያየት በድምጽ ብዛት ሊከሰት የሚችለውን ረብሻ መቀነስ እንደሚገባ ተነግሯቸው ነበር፡፡ ነገር ግን ትምህርቱ እንደተጀመረ አካባቢ ለዘዴው አዲስ በመሆናቸው ጭምር በውይይታቸው ወቅት ከፍተኛ ድምጽ ስለሚሰማ ይረብሽ ነበር፡፡ በኋላ ላይ እየተለማመዱ ሲመጡ ግን ድምጻቸውን በመቀነስ መወያየት በመጀመራቸው ችግሩ ሊቀረፍ ችሏል፡፡ ይህንን ጉዳይ በሚመለከትም Byren (1988፡ 33-35) እና Harmer (1990፡206-207) የሚከተለውን ብለዋል፤ በክፍል ውስጥ ያሉት ተማሪዎች በቡድን ሆነው በሚወያዩበት ጊዜ ድምጻቸው ከፍተኛ ይሆናል፡፡ ሁኔታውን እየተለማመዱት በሄዱ ቁጥር ግን ድምጻቸውን ዝቅ አድርገው መወያየትን ይለማመዳሉ፡፡

ከዚህ በመቀጠል ደግሞ በመጠይቁ ጥያቄ ቁጥር አስራ ሰባት ላይ ለቀረበው ጥያቄ ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ እንደሚከተለው ተተንትኖ ቀርቧል፡፡

ጥያቄ ቁጥር አስራ ሰባት ‹‹በአጠቃላይ በመማር ማስተማሩ ወቅት ስላገኘኸው/ሽው አዲስ የመማር ማስተማር ስልት ተጨማሪ አስተያየት ካለህ/ሽ ግለጽ/ጭ፡፡›› በሚል የቀረበ ነበር፡፡ ለዚህ ጥያቄ አብዛኞቹ ተጠኝ ተማሪዎች ጠቃሚ የሆኑ አስተያየቶችን ሰንዝረዋል፡፡

ተማሪዎቹ የሰጧቸው አስተያየቶች በአጠቃላይ ሲታዩ የመማር ማስተማሩን ሂደት እንደወደዱት፣ የትምህርት አሰጣጡ አዝናኝና ሳቢ እንዲሁም አሳዋቂ እንደነበር፣ የእነሱንም የተሳትፎ ደረጃ ከፍ ያደረገና እርስ በእርሳቸውም እንዲግባቡ ያደረገ እንደነበር የሚያስረዱ ናቸው፡፡ የሁሉንም ተማሪዎች አስተያየት በዚህ ትንተና ላይ ማካተት አስቸጋሪ በመሆኑ ለናሙናነት የሚሆኑ አስተያየቶች ከዚህ በመቀጠል በመልክ በመልካቸው እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

ሀ. የተማሪዎችን ተሳትፎና የማንበብ ባህል የሚያሳድግ መሆኑን በተመለከተ የተሰነዘሩ አስተያየቶች

‹‹ይህ የተማርንበት መንገድ የተለያዩ ጽሑፎችን እንዳነብ ገፋፍቶኛል፡፡ ስለዚህ የተማርንበትን ዘዴ ወድጀዋለሁ፡፡›› በማለት አንድ ተማሪ አስተያየቱን ሰጧል፡፡ በሌላ በኩል የትምህርቱን አሳታፊነት በሚመለከት ደግሞ አንድ ተማሪ ‹‹እርስ በእርሳችን እየተወያየን እንድንማር በመደረጉ ሁሉም ተማሪ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆን አድርጓል፡፡›› ሲል ጽፏል፡፡

ለ. ድርሰት የመጻፍና የማንበብ ችሎታን የሚያሳድግ መሆኑን በተመለከተ የተሰጡ አስተያየቶች

ከአስተያየት ሰጪ ተማሪዎች መካከል አንዱ ይህንን ጉዳይ በሚመለከት እንዲህ ብሏል፤ ‹‹በመማር ማስተማሩ ሂደት ግጥሞችን እንድናነብ መደረጉ በጣም ጠቃሚ ነው፡፡ ምክንያቱም ግጥሞች ሳቢ በመሆናቸው ለማንበብ ያለንን ፍላጎት አሳድገውታል፡፡ በተጨማሪም ድርሰት የመጻፍ ፍላጎቴን ቀስቅሰውታል፡፡›› ሌላ ተማሪ በበኩሉ፤ ‹‹ድርሰት የመጻፍ ፍላጎት አልነበረኝም፡፡ አሁን ግን ይህንን ትምህርት ከተማርኩ ወዲህ የመጻፍ ፍላጎቴ ተነሳስቷል፡፡›› ሲል ጽፏል፡፡

ከነዚህ ሁለት አስተያየቶች እንደምንረዳው በግጥም አማካይነት አማርኛ ቋንቋን ከተማሩ በኋላ ተማሪዎች ድርሰት የማንበብና የመጻፍ ፍላጎታቸው ጨምሯል፡፡ ፍላጎቱ የሌላቸውም ተማሪዎች ጭምር ለማንበብና ለመጻፍ ተነሳሽነት አሳይተዋል፡፡ ይህንን እውነታ ይበልጥ የሚያረጋግጠው ደግሞ በቅድመ ትምህርት ፈተናው ወቅት ድርሰት እንዲጽፉ የሚያዝዙ ጥያቄዎችን ብዙ ተማሪዎች አልሰሩም ነበር፡፡ ነገር ግን በትምህርቱ ሂደት ሁሉም ተማሪዎች ድርሰት ለመጻፍ ጥረት አድርገዋል፤ የተሻሉ የተባሉ

ድርሰቶችም በአባሪ መልክ ተያይዘው ቀርበዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በድህረ ትምህርት ፈተናው ለቀረቡት የድርሰት ጻፍ ጥያቄዎች ሁሉም ተማሪዎች የሚችሉትን ያክል ሙከራ አድርገዋል፡፡ ለዚህ ማስረጃ ይሆኑ ዘንድም በቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናዎች ከተጻፉ ድርሰቶች መካከል ለናሙና የሚሆኑ ድርሰቶች በአባሪ መልክ ተያይዘው ቀርበዋል፡፡ (አባሪ አስራ አንድ ‹‹ሀ›› እና ‹‹ለ››ን ገጽ 115 እና 116 ይመልከቱ)

ሐ. ከነባሩ የማስተማር ዘዴ ጋር በማወዳደር የተሰጡ አስተያየቶች

‹‹የትምህርት አሰጣጡ በፊት ከነበረው በጣም የተሻለ ነው፡፡ ምክንያቱም እየተዝናናን ነበር የተማር ነው፡፡›› በማለት አንድ ተማሪ አስተያየቱን ሰጧል፡፡ ሌላኛው ደግሞ ‹‹ብዙ ተማሪ አማርኛን መማር አይወድም ነበር፡፡ ትምህርቱ በዚህ መልኩ ከተሰጠ ግን ሁሉም ተማሪ እንደኔ መማር ይወዳል ብዬ አስባለሁ፡፡›› ሲል አስተያየቱን ሰንዝሯል፡፡ ከነዚህ አስተያየቶች እንደምንገነዘበው ተማሪዎች በነባሩ ዘዴ መማራቸውን እንደማይወዱት ነው፡፡

መ. የተማሪና መምህር ግንኙነትን በተመለከተ የተሰጡ አስተያየቶች

ይህንን ጉዳይ በተመለከተ አንድ ተማሪ ‹‹አንተ ስታስተምረን እንዝናናለን፡፡ እና ትምህርቱን ወደነዋል፡፡›› በማለት አስተያየቱን ለግሷል፡፡ ሌላኛው በበኩሉ ‹‹ለእኛ ነጻነት ሰጠኸን ስለምንወያይ እንዳንፈራ አድርገኸናል፡፡›› ሲል አስተያዩቱን ሰጧል፡፡

ሠ. የትምህርቱ ሂደት የቡድን ስራን የሚያዳብርና በራስ መተማመንን የሚያጎለብት መሆኑን በተመለከተ የተሰነዘሩ አስተያየቶች

‹‹ትምህርቱ በጣም ጥሩ ነው፡፡ ምክንያቱም ብዙ ስራዎችን በቡድን ሆነን ስለምንሰራ የማናውቃቸውን ነገሮች ከሌሎች እንድናውቅ አድርጎናል፡፡›› አንድ ተማሪ የሰጠው አስተያየት ነው፡፡ በሌላ በኩል አንድ ተማሪ ደግሞ እንዲህ ብሏል፤ ‹‹በትምህርቱ ብዙ ነገር ተምሬያለሁ፡፡ የማንበብ ልምዴ ጨመሯል፣ የመጻፍ ችሎታዬም አድጓል፡፡ ከዚህ በላይ ግን ብዙ እንድንወያይ ስለተደረገ ሳልፈራ ሀሳቤን መግለጽ እንድችል አድርጎኛል፡፡››

ከነዚህ አስተያየቶች መገንዘብ የምንችለው፣ የትምህርቱ ሂደት ተማሪዎችን በጋራ የሚያወያይ፣ የሚያከራክር እንዲሁም የሚያሳትፍ በመሆኑ ሀሳባቸውን ያለምንም ፍርሀት እንዲገልጹ እንዳስቻላቸው ነው፡፡ በዚሁ ምዕራፍ ላይ እንደተጠቀሰው በስነ ጽሑፍ

ቋንቋን ማስተማር ክሂሎችን ከማሳደጉም ባሻገር ሌሎች ተጨማሪ ጠቀሜታዎችም አሉት፡፡ የተማሪዎች አስተያየትም ይህንን እውነታ የሚደግፍ ነው፡፡

ከዚህ በላይ ከ‹‹ሀ›› - ‹‹ሠ›› የቀረቡት አስተያየቶች የመማር ማስተማሩ ሂደት መልካም እንደነበር የሚያመለክቱ ናቸው፡፡ ነገር ግን የተወሰኑ ተማሪዎች ደግሞ በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ አሉ ያሉትን ድክመት የሚያሳዩ አስተያየቶችን ሰጠዋል፡፡ ተማሪዎቹ ከጠቀሷቸው ድክመቶች መካከል በትምህርቱ መጀመሪያ አካባቢ በውይይቶች ወቅት ተከስቶ የነበረውን ጫጫታ በሚመለከትና ትምህርቱ ከሀገር አቀፍ ፈተና ይዘት ጋር አለመጣጣሙን በማስመልከት የተሰጡ አስተያየቶች ዋነኞቹ ናቸው፡፡ እነዚህም እንደሚከተለው ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

ረ. በትምህርቱ ወቅት የሚፈጠረውን ጫጫታ በተመለከተ የተሰነዘሩ አስተያየቶች

ከአንድ ተማሪ የተገኘው አስተያየት እንዲህ ይላል፤ ‹‹ትምህርቱ ጥሩ ነው፡፡ ግን ስንወያይ ጫጫታ ስለሚፈጠር ለመደማመጥ አልቻልንም ነበር፡፡›› ሌላኛው በበኩሉ ‹‹እንዲህ አይነት ነገር አይተን ስለማናውቅ እድሉን ስናገኝ ከመጠን በላይ እንንጫጫለን፡፡ መጀመሪያ አካባቢ መደማመጥ አልችል ብለን ነበር፡፡›› የሚል አስተያየቱን ሰንዝሯል፡፡ ከነዚህ ሁለት አስተያየቶች እንደምንረዳው በጋራ በሚሰሩበት ወቅት ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ስለሚወያዩ ይረብሻል፡፡ ለዚህ ደግሞ በዚሁ ምዕራፍ ላይ እንደተባለው ተማሪዎቹ እርስ በእርስ እየተግባቡ ሲሄዱ ጫጫታው እየቀነሰ ይሄዳል፡፡ ይህም በትምህርቱ ሂደት የታየ ነው፡፡

ሰ. ትምህርቱ የሀገር አቀፍ ፈተናን ታሳቢ አድርጎ እንዲሰጥ የሚያሳስቡ አስተያቶች

‹‹እንደዚህ አይነት ትምህርት ብቻ ከምንማር ይልቅ ለማትሪክ ፈተና የሚረዱን ትምህርቶች ቢሰጡን ይሻላል፡፡ ዋናው የማትሪክ ፈተና ነው፡፡›› የሚል የአንድ ተማሪ አስተያየት አለ፡፡ ሌላኛው ደግሞ እንዲህ ብሎ ጽፏል፤ ‹‹የሰዋስው ትምህርቶች በርከት ብለው ቢሰጡን የተሻለ ነው፡፡ ለማትሪክ ፈተና የሚጠቅመን እሱ ነው፡፡››

ከነዚህ አስተያየቶች መረዳት እንደሚቻለው እነዚህን አስተያየቶች የሰጡት ተማሪዎች ይህ ለሙከራ የተካሄደው ትምህርት ዓመቱን ሙሉ የሚቀጥል ነው የመሰላቸው፡፡ ነገር ግን የዚህ ጥናት አላማ ተማሪዎች በግጥም አማካይነት አማርኛ ቋንቋን ቢማሩ የአንብቦ መረዳትና ጽሕፈት ክሂላቸው ያድግ እንደሆነ በሙከራ ማረጋገጥ ነው፡፡ ስለሆነም ዓመቱን

ሙሉ እንዲህ አይነት ትምህርት ሊሰጣቸው አይችልም፡፡ ምክንቱም መርሀ ትምህርቱ በቋንቋ ክሂሎች ላይ ብቻ ሳይሆን በዕውቀት ዘርፎች ላይም የተመሰረተ ስለሆነ ሁሉንም አይነት ትምህርት በመማር ለሀገር አቀፍ ፈተናው ዝግጁ መሆን ይችላሉ፡፡ እነዚህ ከላይ በ‹‹ረ›› ና ‹‹ሰ›› ስር የቀረቡት አስተያየቶች በጥናቱ አላማ ቁጥር 6 ላይ ከቀረበው ንዑስ አላማ ጋር የሚጣጣሙ ናቸው፡፡ ይኸውም ‹‹በፈጠራዊ ዘዴ በግጥም አማካይነት አማርኛ ቋንቋን በማስተማር ሂደት የሚያጋጥሙ መሰናክሎችን ለይቶ በማውጣት መፍትሄ መፈለግ›› የሚል ንዑስ አላማ ነበር፡፡ በመሆኑም ለጥያቄ ቁጥር 17 ተጠኚ ተማሪዎች የሰጡት በ‹‹ረ›› እና ‹‹ሰ›› ስር የቀረቡት አስተያየቶች ይህ አላማ ግቡን መምታቱን የሚያሳዩ ናቸው፡፡

በአጠቃላይ ከቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናዎች ውጤትና ከጽሑፍ መጠይቁ የተገኙ መረጃዎች ጥናቱ ይዞት የተነሳውን አላማ ከግብ ለማድረስ ያስቻሉ ናቸው፡፡ ምክንያቱም መረጃዎቹ ከአላማዎቹ ጋር የተጣጣሙ ናቸውና፡፡ ከነዚህ ትንታኔዎች በመነሳት በሚቀጥለው ምዕራፍ ማጠቃለያና አስተያየቶች ቀርበዋል፡፡

87

# ምዕራፍ አምስት

# 5.ማጠቃለያና አስተያየት

## 5.1 ማጠቃለያ

የአማርኛ ቋንቋ አንብቦ መረዳትና ጽሕፈት ችሎታን ለማስተማር ግጥም ያለውን ሚና በሙከራ ማረጋገጥ የዚህ ጥናት ዋነኛ አላማ መሆኑ በምዕራፍ አንድ ላይ ተጠቅሷል። ከዚህ ዋነኛ አላማ የተቀዱ ሌሎች ንዑሳን አላማዎችም ቀርበዋል። በምዕራፍ ሶስት ላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ደግሞ ጥናቱ ይሂቸው የተነሳቸውን አላማዎች ከግብ ለማድረስ የቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናዎችና የጽሑፍ መጠይቅ እንዲሁም ኢ. መደበኛ ቃለመጠይቅ በመረጃ መሰብሰቢያነት አገልግለዋል። የተሰበሰቡ መረጃዎችንም በስታትስቲካዊ ዘዴና በገለጻ ስልት ለመተንተን ተሞክሯል። መረጃዎቹ ተሰብስበው በተደረገው ትንተናም ጥናቱ ይሂቸው የተነሳቸው አላማዎች ግባቸውን መምታት ችለዋል። በመሆኑም በዚህ ጥናት የተገኙ ውጤቶች (ግኝቶች) በአጭሩ እንደሚከተለው ቀርበዋል።

በምዕራፍ አራት ላይ ከተደረገው ትንተና ለማየት እንደሚቻለው ምንም ሳይማሩ ለተማሪዎች በተሰጠው የቅድመ ትምህርት ፈተና ውጤት መሰረት ሁለቱም ቡድኖች ($9^{25}$ እና $9^{29}$) ተቀራራቢ የሆነ አጠቃላይ ውጤት አስመዝግበዋል። በየቡድኖቹ ያሉት ተማሪዎች ያስመዘገቡት ውጤት ተደምሮ ለተማሪዎቹ ብዛት በማካፈል በተገኘው ውጤት መሰረትም የ$9^{25}$ ክፍል አማካይ ውጤት 37.229 ሲሆን የ$9^{29}$ አማካይ ውጤት ደግሞ 37.9023 ነው። ይህንን አማካይ ውጤት እንዲሁም መደበኛ ልይይቱን በመያዝ በተደረገው የቲ- ቴስት ስሌት መሰረት የቲ-ስሌት ዋጋው 0.310 ሲሆን በ0.05 የጉልህነት ደረጃ በ114 የነጻነት ደረጃ የቲ-ሰንጠረዥ ዋጋ 1.6645 ሆኗል። ስለዚህ የተገኘው የቲ- ስሌት ዋጋ (0.310) ከቲ-ሰንጠረዥ ዋጋ (1.6645) በማነሱ በተማሪዎች የቅድመ ትምህርት ፈተና ውጤት መካከል የጎላ ልዩነት እንደሌለ ይጠቁማል። ከዚህ በኋላም ለሁለቱ ቡድኖች በተመሳሳይ ግጥሞች፣ በተለያዩ ዘዴዎችና መምህራን ለአራት ሳምንታት ትምህርት ከተሰጠ በኋላ የድህረ ትምህርት ፈተና ተሰጧል።

በድህረ ትምህርት ፈተናውም የእያንዳንዱ ተማሪ ውጤት ተደምሮ ለተማሪዎች ብዛት በማካፈል በተገኘው አማካይ ውጤት መሰረት የ$9^{25}$ ክፍል 51.6207 አማካይ ውጤት ያገኘ

ሲሆን የ9[29] ክፍል ደግሞ 80.29094 አማካይ ውጤት አግኝቷል፡፡ ይህን አማካይ ውጤት መሰረት በማድረግና የተገኘውን መደበኛ ልይይት በመያዝ በተደረገው የቲ- ቴስት ስሌት የቲ- ስሌት ዋጋው 12.900 ሲሆን በ0.05 የጉልህነት ደረጃ በ114 የነጻነት ደረጃ የቲ-ሰንጠረዥ ዋጋ 1.6645 ሆኗል፡፡ ይህ የተገኘው የቲ- ስሌት (12.900) ውጤት ከቲ-ሰንጠረዥ ዋጋው (1.6645) በእጅጉ የበለጠ ሆኗል፡፡ ይህ ውጤትም በተጠኚነት የተያዙት የ9[29] ክፍል ተማሪዎች የተሻለ ውጤት ማስመዝገባቸውን ያመለክታል፡፡ ይህ ውጤት የተገኘውም ነጻ ተለዋዋጭ በሆነው ግጥምን ተጠቅሞ አማርኛ ቋንቋን በማስተማር እንጂ በዘፈቀደ አይደለም፡፡ Hill (1986፡ 37) እና Collie and Slater (1987፡ 18) በፈጠራ ጽሑፎች አማካይነት ቋንቋን ማስተማር የቋንቋ ክሂሎችን ያዳብራል ካሉት ሀሳብ ጋር ይህ የተገኘው ውጤት የሚጣጣም ነው፡፡

ከቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናዎች ውጤት ትንተና ባሻገር ከተጠኚ ተማሪዎች በተገኙ የመጠይቅ ምላሾች ላይ ትንተና ተደርጓል፡፡ በትንተናው መሰረትም በግጥም አማካይነት የአማርኛ ቋንቋን በፈጠራዊ ዘዴ በመማራቸው ተማሪዎች ደስተኞች ናቸው፡፡ ከዚህ ባለፈ የቃላትን አውዳዊ ፍች የመፈለግ፣ ድርሰት የመጻፍ፣ በተሰጡ ቃላትና ሀረጋት አማካይነት ዐ.ነገሮችን የመጻፍ ወዘተ. ችሎታቸው በከፍተኛ ሁኔታ ማደጉን የጥናቱ ግኝት ያመለክታል፡፡

በግጥም አማካይነት በፈጠራዊ ዘዴ አማርኛ ቋንቋን ማስተማር ክሂሎችን ከማሳደጉም ባሻገር ሌሎች ጠቀሜታዎች እንዳሉትም የጥናቱ ግኝት አመላክቷል፡፡ ማለትም እርስ በርስ እየተጋገዙ መስራትን፣ በራስ መተማመንን፣ ያለፍርሀት ሀሳብን ለሌሎች ማስረዳትን ወዘተ. በከፍተኛ ሁኔታ እንዳሳደገላቸው ተጠኚ ተማሪዎች ከሰጡት ምላሽ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

## 5.2 አስተያየት

ቋንቋን በማስተማር ሂደት የተዋጣለትና ምትክ የሌለው የማስተማሪያ ዘዴ እንደሌለ የመስኩ ምሁራን ያስረዳሉ፡፡ እንደ Hill (1986፡ 87) እና Celce — Murcia (1991፡ 55) ገለጻም ይኸኛው የማስተማሪያ ዘዴ የተዋጣለት ነው ብሎ መናገር አይቻልም፡፡ ምክንያቱም ሁሉም ዘዴ የየራሱ ድክመትና ጥንካሬ አለውና፡፡ ከዚህ ይልቅ እንደየ ሁኔታዎቹ ምቹ የሆኑ ዘዴዎችን መጠቀም ይመከራል፡፡ በዚህ ጥናት የተተገበረው

ፈጠራዊ ዘዴም በሁሉም ደረጃ የተሟላ ነው ብሎ መናገር ባይቻልም የተሻለ ዘዴ እንደሆነ የጥናቱ ግኝት አመላክቷል፡፡ በመሆኑም ከዚህ ጥናታዊ ጽሑፍ ውጤት በመነሳት የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ይበልጥ ሳቢና ተወዳጅ እንዲሆን ያደርጋሉ የተባሉ አስተያየቶች ከዚህ እንደሚከተለው ይቀርባሉ፡፡

1. የተማሪዎችን የቋንቋ ክሂሎች ለማሳደግ ስነ ጽሑፍን በመጠቀም ማስተማር የጎላ ጠቀሜታ አለው፡፡ ሆኖም እነዚህን ክሂሎች ለማስተማር የቋንቋ ህግን ብቻ የማስተማር ሁኔታ በሰፊው ይታያል፡፡ ከዚህ ይልቅ ከተማሪዎች አጠቃላይ ሁኔታ ጋር የተመጣጠኑ የፈጠራ ጽሑፎችን በመጠቀም ማስተማር ተመራጭ ነው፡፡ ስለሆነም የቋንቋ መምህራን የስነ ጽሑፍ ስራዎችን ተጠቅመው አማርኛ ቋንቋን ቢያስተምሩ መልካም ነው፡፡ ምክንያቱም በዚህ መንገድ የሚማሩ ተማሪዎች ጠባቂ ብቻ ሳይሆኑ ራሳቸውም ፈጣሪ ይሆናሉና፡፡
2. በቋንቋ ትምህርት ተማሪዎችን አሳታፊ የሆነ ተማሪ- ተኮር ዘዴ መከተል ይበልጥ ተመራጭ እንደሆነ ታምኖበት በፖሊሲ ደረጃ አለ፡፡ ሆኖም አንዳንድ መምህራን ላይ መምህር- ተኮር የማስተማር ዘዴን የመከተል ሁኔታ ይታያል፡፡ የማስተማር ዘዴው መምህር- ተኮር ከሆነ የተማሪዎች ተሳትፎ የተገደበ ይሆናል፣ በራሳቸው የመስራት ፍላጎታቸውም ይዳከማል፡፡ስለዚህ መምህራን ተማሪ አሳታፊ በሆነ መልኩ ቢያስተምሩ፡፡
3. በየኮሌጆቹ እየሰለጠኑ ያሉ የቋንቋ ተማሪዎች ከፈጠራዊ ዘዴ ጋር እንዲተዋወቁ ቢደረግ፣ እንዲሁም ለነባር መምህራን የተለያዩ ስልጠናዎችን በማዘጋጀት ከዚህ ዘዴ ጋር እንዲተዋወቁ ቢደረግ ጥሩ ነው፡፡
4. የመማሪያ መጻሕፍት አዘጋጆች፣ የስርዓተ ትምህርት ቀራጮች እና ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት በስነ ጽሑፍ ቋንቋን ለማስተማር የሚያስችሉ ይዘቶችን በሚያዘጋጇቸው የትምህርት መሳሪያዎች ውስጥ ቢያካትቱ ጥሩ ነው፡፡
5. የሀገራችን በርካታ ትምህርት ቤቶች ካሉባቸው በርካታ ችግሮች መካከል የክፍል ጥበትና የመቀመጫ ወንበሮች ምቹ አለመሆን ይጠቀሳሉ፡፡ በርካታ ተማሪዎች በጠባብ ክፍል ውስጥ የሚገኙ ከሆነ መምህራን ተማሪዎቻቸው የሚካሄዱትን ውይይት እንደልብ እየተዘዋወሩ ለመከታተል አያመችም፡፡ ከዚህ ባሻገር ለመቀመጫነት የሚያገለግሉት ወንበሮች በቀላሉ የማይንቀሳቀሱና የቡድን ስራ ለመስራትም የማይመቹ ናቸው፡፡ ስለሆነም በየክፍሉ የሚመደቡት ተማሪዎች

የተመጠኑ ቢሆኑና ወንበሮቹም ለውይይት ይመች ዘንድ በቀላሉ የሚንቀሳቀሱ ሆነው ቢሰሩ መልካም ነው፡፡

በአጠቃላይ ከዚህ በላይ ከቀረቡት አስተያቶች ውጪ ሌሎችም አስተያየቶች ሊኖሩ እንደሚችሉ የዚህ ጥናት አጥኚ ያምናል፡፡

# ዋቢ ጽሑፎች


ሰለሞን ደሬሳ:: 1963:: *ልጅነት::* አዲስ አበባ፡ ሀሌ መጻሕፍት::

በዕውቀቱ ስዩም:: 1995:: *ኗሪ አልባ ጎጆዎች::* አዲስ አበባ፡ ቅድስተ ማርያም ማተሚያ ቤት::

___________:: 1999:: *እንቅልፍና እድሜ::* ቦስተን፡ ደረኮ አሳታሚ::

በድሉ ዋቅጅራ። 1996:: *በስነ ጽሑፍ ቋንቋን ማስተማር::* አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት።

ብርሀኑ ገበየሁ:: 1999:: *የአማርኛ ስነ ግጥም::* አዲስ አበባ፡ አልፋ አሳታሚዎች::

ተስፋዬ ሸዋዬ:: 1981:: ስነ ልሳንና ቋንቋን ማስተማር:: አዲስ አበባ፡ (ያልታተመ)

አያልነህ ሙላት:: 1989:: *ማን ይሆን የበላ?::* አዲስ አበባ፡ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት::

ክንፈሚካኤል ሱጋ:: 1995:: ‹‹ስነ ጽሑፋዊ ይዘቶች የተማሪዎችን የቋንቋ ክሂልና የስነ ጽሑፍ እውቀት ለማሳደግ ያላቸው እገዛ በ1993ና በ1994 ዓ.ም ለ10ኛ እና 11ኛ ክፍል መማሪያነት በተግባር ላይ በዋሉ መጻህፍት››:: ለ2ኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ:: አዲስ አበባ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል፣ አ.አ.ዩ.:: (ያልታተመ)

ውዳላት ገዳሙ:: 1996:: *እናትና ልጅ::* አዲስ አበባ፡ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት::

ዘመንፈስ ባራኪ:: 1991:: ‹‹በስነ ጽሑፍ አማካይነት አማርኛ ቋንቋን በማስተማር የአጭር ልቦለድ ሚና፤ በ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ጥናት››:: ለ2ኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ:: አዲስ አበባ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽ ሑፍ ትምህርት ክፍል፣ አ.አ.ዩ.:: (ያልታተመ)

ዘሪሁን አስፋው። 1992። *የስነ ጽሁፍ መሰረታዊያን።* አዲስ አበባ፡ ንግድ ማተሚያ ቤት።

ያለው እንዳወቀ:: 1998:: *የምርምር መሰረታዊ መርሆችና አተገባበር::* አዲስ አበባ፡ አልፋ አታሚዎች::

ዮናስና ሌሎች:: 1966:: ‹‹አማርኛ ለኮሌጅ ደረጃ የተዘጋጀ››:: የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል፣ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርሲቲ:: (ያልታተመ)

ዳዊት ፍሬሕይወት፡፡ 2000፡፡ ‹‹በቤኒሻንጉል ጉሙዝና በጋምቤላ ክልሎች ለመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ እርከን (7ኛና 8ኛ ክፍል) ተማሪዎች በተዘጋጁ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱ ስነ ጽሑፋዊ ስራዎች አመራረጥና አደረጃጀት››፡፡ ለ2ኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፡፡ አዲስ አበባ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል፣ አ.አ.ዩ.፡፡ (ያልታተመ)

ጌትነት ታፈረ፡፡ 1998፡፡ ‹‹ልቦለድን በመጠቀም በክፍል ውስጥ የአንብቦ መረዳት ትምህርት አቀራረብ ፍተሻ፤ በትግራይ ክልል፣ማዕከላዊ ዞን፣ በተመረጡ አራት ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ላይ የተካሄደ ጥናት››፡፡ ለ2ኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፡፡ አዲስ አበባ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል፣ አ.አ.ዩ.፡፡ (ያልታተመ)

ጌትነት አዲስ፡፡ 2001፡፡ ‹‹በረጅም ልቦለድ ቅንጫቢ አማርኛ ቋንቋን ማስተማር ያለው ውጤታማነት በተመረጠ አንድ የምስራቅ ጎጃም ዞን ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ጥናት››፡፡ ለ2ኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፡፡ አዲስ አበባ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል፣ አ.አ.ዩ.፡፡ (ያልታተመ)

ጌትነት እንየው፡፡ 2004፡፡ *እውቀትን ፍለጋ፡፡* አዲስ አበባ፡ አልፋ አሳታሚዎች፡፡

ጸጋዬ ገ/መድህን፡፡ 1966፡፡ *እሳት ወይ አበባ፡፡* አዲስ አበባ፡ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፡፡

ፈቃደ አዘዘ፡፡ 1991፡፡ ‹‹አንዳንድ ነጥቦች ስለ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አላማዎች፣ ስለ መማሪያ መፃህፍትና ስነ ጽሑፍ ሚና በቋንቋ ትምህርት (1944-1983)››። ለቋንቋዎች ጥናት ተቋም ዘጠነኛ ዓመታዊ ሴሚናር የቀረበ፣ አ.አ.ዩ

Atkins,J. et al.. 1996. *College English: Instructors Manual* . Addis Ababa: AAU.

Brumfit, C.J. and Carter, R.A.. (eds). 1986. *Literature and Language teaching.* Oxford: OUP.

Byren, D. 1988. *Teaching Writing skill.* London: Longman group UK Limited.

Carter, R.. 1986. *Language, Literature and Learner.* New York: Longman Ltd

Carter, R. and Long, M.N.. 1991. *Teaching Literature.* London: Rutledge.

Celce- Murcia, M. 1991. *Teaching English as a Second or Foreign Language*. Boston: Heiland Heinle publisher.

Collin, J. and Slater. 1987. *Literature in the Language Classroom.* Cambridge. CUP.

Davies, A. 1988. "Communicative Language Teaching." in Arthur Hughes (ed). *Testing English for university study.* (pp. 5 — 15). Hong Kong: Modern English publication in association with the British council.

Dyer, C.. 1995. *Beginning Research in Psychology: A Practical Guide to Research Methods and Statistics.* Oxford: Balck Well.

Harmer, J.. 1990. *Begning Research in Psychology: A Practical Guide to Research Methods and Statistics*. Oxford: OUP.

Hatch, E. and H. Farhaday. 1982. *Research Design and Statistics for Applied Linguistics*. Cambridge: Newbury house publishers:

Hill, J.. 1986. *Using Literature in Language Teaching.* London: Macmillan Publishers Ltd.

Ibsen, E.. 1995. ‹‹The Double Role of Fiction in Foreign Language Teaching Towards A Creative Methodology››. *In Selected Articles from the English Teaching Fourm.* By Thomas ed. Washington D.C. USA.

Lazar, G.. 1993. *Literatue and Langauge Teaching*. Cambridge: CUP.

Mckay, S.. 1986. ‹‹Literature in Language Classroom.›› In Brumfit, C.J. and R.A. Carter (eds). *Literature and Langauge Teaching.* Hong kong: Educational Law-priced Books Scheme with Oxford University Press.

McRae, J.. 1991. *Literature with a Sall.* Hong Kong: Macmillan publisher.

Nuttall, C.. 1982. *Teaching Reading Skills in a Foreign Language*. London: Heineman Education Book.

Silberstein, S.. 1994. *Techniques and Resources in Teaching Reading.* Oxford: OUP.

Short. 1995. Exploring the Language and Prose. London: Longman.

Walker, R.. 1983. *Language for Literature: A Guide to Language Use, Style and Criticism.* Great Britain: Scotprint Ltd.

Widdowson, H.G.. 1975. *Stylistic and Teaching of Literature*. Hong Kong: Longman

William, R.. 1991. *Reading in the Language Classroom.* Hong kong, Macmillan Publishers Ltd.

# አባሪዎች

አባሪ አንድ

## በደምበጫ ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ለሚማሩ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀ የቅድመ ትምህርትና ድህረ ትምህረት የአማርኛ ቋንቋ ፈተና

አጠቃላይ መመሪያ

ይህ የቅድመ ትምህርት ፈተና ከሁለት ግጥሞች የተዘጋጁ ጥያቄዎችን ያካተተ ነው። ፈተናው በውስጡ የተለያዩ ቃላትን አውዳዊ ፍቺ መፈለግን፣ ክፍት ቦታዎችን በተስማሚ ቃላትና ሀረጋት መሙላትን፣ የዐ.ነገር አወቃቀሮችንና ድርሰት መጻፍን ያካተተ ነው። በመሆኑም በእያንዳንዱ የፈተናው ክፍል ስር የተሰጡትን መመሪያዎች መሰረት በማድረግ መልሳችሁን በተሰጣችሁ የመልስ መስጫ ወረቀት ላይ አስፍሩ።

ግጥም አንድ

**ለካስ!**

ያኔ በመጽው ወራት - በጸደይ የጥቢ በጋ፣
ሌሊት በዶሮ ጩኸት - በቅጡ ጠብቶ ሳይነጋ፣
በድብብቆሽ ሳቢያ - አንዱ ካንዳችን ስናመልጥ፣
በጓሳ ጎድሩ መሽገን - በጨፌ ሰርዶው ስንሮጥ።
ያስኳላ ጊዜው ቡረቃ - ኮረጆ እርሳስ ደብተሩ፣
የማደግ ምኞት እሳቤው - የረፍት ቀን ግርግሩ፣
ከመንደራችን በታች - ካለው ጋራና ሜዳ፣
ከዱር እንጨት ስንሰብር - ከምንጭ ውሀ ስንቀዳ።
ከወንዝና ፏፏቴው ስር - ከጨሌው የሳር አመዳይ፣
ከብቶችን አሰማርተን - በአረንጓዴው መስክ ላይ፣
በነፋስ ሽውሽውታ አጀብ - እንደኩል በጠራው ሰማይ፣
ሲደክመን አረፍ ብለን - በሶሪት የአበባ አደይ፣
ዕቃ'ቃ ጨዋታ ብለን - የልግጥየሽ ቤት ሰርተን፣
ምር እንዳይሆን ተማምለን - እዚያው የውሸት ተጋብተን፣
ጥብቋችንን ተጋርተን - ተቃቅፈን አብረን ተኝተን፣
ነፍሴ በሀሴት ጠልቃ - ስሆን በክንድ እቅፍህ፣
እንዴት ነበር ደስስስ እሚለኝ - ሲሞቀኝ ጠረን ትንፋሽህ?

ለካስ የመውደድ ድንበር - የፍቅርም አለው ዳርቻ፣
አብሮነትን 'ሚያስተው - ሚያሰኝ መሆን ለብቻ፡፡
እንዳይጨበጥ ተስፋ - ሳነሳው የጥንት የጧቱን፣
እንደሩቅ አለም ብሽርታ - ሳስበው ያለፍንበቱን፣
ለካስ ፍቅርም እንደሰው - ከስቶ ጠቁሮ ያረጃል፣
ለዛ ወዙ ገርጥቶ - ውበት ጣዕሙ ያፈጃል!
ጉልበት አቅሙ ተሟጦ - አቅሉን ረስቶ ይጃጃል!!
ይኸው ተረስቶ ዛሬማ - በዘመን ዳበዘና ሻግቶ፣
ማተብ ውሉ 'ማይገኝ - ውትብትብ ድር አድርቶ፣
ልጅነት ለጎልማሳነት - ነበር ትዝታን ተክቶ፣
አለፈ ጥሎን ተጓዘ - እኔውም አንተን ረስቶ፡፡

/ውድአላት ገዳሙ፣ እናትና ልጅ፣ 1996፣ ከገጽ16-17 የተወሰደ/

**ሀ.** ከላይ የቀረበውን ግጥም መሰረት በማድረግ ለሚከተሉት ቃላትና ሀረጋት ትክክለኛውን አውዳዊ ወይም አገባባዊ ፍቺ የሚያመለክተውን ቃል ወይም ሀረግ የያዘውን ሆሄ መርጠህ/ሽ በመልስ መስጫ ወረቀትህ/ሽ ላይ ጻፍ/ፊ፡፡

1. መጽው
   ሀ. የክረምት ወቅት ለ. የመኸር ወቅት
   ሐ. የበልግ ወቅት መ. የበጋ ወቅት
2. ድር
   ሀ. ጠንካራ ፈትል ለ. ዝርግ
   ሐ. የተለመጠ መ. ዘሀ
3. ቡረቃ
   ሀ. ፍንደቃ ለ. ረብሻ
   ሐ. ዝላይ መ. ደስታ
4. ጋራ
   ሀ. ጭፈራ ለ. አብሮ መሆን
   ሐ. ከፍ ያለ ቦታ መ. ዝቅ ያለ ቦታ
5. ጨሌ
   ሀ. በአንገት ላይ የሚደረግ ጌጥ ለ. የሳር ቡቃያ
   ሐ. ጾቃ መ. የዛር መለመኛ
6. ሽውሽውታ
   ሀ. ግርፋት ለ. ምች
   ሐ. ምታት መ. የወሬ ፍንጭ
7. ጥብቆ
   ሀ. እግረ አጭር ልብስ ለ. ትንሽ ልብስ
   ሐ. እጀ አጭር ልብስ መ. ጥብቅ ያለ ልብስ

| | | |
|---|---|---|
| 8. ድንበር | ሀ. ክልል | ለ. ሀገር |
| | ሐ. መውጫ | መ. ወሰን |
| 9. አቅል | ሀ. ጥበብ | ለ. ሀሳብ |
| | ሐ. ብልሃት | መ. ትእግስት |
| 10. ጠረን | ሀ. መጥፎ ሽታ | ለ. የሚከረፋ |
| | ሐ. የሚሰነፍጥ | መ. ጥሩ ሽታ |

**ለ.** የሚከተሉትን ባዶ ቦታዎች ተስማሚ ናቸው በምትሏቸው ቃላት አሟሉ። የምትሞሏቸው ቃላት በግራ በኩል የሚገኙት ቃላት ዘሮች መሆን ይገባቸዋል።

1. ውሀ ሩዝ የሚበቅለው በ__________መሬት ላይ ነው።
2. ዘመን ማጨስ__________አይደለም።
3. ሰማይ __________ቀለም እወዳለሁ።
4. ቤት ከበደ ለኛ ቤተሰብ__________ነው።
5. አለም ገዳም ከ__________ተግባር ራሳቸውን ያገለሉ ሰዎች የሚኖሩበት ስፍራ ነው።
6. ልጅነት __________ጥሩ ዜጋ እንዲሆኑ በስነ ምግባር ማሳደግ ያስፈልጋል።
7. ጨዋታ አየለ በባህሪው__________ነው።
8. ተክቶ ኢህአዴግ የ__________ፖሊሲውን እየተገበረ ነው።
9. ሻግቶ __________እንጀራ ለጤና ጠንቅ ነው።
10. ተንዘ ዘመናዊ__________ፈጣን ናቸው።

**ሐ.** የሚከተሉት አባባሎች ከግጥሙ ውስጥ የወጡ ናቸው። አባባሎቹ በግጥሙ ውስጥ የያዙትን ሀሳብ በራስህ/ሽ አባባል አብራራ/ሪ።

1. ምር እንዳይሆን ተማምለን - እዚያው የውሸት ተጋብተን
2. አብሮነትን ’ሚያስተው…
3. ለካስ ፍቅርም እንደሰው - ከስቶ ጠቁሮ ያረጃል
4. …የፍቅርም ዳርቻ አለው
5. እንደሩቅ አለም ብኘርታ….

**መ.** የሚከተሉትን ጥያቄዎች በግጥሙ መሰረት በተሟሉ ዐ.ነገሮች መልስ/ሺ።

1. ግጥሙን አንብበህ/ሽ ስትጨርስ/ሺ ምን ዓይነት ስሜት ተሰማህ/ሽ?
2. የግጥሙን ርዕስ በሌላ ተካው/ተኪው ብትባል/ብትባይ ምን ትለዋለህ/ትይዋለሽ?

3. ገጣሚዋ ፍቅርን ከሰው ልጅ ምን መሆን ጋር ነው ያነጻጸሩት?
4. የግጥሙ ጸሐፊ ‹‹አለፈ ጥሉን ተኳዞ - እኔውም አንተን ረስቶ›› ሲሉ ምን ማለታቸው ነው?
5. የመውደድ ድንበሩ፣ የፍቅር ዳርቻው እስከምን ድረስ ነው?

ሠ. ‹‹የልጅነት ጊዜ ትዝታዬ›› በሚል ርዕስ ከ50 ባልበለጡ ቃላት ልጅነትህን/ሽን የሚያስታውስ አንድ ድርሰት ጻፍ/ፊ?

ግጥም ሁለት

## ዘላለማዊ ነሽ

የቀስተ ደመና፣ የውበት አምሳያ
የትውልድ ጅረት፣ እድሜ መቀጠያ
የአብሮነት መኖር ድባብ፣ ህብር - መጠለያ
የተበተነ ዘር፣ በአንድ መቋጠሪያ፤...
መሆንሽን የረሱ፣
ማተብ የበጠሱ፣
የእምነትሽን ጽናት፣
የእውነትሽን ጥራት፣
በጊዜ መስታወት እያደር ያዩታል፤
ዘላለምነትሽን፣ ዘላለም ያውቁታል፡፡
የማንነቴ አርማ፣ ሰንደቅ ምልክቴ
የኢትዮጵያዊነት፣ ሞገስ በረከቴ
የሰውነት ክብሬ፣ የመንፈስ ጽናቴ
መነሻ መድረሻ፣ ስሬ መሰረቴ፤...
መሆንሽን አውቄ፤
በአንቺ ስር ደምቄ፤
አንገቴን አቅንቼ፤
ሽቅብ ተመልክቼ፤
ስትውለበለቢ ካንቺ ያነበብኩት

ክብር ነው፣ ነጻነት፣ ፍቅር፣ እውነት፣ እምነት፡፡

አላማሽ ሰንደቁ፣ ስሩ የጠለቀ

ቀለምሽ ምስጢሩ፣ ቅኔው የመጠቀ

ፍቅርሽ መቋጠሪያው፣ ውሉ የጠበቀ፤...

አይጥሉሽ - አይቆርጡሽ

አይክዱሽ - አይፍቁሽ

በህይወት የዘሩሽ

በደም ያጸደቁሽ

አረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ አርገው ያቆሙሽ

ሰንደቅ አላማዬ ዘላለማዊ ነሽ!!

/ጌትነት እንየው፣ እውቀትን ፍለጋ፣ 1994፣ ከገጽ 78-79 የተወሰደ/

ሀ. ‹‹ዘላለማዊ ነሽ›› በሚል ርዕስ የቀረበውን ግጥም መሰረት በማድረግ ለተከታዮቹ ቃላትና ሀረጋት አገባባዊ ወይም አውዳዊ ፍቺ ይሆናል የምትለውን/ የምትይውን መልስ የያዘውን ሆሄ በመምረጥ በመልስ መስጫ ወረቀትህ/ሽ ላይ ጻፍ/ፊ፡፡

1. አምሳያ
   ሀ. ቅጥ ለ. ተመሳሳይ
   ሐ. አብነት መ. አይነት
2. ድባብ
   ሀ. ትልቅ ጥላ ለ. ደስታ
   ሐ. ፍርሃት መ. የዛፍ ጥላ
3. ሀብር
   ሀ. ላሀይ ለ. አኳኋን
   ሐ. ጠባይ መ. አንድነት
4. ማተብ
   ሀ. የእጅ ጌጥ ለ. የአንገት ክር
   ሐ. የእግር ጌጥ መ. የጆሮ ጌጥ
5. ዘላለም
   ሀ. በአብዛኛው ለ. አልፎ አልፎ
   ሐ. ሁልጊዜ መ. ወደፊት
6. አርማ
   ሀ. ምልክት ለ. መለያ
   ሐ. መታወቂያ መ. መቆሚያ
7. ዘር
   ሀ. ዝርያ ለ. ትውልድ
   ሐ. ፍሬ መ. ጥሬ
8. መንፈስ
   ሀ. ምትሀት ለ. መብረር
   ሐ. ረቂቅ መ. አእምሮ

9. የተበተነ    ሀ. የተዘራ    ለ. የጠፋ
ሐ. የሄደ    መ. የበነነ

10. ሰውነት    ሀ. ገላ    ለ. ሰው መሆን
ሐ. አካል    መ. መልክ

**ለ.** በ‹‹ሀ›› ስር የተዘረዘሩትን ቃላትና ሀረጋት በ‹‹ለ›› ስር ለተዘረዘሩት ቃላትና ሀረጋት አውዳዊ ፍቺ አዛምድ/ጂ።

| ሀ | ለ |
| --- | --- |
| 1. ማተብ የበጠሱ | ሀ. ሁሌም ትኖሪያለሽ |
| 2. የማንነቴ አርማ | ለ. መጀመሪያና መጨረሻ |
| 3. መነሻ መድረሻ | ሐ. እምነታቸውን የከዱ |
| 4. ሽቅብ ተመልክቼ | መ. ምልክቴ |
| 5. ዘላለማዊ ነሽ | ሠ. ወደላይ አይቼ |

**ሐ.** የሚከተሉትን ባዶ ቦታዎች ተስማሚ ናቸው በምትላቸው/ በምትያቸው ቃላት አሟላ/ይ። የምትሞላቸው/ የምትሞያቸው ቃላት በግራ በኩል ከሚገኙት ቃላት ዘሮች መሆን ይገባቸዋል።

1. መኖር    በከተማ____________ህዝብ ቁጥር በከፍተኛ ደረጃ እየጨመረ ነው።
2. መቋጠሪያ    ለማ የሳምንት ቀለቡን____________መጣ።
3. ሰውነት    ____________ማሰብ የሚችል ማህበራዊ እንስሳ ነው።
4. መንፈስ    ባለፈው ዓመት የተከፈተው____________መዝሙር ቤት ተዘጋ።
5. ተበተነ    በመስመር መዝራት በ____________ከመዝራት የበለጠ ጠቃሚ ነው።
6. ክብር    ጠንክሮ በመስራት____________ይቻላል።
7. ያነበብኩት    ____________ለተማሪዎች እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው።
8. አውቄ    ክት/ቤት____________ይገበያል።
9. ደምቁ    የዘንድሮው በዓል በጣም____________ነበር።
10. ጥራት    የደፈረሰው ውሀ____________።

መ. ከዚህ ቀጥሎ በእዝባር የተሰያዩ ቃላት ወይም ሀረጋት ቀርበዋል፡፡ በቃላቱ ወይም ሀረጋቱ ላይ ሌሎች ከምንባቡ ውጭ የሆኑ ሀረጋትን በመጨመር ሙሉ መልዕክት ሊያስተላልፉ የሚችሉ ዐ.ነገሮችን መስርት/ቺ፡፡

1. መስታወት/ ያዩታል
2. ዘር/ ያውቁታል
3. መኖር/ አውቂ
4. በደም/ ተመልክቺ
5. ማተብ/ ነው

ሠ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በግጥሙ መሰረት በተሟሉ ዐ.ነገሮች መልስ/ሺ፡፡

1. የግጥሙ መልዕክት ምን ይመስልኃል/ ይመስልሻል?
2. ገጣሚው ‹‹የተበተነ ዘር፣ በአንድ መቋጠሪያ›› ሲሉ ምን ለማለት ፈልገው ነው?
3. ሰንደቅ አላማ ለደራሲው ምን ሆና ነው የተሳለችው?
4. ‹‹በጊዜ መስታወት እያደር ያዩታል›› የተባሉት ምን አይነት ሰዎች ናቸው?
5. የግጥሙ ጸሐፊ ሰንደቅ አላማችን ስትውለበለብ ያነበቡት ምን ምን ነገር ነው?

ረ. ‹‹ዘላለማዊ ነሽ›› በሚል ርዕስ የቀረበውን ግጥም ወደ ዝርው ጽሑፍ ቀይረህ/ሽ ጻፍ/ፊ?

## አባሪ ሁለት

## በመደበኛዋ መምህርት በተለመደው ዘዴ ተዘጋጅተው የቀረቡ መልመጃዎች

ግጥም አንድ

**ሰርጾ ያልገባ እውቀት**

ስልጣኔ ማለት ማወቅ መመራመር
ማካፈል መቀነስ መች ብቻ መደመር፤
ስልጣኔ አይደለም በሰው ጥበብ ማድራት
በሰው ጥበብ ማጌጥ በሰው ጥበብ መኩራት።
የራስን ህሊና ሰርጾ ያልገባ እውቀት
የአለት ላይ ውሃ ነው የደቂቃ እርጥበት።
በተውሶ ቮልቮ፣ ጀት እየበረረ
በምጽዋት አስፕሪን ታክሞ እየኖረ
በልመና ውስኪ ጠንብዞ እያደረ
ተራመድኩ ይለናል ከኋላ እየቀረ።
በጥቁር መነጽር ዐይናችንን አጥረው
በብልጭልጭ ዶቃ እጃችንን አስረው፤
በራሳቸው ታሪክ ባህል ወግ ተምረን
ሊቃውንት ስላሉን «ሊቅ ነን» እንበል አብረን?
ሊቅነት እንዲህ ነው ማጌጥ በተውሶ፤
ላይደምቅ ላያኮራን ከዓመት ዓመት ደርሶ!
ስልጡን እንሁን ካል በጥበብ አሻራ
ፈልቅቀን እናውጣ ዕውቀትን ከስራ።

/አያልነህ ሙላት፣ ማን ይሆን የበላ?፣ 1989፣ ገጽ 71/

ክፍል አንድ፡- አንብቦ መረዳት

1. የቀረበውን ግጥም መሰረት በማድረግ ለተከታዮቹ ጥያቄዎች መልስ ስጡ፡፡
   ሀ. ገጣሚው ‹‹ሰርጾ ያልገባ ዕውቀት›› ሲል ምን ለማለት ፈልገው ነው?
   ለ. ስልጡን ለመሆን ምን ማድረግ ያስፈልጋል?
   ሐ. በግጥሙ ውስጥ ‹‹ተራመድኩ ይለናል ከኋላ እየቀረ›› የተባለው ምን አይነት ሰው
   ነው?
   መ. ‹‹ሰርጾ ያልገባ ዕውቀት›› የሚለው ግጥም ምን ያስተምራል ብላችሁ ታስባላችሁ?
   አስረዱ፡፡

2. የሚከተሉት ቃላት በምንባቡ መሰረት የያዙትን ትርጉም አስረዱ፡፡

| | |
|---|---|
| ሀ. እውቀት | ሠ. አስፐሪን |
| ለ. ስልጣኔ | ረ. ጾቃ |
| ሐ. ህሊና | ሰ. ሊቃውንት |
| መ. ቮልቮ | ሸ. ወግ |

ክፍል ሁለት፡- መጻፍ

1. ግጥሙ ያሳደረባችሁን ስሜት በአጭሩ ግለጹ፡፡
2. ግጥሙ ለማስተላለፍ የፈለገው መልዕክት ምንድነው? አጠር አድርጋችሁ አስረዱ፡፡
3. ግጥሙን ወደ ዝርው ጽሑፍ ቀይራችሁ ጻፉ፡፡

ክፍል ሶስት፡- ሰዋስው

1. ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በምሳሌው መሰረት መልሱ፡፡
   ምሳሌ፡- ተምረን → -ን (ባለቤት አመልካች)
   ሀ. ተራመድኩ
   ለ. እየበረረ
   ሐ. አጥረው
   መ. ፈልቅቀን
   ሠ. ራሳቸው

2. ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በምሳሌው መሰረት መልሱ፡፡
   ምሳሌ፡- ማወቅ → አወቀ
   ሀ. መኩራት
   ለ. ማካፈል
   ሐ. መመራመር
   መ. ማድራት

3. በሚከተሉት ቃላት ዐ. ነገር መስርቱባቸው፡፡

ሀ. መቀነስ
ለ. ታሪክ
ሐ. ማጌጥ
መ. ውሃ
ሠ. እርጥበት
ረ. ስራ
ሰ. መነጽር
ሸ. ዓመት

ክፍል አራት፡- ንግግር

1. በሌሎች ታሪክ፣ ባህል፣ ወግ መማር ሊቅ ለመሆን ያስችላል ብላችሁ ታስባላችሁ? ተወያዩ፡፡
2. ‹‹ስልጣኔ አይደለም በሰው ጥበብ ማድራት›› የሚለው ስንኝ የሚያስተላልፈውን መልዕክት አስረዱ፡፡

ግጥም ሁለት

**ከዛፍ የተቀሰመ ዜማ**

ካለም እቅፍ ወጥቶ
ካለም እቅፍ ሸሽቶ
ወደ ገዳም ሲሄድ
ደክሞት ተዝለፍልፎ
ብላቴናው ያሬድ ካንድ ዛፍ ስር አርፎ
ከዛፉ ግንድ ስር ትል ሲሸልል ሰማ
እንዲህ በሚል ዜማ
‹‹ዛፉ ነው ህይወቴ
ቅጠሏም ራቴ
ሰባት ጊዜ ልውደቅ
ሰባቴ እንድወጣ
የኗላ የኗላ እራቴን አላጣ››
ይህንን ስትሰማ ቅጠሊቱ ራደች
መሸሽ ባይሆንላት ሙሾዋን ወረደች
‹‹ዛፉ ህይወቴ ነው
ግን ሃያል ቢመስልም
ተራራ ቢያክልም

የማታ የማታ

ከትል አያስጥልም››

ያሬድ ይህን ሰምቶ

ትሉ በጥረቱ እራት ሲበላ አይቶ

ተስፋውን አጸና

በቅጠሏ እጣ ግን ተነካ ልቦናው

ከዚያም ተመስሶ

የትሉን ፋከራ

የቅጠሏን ለቅሶ

ባንድ ላይ ለውሶ

ዜማውን ቀመረ

ዜማው ተዘመረ

ከሰው ነፍስ ተስማማ

በሰው ድምጽ አማረ።

/በዕውቀቱ ስዩም፣ ኗሪ አልባ ጎጆዎች፣ 1995፣ ከገጽ 60 - 61/

ክፍል አንድ፡- አንብቦ መረዳት

1. ግጥሙን መሰረት በማድረግ ተከታዮቹን ጥያቄዎች መልሱ።
   ሀ. ገጣሚው ‹‹ሰባት ጊዜ ልውደቅ፣ ሰባቴ እንድወጣ›› ሲሉ ምን ማለታቸው ነው?
   ለ. ብላቴናው ያሬድ ትሉ ምን እያለ ሲሸልል ነው የሰማው?
   ሐ. ቅጠሊቱ የራደችው ለምንድነው?
   መ. ያሬድ በቅጠሏ እጣ ለምንድነው ልቦናው የተነካው?
   ሠ. ‹‹ከዛፍ የተቀሰመ ዜማ›› ከሚለው ግጥም ምን ተማራችሁ?

2. የሚከተሉት ቃላት በምንባቡ መሰረት የያዙትን ትርጉም አስረዱ።

| | |
|---|---|
| ሀ. ዜማ | ሠ. ቀመረ |
| ለ. ተስፋውን | ረ. ነፍስ |
| ሐ. እጣ | ሰ. ገዳም |
| መ. ለቅሶ | ሸ. ፋከራ |

ክፍል ሁለት፡- መጻፍ

1. የግጥሙ መልዕክት ምን ይመስላችኋል? አስረዱ፡፡
2. ግጥሙን አንብባችሁ ስትጨርሱ የተሰማችሁን ስሜት ግለጹ፡፡
3. የግጥሙን ርዕስ በሌላ ተኩት ብትባሉ ምን የሚል ርዕስ ትሰጡታላችሁ?

ክፍል ሶስት፡- ሰዋስው

1. የሚከተሉት ቃላት ከምን የቃል ክፍል እንደሚመደቡ ግለጹ፡፡

| | |
|---|---|
| ሀ. ሲሄድ | ሠ. ሰምቶ |
| ለ. ዛፍ | ረ. ነፍስ |
| ሐ. ዜማ | ሰ. አማረ |
| መ. ራደች | ሸ. ድምጽ |

2. ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በምሳሌው መሰረት መልሱ፡፡

   ምሳሌ፡- ሰማ → መስማት

   ሀ. ወጥቶ
   ለ. አርፎ
   ሐ. ወረደች
   መ. ተነካ
   ሠ. ለውሶ

3. በተከታዮቹ ቃላት ዐ.ነገር ስሩባቸው፡፡

| | |
|---|---|
| ሀ. ተመለሰ | ሠ. ትል |
| ለ. እቅፍ | ረ. እራቴን |
| ሐ. ተራራ | ሰ. እንድወጣ |
| መ. ወረደች | ሸ. ሰባት |

ክፍል አራት፡- መናገር

1. ቅዱስ ያሬድ የቀመረው ዜማ ከሰው ነፍስ የተስማማውና በሰው ድምጽ ያማረው ለምን ይመስላችኋል? ተወያዩበት፡፡
2. ስለቅዱስ ያሬድ የምታውቁትን ለጓደኞቻችሁ ንገሯቸው፡፡

## አባሪ ሶስት

## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሙዩኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

## የድህረ ምረቃ መረሐ ግብር

## በደምበጫ ከፍተኛ ትምህርት መሰናዶና አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት በሚማሩ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የሚሞላ መጠይቅ

**መግቢያ**

የዚህ መጠይቅ አላማ፤ ዘጠነኛ ክፍል የምትማሩ ተማሪዎች ከስነ ጽሑፍ ዘሮች መካከል አንዱ በሆነው ግጥም ተጠቅሞ አማርኛ ቋንቋን እንድትማሩ ቢደረግ የእናንተ ምላሽ ምን እንደሚመስል አስተያየት ለማሰባሰብ ነው፡፡

ከጥናቱ የሚገኘው ውጤት ከፍተኛ ጠቀሜታ እንደሚኖረው ይታሰባል፡፡ ስለዚህ በመጠይቁ ስር የሰፈሩትን ጥያቄዎች በትዕግስት በማንበብ ትክክል ናቸው ብላችሁ የምታስቧቸውን መልሶች እንድትሰጡ እየጠየቅሁ መጠይቁን በመሙላት ለምታደርጉልኝ ትብብር አስቀድሜ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

**ማሳሰቢያ**

ሀ. መጠይቁ በግል የሚሞላ ነው፡፡

ለ. መጠይቁን የሚሞሉት የቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናዎችን የወሰዱ፣ በአዲሱ ዘዴ

የተማሩ ተማሪዎች ብቻ ናቸው፡፡

ሐ. በመጠይቁ ላይ ስም መጻፍ አያስፈልግም፡፡

**ክፍል አንድ**

ከዚህ በታች ያሉትን ባዶ ቦታዎች በመሙላት ለተጠየቁት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ስጥ/ስጪ፡፡ ተ.ቁ 4ን ግን ትክክለኛውን መልስ በማክበብ መልስ/ሽ፡፡

1. ጾታ______________________________
2. ዕድሜ______________________________
3. የአፍ መፍቻ ቋንቋ__________________
4. በሚኒሚዲያ፣ በስነ ጽሑፍና ድራማ ክበቦች ተሳትፎ ታደርጋለህ/ታደርጊያለሽ?
   ሀ. አዎ ለ. አላደርግም
5. ለተ.ቁ. 4 መልስህ/ሽ ‹‹አዎ›› ከሆነ የተሳተፍክበትን/ የተሳተፍሽበትን ክበብ ስም ግለጽ/ጪ፡፡________________________________________________

## ክፍል ሁለት

ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ትክክል ናቸው ብለህ/ሽ የምታስባቸውን/ የምታስቢያቸውን መልሶች የያዙትን ሆሂያት በመምረጥ መልስ/ሽ።

እያንዳንዱ ሆሄ የሚወክላቸው ሀሳቦች የሚከተሉት ናቸው።

ሀ. በጣም እስማማለሁ ለ. እስማማለሁ

ሐ. አልስማማም መ. በጣም አልስማማም

1. ከዚህ በፊት በትርፍ ጊዜዬ የተለያዩ የፈጠራ ጽሑፎችን ማለትም አጭር ልቦለድ፣ ረጅም ልቦለድ፣ ግጥም፣ ተውኔት...ወዘተ. አንብቤ ወይም ተከታትዬ አውቃለሁ።

   ሀ. ለ. ሐ. መ.
2. ቀደም ሲል የተለያዩ ልቦለዶችን፣ ግጥሞችን...ወዘተ. የማነበው ማርክ ወይም ውጤት ለማግኘት ስል ነበር።

   ሀ. ለ. ሐ. መ.
3. የፈጠራ ጽሑፎችን አንብቤ በመረዳት ከነሱ የሚዘጋጁትን መልመጃዎች ለመመለስ የሚያስችል በቂ የሆነ ትምህርት ከ9ኛ ክፍል በፊት ተምሬያለሁ።

   ሀ. ለ. ሐ. መ.
4. የፈጠራ ጽሑፎችን አንብበን እርስ በርስ በመወያየትና በመተጋገዝ መማራችን የቋንቋ ክሂሎችንን ለማጎልበት ይረዳናል ብዬ አስባለሁ።

   ሀ. ለ. ሐ. መ.
5. የቀረቡልንን ግጥሞች ካነበብን በኋላ በጋራ በመወያየት እንድንሰራቸው በሚሰጡን መልመጃዎች ላይ ስንወያይ የቡድን አባላት የምንሰነዝረው ሀሳብ እርስ በርሱ የሚደጋገፍ ነበር።

   ሀ. ለ. ሐ. መ.
6. ግጥሞችን ካነበብን በኋላ ስንወያይ በመካከላችን የሀሳብ ልዩነት ይፈጠር ስለነበር ሳንግባባ እንቀር ነበር።

   ሀ. ለ. ሐ. መ.
7. ግጥሞችን ካነበብን በኋላ በምናደርገው ውይይት በመካከላችን የሀሳብ ልዩነት ቢፈጥርም ከምናነሳቸው የማሳመኛ ነጥቦች የተነሳ ወደ አንድ ሀሳብ ለመምጣት አያቅተንም ነበር።

   ሀ. ለ. ሐ. መ.
8. የክፍልም ሆነ የቤት ስራ እንድሰራ መደረጉ በትምህርቱ ወቅት ራሴን ችዬ የመስራት ልምድ እንዳዳብር አግዞኛል ብዬ አምናለሁ።

   ሀ. ለ. ሐ. መ.
9. የግልም ሆነ የቡድን ስራ ተሰጥቶኝ የቃላትን አውዳዊ ፍቺ ስፈልግ፣ ዐ.ነገርን በሌላ መንገድ ስጽፍ ወዘተ. ይከብደኝ ነበር።

   ሀ. ለ. ሐ. መ.

10. አሁን በተማርኩበት ዘዴ መሰረት የቃላትን አውዳዊ ፍቺ የመለየት፣ ዐ.ነገርን በሌላ መንገድ የመጻፍ፣ ድርሰት የመጻፍ ወዘተ. መልመጃዎችን መለማመድ የቋንቋ ችሎታዬን ለማጎልበት ይጠቅመኛል።

ሀ. ለ. ሐ. መ.

11. እኛ እርስ በርስ እየተወያየን ከምንማማር ይልቅ ሁሉንም ትምህርት መምህሩ ቢያስተምረን የተሻለ ነው ብዬ አምናለሁ።

ሀ. ለ. ሐ. መ.

12. በአዲስ (ፈጠራዊ) ዘዴ ቋንቋን መማር ከጀመርኩ ወዲህ የተለያዩ የፈጠራ ጽሑፎችን በጥልቀት ማንበብና መገንዘብ ችያለሁ።

ሀ. ለ. ሐ. መ.

13. በዚህ አይነት ዘዴ አማርኛ ቋንቋን መማሬን ወድጄዋለሁ።

ሀ. ለ. ሐ. መ.

14. አሁን በተማርኩበት ዘዴ አማካይነት በገቡበት አውድ የቃላትን ፍቺ እንድፈልግ፣ ድርሰት እንድጽፍ ወዘተ. በሚደረግበት ጊዜ ደስተኛ አልነበርኩም።

ሀ. ለ. ሐ. መ.

## ክፍል ሶስት

ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች አንብበህ/ሽ ከተሰጡት ዝርዝር አማራጮች መካከል መልስ ይሆናሉ የምትላቸውን/ የምትያቸውን ፊደላት አክብብ/ቢ። ምርጫህ/ሽ ከአንድ በላይ ከሆነ በተሰጠው ክፍት ቦታ በቁጥር ቅደም ተከተል ሰጠህ/ሽ አስፍር/ሪ።

ከዚህ ባሻግር ከተሰጡት ምርጫዎች መካከል መልስ የምትለው/የምትይው ከሌለ መልስ ይሆናል ብለህ/ሽ የምታስበውን/ የምታስቢውን ሀሳብ በጥያቄዎቹ ስር በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ በመጻፍ መልስ።

15. ለጥያቄ ቁጥር ‹‹13›› የሰጠኸው/ሽው መልስ ‹‹ሀ›› ወይም ‹‹ለ›› ከሆነ ምክንያቱ ምንድነው ብለህ/ሽ ታስባለህ/ታስቢያለሽ።

ሀ. እርስ በርስ እየተዝናናንና እየተረዳዳን እንድንማማር የሚያደርግ በመሆኑ

ለ. የመማር ማስተማር ሂደቱ በአብዛኛው በእኛ የሚከናዎን በመሆኑ

ሐ. የመማር ማስተማር ሂደቱ ባብዛኛው በመምህሩ የሚከናዎን በመሆኑ

መ. ተማሪው ትምህርቱን በስርዓት እንዲከታተል ስለሚያግዘው በክፍል ውስጥ ሊኖር

የሚችለውን ረብሻና ጫጫታ የሚቀንስ በመሆኑ

ሠ. የመማር ማስተማር ዘዴው ለኛ አዲስ በመሆኑ

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

________________::

16. ለጥያቄ ተ.ቁ ‹‹14›› የሰጠኸው/ሽ መልስ ‹‹ሀ›› ወይም ‹‹ለ›› ከሆነ ምክንያቱ ምንድን ነው ብለህ/ሽ ታስባለህ/ታስቢያለሽ፡፡

ሀ. የትምህርቱ ሂደት ባብዛኛው በመምህሩ የሚመራ በመሆኑ

ለ. የትምህርቱ ሂደት ተማሪውን የሚያሳትፍ በመሆኑ

ሐ. ቀደም ሲል የምማርበት የትምህርት ሂደት ሁሉም ነገር በመምህሩ መሪነት የሚከናዎን በመሆኑ

መ. በቡድንም ሆነ ክፍሉ በሙሉ በሚያደርገው ውይይት የተነሳ የክፍሉ ጸጥታ የሚደፈርስ በመሆኑ

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

________________::

17. በአጠቃላይ በመማር ማስተማሩ ወቅት ስላገኘኸው/ሽው አዲስ የመማር ማስተማር ስልት ተጨማሪ አስተያየት ካለህ/ሽ ግለጽ/ጭ፡፡

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

________________________

## አባሪ አራት

በደምበጫ ከፍተኛ ትምህርት መሰናዶና አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት በ2005 ዓ.ም. ለሚማሩ የ9[25] ክፍል (በቁጥጥር ሁኔታ ለተጠኑ) ተማሪዎች የተሰጠ የቅድመ ትምህርት ፈተና ውጤት መግለጫ

| ተ.ቁ | የፈተና ኮድ | የአራሚ 1 ውጤት | የአራሚ 2 ውጤት | የአራሚ 3 ውጤት | አማካይ ውጤት |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 2501ሀ | 55 | 57 | 55 | 55.67 |
| 2 | 2502ሀ | 30 | 28 | 32 | 30 |
| 3 | 2503ሀ | 47 | 43 | 45 | 45 |
| 4 | 2504ሀ | 35 | 38 | 35 | 36 |
| 5 | 2505ሀ | 27 | 26 | 28 | 27 |
| 6 | 2506ሀ | 30 | 28 | 31 | 29.67 |
| 7 | 2507ሀ | 14 | 17 | 20 | 17 |
| 8 | 2508ሀ | 28 | 26 | 24 | 26 |
| 9 | 2509ሀ | 46 | 46 | 45 | 45.67 |
| 10 | 2510ሀ | 29 | 30 | 28 | 29 |
| 11 | 2511ሀ | 76 | 20 | 18 | 18 |
| 12 | 2512ሀ | 22 | 20 | 21 | 21 |
| 13 | 2513ሀ | 20 | 22 | 19 | 20.33 |
| 14 | 2514ሀ | 28 | 29 | 30 | 29 |
| 15 | 2515ሀ | 50 | 48 | 49 | 49 |
| 16 | 2516ሀ | 23 | 21 | 22 | 22 |
| 17 | 2517ሀ | 25 | 23 | 23 | 23.67 |
| 18 | 2518ሀ | 28 | 28 | 26 | 27.33 |
| 19 | 2519ሀ | 42 | 40 | 41 | 41 |
| 20 | 2520ሀ | 57 | 54 | 58 | 56.33 |
| 21 | 2521ሀ | 29 | 30 | 31 | 30 |
| 22 | 2522ሀ | 63 | 60 | 63 | 62 |
| 23 | 2523ሀ | 18 | 16 | 20 | 18 |
| 24 | 2524ሀ | 31 | 33 | 30 | 32 |
| 25 | 2525ሀ | 45 | 48 | 45 | 46 |
| 26 | 2526ሀ | 59 | 60 | 58 | 59 |
| 27 | 2527ሀ | 45 | 47 | 45 | 45.67 |
| 28 | 2528ሀ | 52 | 50 | 51 | 51 |
| 29 | 2529ሀ | 29 | 30 | 31 | 30 |
| 30 | 2530ሀ | 40 | 40 | 42 | 40.67 |
| 31 | 2531ሀ | 64 | 65 | 63 | 64 |
| 32 | 2532ሀ | 26 | 28 | 26 | 30 |
| 33 | 2533ሀ | 58 | 60 | 61 | 59.67 |
| 34 | 2534ሀ | 48 | 46 | 45 | 46.33 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 35 | 2535ป | 37 | 39 | 38 | 38 |
| 36 | 2536ป | 29 | 30 | 28 | 29 |
| 37 | 2537ป | 57 | 56 | 55 | 56 |
| 38 | 2538ป | 36 | 34 | 37 | 35.67 |
| 39 | 2539ป | 24 | 22 | 23 | 23 |
| 40 | 2540ป | 45 | 44 | 47 | 45.33 |
| 41 | 2541ป | 46 | 47 | 45 | 46 |
| 42 | 2542ป | 39 | 38 | 37 | 38 |
| 43 | 2543ป | 26 | 24 | 28 | 26 |
| 44 | 544ป | 40 | 42 | 40 | 40.67 |
| 45 | 2545ป | 48 | 47 | 50 | 48.33 |
| 46 | 2546ป | 30 | 33 | 30 | 31 |
| 47 | 2547ป | 24 | 23 | 25 | 24 |
| 48 | 2548ป | 16 | 17 | 18 | 17 |
| 49 | 2549ป | 39 | 40 | 41 | 40 |
| 50 | 2550ป | 19 | 22 | 20 | 20.33 |
| 51 | 2551ป | 26 | 29 | 26 | 27 |
| 52 | 2552ป | 43 | 45 | 41 | 43 |
| 53 | 553ป | 68 | 69 | 66 | 67.67 |
| 54 | 2554ป | 26 | 27 | 25 | 26 |
| 55 | 2555ป | 33 | 33 | 34 | 33.33 |
| 56 | 2556ป | 46 | 48 | 44 | 46 |
| 57 | 2557ป | 58 | 59 | 60 | 59 |
| 58 | 2558ป | 19 | 21 | 20 | 20 |

## አባሪ አምስት

በደምበጫ ከፍተኛ ትምህርት መሰናዶና አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት በ2005 ዓ.ም. ለሚማሩ የ9[29] ክፍል (በተጠኝነት ሁኔታ ለተጠኑ) ተማሪዎች የተሰጠ የቅድመ ትምህርት ፈተና ውጤት መግለጫ

| ተ.ቁ | የፈተና ኮድ | የአራሚ 1 ውጤት | የአራሚ 2 ውጤት | የአራሚ 3 ውጤት | አማካይ ውጤት |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 2901ሀ | 50 | 48 | 49 | 49 |
| 2 | 2902ሀ | 37 | 36 | 38 | 37 |
| 3 | 2903ሀ | 68 | 66 | 70 | 68 |
| 4 | 2904ሀ | 22 | 21 | 22 | 21.67 |
| 5 | 2905ሀ | 19 | 19 | 19 | 19 |
| 6 | 2906ሀ | 35 | 36 | 37 | 36 |
| 7 | 2907ሀ | 46 | 47 | 46 | 46.33 |
| 8 | 2908ሀ | 23 | 25 | 27 | 25 |
| 9 | 2909ሀ | 43 | 40 | 42 | 41.67 |
| 10 | 2910ሀ | 37 | 38 | 40 | 38.33 |
| 11 | 2911ሀ | 64 | 62 | 63 | 63 |
| 12 | 2912ሀ | 26 | 26 | 28 | 26.67 |
| 13 | 2913ሀ | 30 | 32 | 31 | 31 |
| 14 | 2914ሀ | 42 | 40 | 44 | 42 |
| 15 | 2915ሀ | 20 | 22 | 22 | 21.33 |
| 16 | 2916ሀ | 27 | 27 | 29 | 27.67 |
| 17 | 2917ሀ | 53 | 51 | 53 | 52.33 |
| 18 | 2918ሀ | 31 | 32 | 30 | 31 |
| 19 | 2919ሀ | 29 | 28 | 27 | 28 |
| 20 | 2920ሀ | 45 | 44 | 46 | 45 |
| 21 | 2921ሀ | 43 | 41 | 40 | 41.33 |
| 22 | 2922ሀ | 28 | 27 | 28 | 27.67 |
| 23 | 2923ሀ | 31 | 33 | 32 | 32 |
| 24 | 2924ሀ | 44 | 44 | 44 | 44 |
| 25 | 2925ሀ | 58 | 56 | 57 | 57.67 |
| 26 | 2926ሀ | 26 | 24 | 23 | 24.33 |
| 27 | 2927ሀ | 53 | 51 | 52 | 52 |
| 28 | 2928ሀ | 66 | 64 | 65 | 65 |
| 29 | 2929ሀ | 45 | 44 | 46 | 45 |
| 30 | 2930ሀ | 23 | 22 | 24 | 23 |
| 31 | 2931ሀ | 19 | 20 | 19 | 19.33 |
| 32 | 2932ሀ | 38 | 37 | 39 | 38 |
| 33 | 2933ሀ | 49 | 51 | 53 | 51 |
| 34 | 2934ሀ | 56 | 57 | 55 | 56 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 35 | 2935υ | 27 | 28 | 25 | 26.67 |
| 36 | 2936υ | 27 | 28 | 29 | 28 |
| 37 | 2937υ | 31 | 33 | 30 | 31.33 |
| 38 | 2938υ | 55 | 56 | 54 | 55 |
| 39 | 2939υ | 60 | 60 | 61 | 60.33 |
| 40 | 2940υ | 29 | 28 | 27 | 28 |
| 41 | 2941υ | 18 | 19 | 17 | 18 |
| 42 | 2942υ | 40 | 44 | 41 | 41.67 |
| 43 | 2943υ | 33 | 30 | 31 | 31.33 |
| 44 | 2944υ | 25 | 24 | 23 | 24 |
| 45 | 2945υ | 53 | 58 | 56 | 55.67 |
| 46 | 2946υ | 62 | 61 | 60 | 61 |
| 47 | 2947υ | 21 | 20 | 22 | 21 |
| 48 | 2948υ | 40 | 38 | 39 | 39 |
| 49 | 2949υ | 21 | 23 | 20 | 21.33 |
| 50 | 2950υ | 50 | 52 | 53 | 51.67 |
| 51 | 2951υ | 25 | 24 | 27 | 25 |
| 52 | 2952υ | 39 | 37 | 41 | 39 |
| 53 | 2953υ | 31 | 29 | 33 | 31 |
| 54 | 2954υ | 21 | 23 | 20 | 21.33 |
| 55 | 2955υ | 56 | 57 | 56 | 56.33 |
| 56 | 2956υ | 22 | 22 | 24 | 22.67 |
| 57 | 2957υ | 30 | 31 | 32 | 30.33 |
| 58 | 2958υ | 20 | 50 | 52 | 51 |

## አባሪ ስድስት

በደምበጫ ከፍተኛ ትምህርት መሰናዶና አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት በ2005 ዓ.ም. ለሚማሩ የ$9^{25}$ ክፍል (በቁጥጥር ሁኔታ ለተጠኑ) ተማሪዎች የተሰጠ የድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት መግለጫ

| ተ.ቁ | የፈተና ኮድ | የአራሚ 1 ውጤት | የአራሚ 2 ውጤት | የአራሚ 3 ውጤት | አማካይ ውጤት |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 2501ለ | 60 | 63 | 61 | 61.33 |
| 2 | 2502ለ | 71 | 72 | 69 | 70.67 |
| 3 | 2503ለ | 44 | 44 | 44 | 44 |
| 4 | 2504ለ | 38 | 36 | 40 | 38 |
| 5 | 2505ለ | 56 | 58 | 54 | 56 |
| 6 | 2506ለ | 67 | 66 | 65 | 66 |
| 7 | 2507ለ | 48 | 49 | 48 | 48.33 |
| 8 | 2508ለ | 45 | 42 | 42 | 43 |
| 9 | 2509ለ | 40 | 39 | 41 | 40 |
| 10 | 2510ለ | 28 | 27 | 30 | 28.33 |
| 11 | 2511ለ | 31 | 33 | 29 | 31 |
| 12 | 2512ለ | 61 | 60 | 59 | 60 |
| 13 | 2513ለ | 70 | 72 | 68 | 70 |
| 14 | 2514ለ | 67 | 69 | 71 | 69 |
| 15 | 2515ለ | 52 | 50 | 53 | 51.67 |
| 16 | 2516ለ | 44 | 47 | 44 | 45 |
| 17 | 2517ለ | 39 | 38 | 40 | 39 |
| 18 | 2518ለ | 54 | 56 | 53 | 54.33 |
| 19 | 2519ለ | 50 | 52 | 51 | 51 |
| 20 | 2520ለ | 59 | 60 | 62 | 60.33 |
| 21 | 2521ለ | 72 | 75 | 71 | 72.67 |
| 22 | 2522ለ | 22 | 22 | 22 | 22 |
| 23 | 2523ለ | 34 | 31 | 32 | 31.33 |
| 24 | 2524ለ | 44 | 45 | 43 | 44 |
| 25 | 2525ለ | 42 | 40 | 41 | 41 |
| 26 | 2526ለ | 50 | 52 | 50 | 50.67 |
| 27 | 2527ለ | 36 | 38 | 38 | 37.33 |
| 28 | 2528ለ | 59 | 58 | 60 | 59 |
| 29 | 2529ለ | 66 | 63 | 64 | 64.33 |
| 30 | 2530ለ | 79 | 80 | 81 | 80 |
| 31 | 2531ለ | 44 | 44 | 43 | 43.67 |
| 32 | 2532ለ | 78 | 77 | 79 | 78 |
| 33 | 2533ለ | 54 | 53 | 52 | 53 |
| 34 | 2534ለ | 69 | 70 | 72 | 70.33 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 35 | 2535ก | 68 | 68 | 68 | 68 |
| 36 | 2536ก | 70 | 71 | 72 | 71 |
| 37 | 2537ก | 55 | 55 | 52 | 54 |
| 38 | 2538ก | 37 | 38 | 35 | 36.67 |
| 39 | 2539ก | 41 | 40 | 42 | 41 |
| 40 | 2540ก | 43 | 46 | 45 | 44.67 |
| 41 | 2541ก | 49 | 50 | 52 | 50.33 |
| 42 | 2542ก | 58 | 59 | 59 | 58 |
| 43 | 2543ก | 77 | 78 | 76 | 77 |
| 44 | 2544ก | 49 | 50 | 50 | 49.67 |
| 45 | 2545ก | 65 | 63 | 62 | 63.33 |
| 46 | 2546ก | 56 | 57 | 55 | 56 |
| 47 | 2547ก | 52 | 54 | 50 | 32 |
| 48 | 2548ก | 48 | 45 | 48 | 47 |
| 49 | 2549ก | 38 | 36 | 37 | 37 |
| 50 | 2550ก | 60 | 62 | 61 | 61 |
| 51 | 2551ก | 41 | 44 | 42 | 42.33 |
| 52 | 2552ก | 53 | 50 | 52 | 51.67 |
| 53 | 2553ก | 62 | 60 | 64 | 62 |
| 54 | 2554ก | 25 | 27 | 24 | 25.33 |
| 55 | 2555ก | 47 | 45 | 49 | 47 |
| 56 | 2556ก | 33 | 35 | 31 | 33 |
| 57 | 2557ก | 51 | 50 | 50 | 50.33 |
| 58 | 2558ก | 42 | 44 | 43 | 43 |

## አባሪ ሰባት

በደምበጫ ከፍተኛ ትምህርት መሰናዶና አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት በ2005 ዓ.ም. ለሚማሩ የ9[29] ክፍል (በተጠኘነት ሁኔታ ለተጠኑ) ተማሪዎች የተሰጠ የድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት መግለጫ

| ተ.ቁ | የፈተና ኮድ | የአራሚ 1 ውጤት | የአራሚ 2 ውጤት | የአራሚ 3 ውጤት | አማካይ ውጤት |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 2901ለ | 80 | 83 | 82 | 91.67 |
| 2 | 2902ለ | 78 | 80 | 79 | 79 |
| 3 | 2903ለ | 90 | 91 | 90 | 90.33 |
| 4 | 2904ለ | 92 | 93 | 91 | 92 |
| 5 | 2905ለ | 89 | 85 | 87 | 87 |
| 6 | 2906ለ | 78 | 76 | 79 | 77.67 |
| 7 | 2907ለ | 69 | 70 | 71 | 70 |
| 8 | 2908ለ | 94 | 97 | 94 | 95 |
| 9 | 2909ለ | 90 | 89 | 91 | 90 |
| 10 | 2910ለ | 83 | 80 | 83 | 82 |
| 11 | 2911ለ | 77 | 76 | 77 | 76.67 |
| 12 | 2912ለ | 66 | 68 | 67 | 67 |
| 13 | 2913ለ | 70 | 72 | 72 | 72 |
| 14 | 2914ለ | 78 | 79 | 80 | 79 |
| 15 | 2915ለ | 84 | 83 | 80 | 82.33 |
| 16 | 2916ለ | 92 | 90 | 94 | 92 |
| 17 | 2917ለ | 73 | 74 | 71 | 72.67 |
| 18 | 2918ለ | 82 | 80 | 82 | 81.33 |
| 19 | 2919ለ | 74 | 75 | 73 | 74 |
| 20 | 2920ለ | 69 | 70 | 71 | 70 |
| 21 | 2921ለ | 63 | 91 | 91 | 91.67 |
| 22 | 2922ለ | 88 | 89 | 90 | 89 |
| 23 | 2923ለ | 71 | 73 | 69 | 71 |
| 24 | 2924ለ | 80 | 83 | 83 | 82 |
| 25 | 2925ለ | 79 | 80 | 81 | 80 |
| 26 | 2926ለ | 72 | 73 | 71 | 72 |
| 27 | 2927ለ | 84 | 84 | 84 | 84 |
| 28 | 2928ለ | 69 | 68 | 70 | 69 |
| 29 | 2929ለ | 77 | 76 | 78 | 77 |
| 30 | 2930ለ | 86 | 89 | 88 | 87.67 |
| 31 | 2931ለ | 95 | 96 | 93 | 94.67 |
| 32 | 2932ለ | 78 | 79 | 80 | 79 |
| 33 | 2933ለ | 83 | 81 | 80 | 81.33 |
| 34 | 2934ለ | 91 | 93 | 89 | 91 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 35 | 2935ለ | 66 | 67 | 65 | 66 |
| 36 | 2936ለ | 75 | 76 | 78 | 76.33 |
| 37 | 2937ለ | 82 | 84 | 83 | 83 |
| 38 | 2938ለ | 68 | 70 | 71 | 69.67 |
| 39 | 2939ለ | 69 | 70 | 68 | 69 |
| 40 | 2940ለ | 80 | 83 | 80 | 81 |
| 41 | 2941ለ | 77 | 76 | 77 | 76.67 |
| 42 | 2942ለ | 88 | 88 | 91 | 89 |
| 43 | 2943ለ | 79 | 83 | 81 | 80 |
| 44 | 2944ለ | 70 | 74 | 72 | 72 |
| 45 | 2945ለ | 67 | 70 | 70 | 68.33 |
| 46 | 2946ለ | 85 | 82 | 85 | 84 |
| 47 | 2947ለ | 81 | 84 | 80 | 81.67 |
| 48 | 2948ለ | 68 | 70 | 72 | 70 |
| 49 | 2949ለ | 71 | 70 | 72 | 71 |
| 50 | 2950ለ | 78 | 80 | 79 | 79 |
| 51 | 2951ለ | 95 | 96 | 93 | 94.67 |
| 52 | 2952ለ | 80 | 82 | 79 | 80.33 |
| 53 | 2953ለ | 81 | 85 | 83 | 83 |
| 54 | 2954ለ | 75 | 75 | 74 | 75 |
| 55 | 2955ለ | 68 | 66 | 70 | 68 |
| 56 | 2956ለ | 89 | 90 | 92 | 90.33 |
| 57 | 2957ለ | 90 | 90 | 90 | 90 |
| 58 | 2958ለ | 86 | 87 | 84 | 85.67 |

## አባሪ ስምንት

## ድርሰት ለማረም የሚያስችል የነጥብ አሰጣጥ

**ይዘት** ከ 0 — 3 ነጥብ

0 ስለ ርዕሱ ምንም እውቀት የሌለው፣ ከይዘቱ ጋር ያልተስማማና ከርዕሱ
ጋር ያልተገናኘ

1 ስለ ርዕሱ ጥቂት እውቀት ያለው፣ ትንሽ ፍሬ ጉዳይ ብቻ ያለበት

2 ስለርዕሱ በቂ ዕውቀት ያለው፣ በጥሩ መልኩ የቀረበ

3 ስለ ርዕሱ መካከለኛ ዕውቀት ያለው፣ በመካከለኛ ደረጃ የቀረበ

4 ስለ ርዕሱ የተሟላ ዕውቀት ያለው፣ በሚገባ ተብራርቶ የቀረበ

**አደረጃጀት** ከ 0 — 3 ነጥብ

0 በእያንዳንዱ አንቀጽና በዋናው ጽሑፍ ላይ ምንም አይነት የሀሳብ አደረጃጀት የማይታይበት፣ ሀሳብ የማያስተላልፍ

1 በእያንዳንዱ አንቀጽና በዋናው ጽሑፍ ላይ ጥቂት የሀሳብ አደረጃጀት ያለው፣ ሀሳቦች ያልተጣጣሙበት

2 በሚገባ ያልተደራጀ፣ ነገር ግን ዋናው ሀሳብ ተለይቶ የሚታወቅ

3 የጽሑፉ አጠቃላይ ቅርጽና የአንቀጾች ውስጣዊ አደረጃጀት በሚገባ የተደራጀ፣ ግልጽ ሆኑ ሀሳቦች የቀረቡበት

**ጽምረት** ከ 0 — 3 ነጥብ

0 ጽምረት የማይታይበት፣ ለማስተላለፍ የተፈለገውን ሀሳብ የጽሑፉ ሀሳብ
የተበታተነ በመሆኑ ለማስተላለፍ የማይችል

1 መልዕክቱን ለመረዳት የሚያስቸግር፣ በቂ ጽምረት የሌለው

2 በቂ ጽምረት የሚታይበት፣ የጽምረት ችግር ቢታይበትም መልዕክቱን ለመረዳት የማያዳግት

3 ጥሩ ጽምረት ያለውና መልካም ተግባቦት የመፍጠር ሀይል ያለው

**ቃላት** ከ 0 — 4 ነጥብ

0 መሰረታዊ ተግባቦት ለመፍጠር የማይችል ደካማ የቃላት ዕውቀትና አጠቃቀም የሚታይበት

1 ቃላትን የሚደጋግም፣ ምሳሌ፡- የቃላት ቅርጽ፣ መረጣና አጠቃቀም ላይ ተደጋጋሚ ስህተት የሚታይበት

2 በቃላት ቅርጽ፣ መረጣና አጠቃቀም ላይ ተገቢ ያልሆነ ድግግሞሽ የሚታይበት

3 ተፈላጊ የሆኑ ቃላት ድግግሞሽ ብቻ የሚታይበት

4 ጥርት ያለና በሳል ሆነ የቃላት መረጣና አጠቃቀም የሚታይበት

**ሰዋስው** ከ 0 — 3 ነጥብ

0 በእያንዳንዱ ዐ.ነገር ላይ ሰዋስዋዊ ስህተት ያለበት

1 በጣም ተደጋጋሚ የሰዋስው ስህተት ያለበት። ለምሳሌ በጽሑፉ ውስጥ ከ10 በላይ ሰዋስዋዊ ስህተቶች ያሉበት

2 በጣም አነስተኛ የሰዋስው ስህተት ያለበት። ለምሳሌ በጽሑፉ ውስጥ ከ10 በታች ሰዋስዋዊ ስህተቶች ያሉበት

3 ዐ.ነገሮቹ ከሰዋስዋዊ ስህተት የጸዱ

**የፊደል አጣጣልና ስርዓተ ነጥብ** ከ 0 — 2 ነጥብ

0 እጅግ ደካማ የፊደል አጣጣልና የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም የሚታይበት

1 አነስተኛ የፊደል አጣጣልና የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ችግር የሚታይበት

2 ከፍተኛ የፊደል አጣጣልና የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ብቃት የሚታይበት

በመሆኑም ይዘትና አደረጃጀትን በተመለከተ ከ10 የሚያዘው ነጥብ እንደሚከተለው መሆን አለበት።

| | |
|---|---|
| ይዘትና ሀሳብ | 4 ነጥብ |
| አደረጃጀት | 3 ነጥብ |
| ጽምረት | 3 ነጥብ |

የቋንቋ አጠቃቀምን በሚመለከት ከ10 የሚያዘው ነጥብ እንደሚከተለው መሆን አለበት

| | |
|---|---|
| ሰዋስው | 4 ነጥብ |
| ቃላት | 4 ነጥብ |
| ስርዓተ ነጥብና የሆሄያት አጣጣል | 2 ነጥብ |

ምንጭ /Atkins, 1996:14)

## አባሪ ||ጠኝ

### የቲ- ቴስት ቀመር

$$t = \frac{x_1 - x_2}{\sqrt{\frac{S_1^2 + S_2^2}{n}}}$$

### ምልክቶቹ የሚወክሉት

$X_1$ = የናሙና አንድ አማካይ ውጤት

$X_2$= የናሙና ሁለት አማካይ ውጤት

$S_1^2$ = የናሙና አንድ የልይይት መጠን

$S_2^2$ = የናሙና ሁለት የልይይት መጠን

n = የናሙና አንድ ወይም የናሙና ሁለት ብዛት

ምንጭ:- /ያለው፣ 1998፣ 282/

አገሬ 10 "ሀ"

## ፍቅር ስራ

ጊዜን ሳናባክን ለትምህርት ቀጥሮ
ጠንክረን መስራት ነው ከዛሬ ጀምሮ
መስራት አለብን የሀገራችን ኩራ!!

መሰረት መሆ እንድንችል ለልጆች
ለልጆች አገር ትርጉም መሆኑ
ቋንቋ ዘለቄ እንዲሰጥ መሆን!!

ለተማሪ ገጠሩ ወንዱ ተዳምሮ ለአንድ
ለአንድ ወገንነ ነህ ለሁሉ!!

~~እህን ሠንደቅ ንን እንድትሰጥ ጠብቁ!!~~

ጉሩ ዛሬ እንድ ወስሉ ታጥቆ
እህን ሠንደቅ ንን እንድትሰጥ ጠብቁ
ለወን የወንድነ መዘመብ ጉሩ ስሉ ሠራ
መሀየ ወገንርሰ ሠአትን ታገሁ!!

ጥሩ ተጽፏል የቃላት ስንጠቃ የተስተካከ መሆን አለበት

9/10

በጣም ጥሩ
ጎበዝ!

~~በመጀመሪያ ደረጃ ስለ ሰላም የሚከተሉትን ለማብራራት እሞክራለሁ~~

## ሰላም

በመጀመሪያ ስለሀገራችን ትንሽ አንዳንድ ነገሮችን
እንነጋገር:: የእኛ ሀገር ኢትዮጵያ የብዙ ብሄር ብሄረሰቦች
ሀገር ናት መሆኗ አስመስክራ በአለ የዘመናት የመቻቻል
ባህሏ ሆና ለመቆየት የቻለችው ሀገር ነው:: ሀገራችን አሁን
ደግሞ (ሰላም ሀገር) በመሆን ፣ ከዓለም የሰላም አገሮች
ዘመን ደግሞ ለሰላም እንቅ የሆነ የሰላም አስፈላጊነት
እንደሚገባ ይህን (ለሰላም) ለመረዳት የሚያስችል ነው
ለመታሰቢያ እንድንችል:: የሰላም ምንነት ፣ ስለሰላም
እንደሚገባ ህዝብ ነፃነት ለሀገሮች ሀገራችን ለሰላም
ለሀገር ለመኖር አስፈላጊ ነው:: ስለዚህ ግን ሰላም
ያለ ሰላም ልማት የለም ለኢትዮጵያ ለመኖር እንደ
የሚገኝ ለመኖር በተለያዩ ጉዳዮች ተፅዕኖ ያሳድራል::
ሰላም ሀገር የሚያመጣ ልማት ዕድገት የሚያመጣ ሰላም
ጊዜያት ወደ ወደፊት በመሆን የሚያስችል:: የኢትዮጵያ
የታሪክ ሰላምን ለማምጣት እንደሚያስፈልግ ለመኖር
ስለ ዕድገት መልካም የሚያደርግ ይሆናል:: የእኛ ሀገር
ሰላምም እንደሚያስፈልግ ሰላም እንደሚፈልግ ሰላማዊ
እንደሆነ የምንችል ሰላም ሰላምም ለሀገራችን
እንደሆነ ለማለት እንደ እንደ የእንደዚህ ሀገር
መፍትሄ ይሆናል::

● ወሰለላ የሚገኝ ሰላምን ለማጠናከር
⊕ ስለሰላም ለመኖር የሚችሉ ዜጎች በሀገር የሚሆን

8/10

በጣም ጥሩ ነው!

ሐ,

1, ሰባት ቋንቋን ጣለ ቋንቋ ገመተናል:: በመጀመሪያ ባህሉና ወጉን ~~[illegible]~~ ሆኖናል ለመግለፅ ነው::

2, በጋራ መሆናችን የሚያጸናክረው::

3, ቶፊር ተቋቋሚ ነው :: መደመሩ የተፈጠረ አብቶ የመረለበ እንደመሆኑ እንደሆነው

5, ያለው ጊዜ በሕይወት ረጅም

8/10

4, ቶፊር መግባቱ ይቀርለዋል

መ, 1, የመንፈስ መዝሙናት

2, ~~[illegible]~~ ሽይወት

3, ወይን / ~~[illegible]~~ /ተወዳዳሪ/.

2/10

4 ወጆች ትቶ አብቶ ኤሉቶአል ይወዳል እንደተነሙ::

5. ለባቶቹን እንሽ ጋለም ይሄ

ሠ, የወጆች ጊዜ ትዝታ

በዓሉን ኑሯችም ዛሬ ይንበሙ ወሬ ፈንድቶ ሽንሽ ገመር መንደር ተመለዩን ያዩውን ይሆላል ወጆች ነበርን:: እኔና ጓደኛዬ ሚለት ነው:: በልጅ ነቶቹን የመገናው መንገድ ለበቶችን እጠ ገባ ሰለገበር ይንጋቁበሙገደካና በመሚሁት ቶፊሮችን ክረፎ እንቀጥልመን ነበር:: ሠፈር ልቶ እኔና ጓደኛዬ ወደ መሰመር ሰይን ይንጋቁ ሳንሠበስብ ጎናዋ የሰፈር በሚለት ለቁንንሰ ያፋንጣን ይወር:: ወይም የልጅ ነገር ሞንቃ እጀቶቻቸው በቋሚሞቻቸን "እሠን ተመለሰ ለመጠ ገገና ናሠ ወዴለቹሠ" በሚለት ይለጠገቃቸን:: እናም ተፈተለብን:: "እንገኛም" አለን በኋላ ወደ ቦታችን

በጣም ደስ ነው!

9

ጓደኞቼ
ⓐ ሁሉንአቀፍ ቶፊር ይተዳ
ⓑ የቆሰለት ጊዜውለን ይቶተመለ

ሀ, የሰሜኑ ጋራ ቀዝቃዜ

በሰሜኑ ጋራ ከዜናት ከእነቱ ጉዞ ለመጠ ቁጥሩ ከጓደኞቹ ጋር እየተጫወተ
እሱር እየሬመሁ እና ዳቃ እየሮጠሁ እጆቹ ነበር።
ተለዛሁ በዜናን ጋራ ~~የሰሜናን~~ በሰሜናን ብዙ አለመቀጥም ነበር።
ከዜና ቀስ በቀስ እና መረሁ በጋራሁ ጋራ እናት እለቤን
በመተዘዝ ከበተና ዳጁ እየመሰቃሁ እየር ነበር።
በዜና በመቀጠል ቀ እሰውት ሲሞላት እየሰራ ዘረጃ ቀለቶ ገዛ።

<u>ማስታወሻ</u>

- [illegible]
- [illegible]
  [illegible]
- [illegible]
- [illegible]

# ማረጋገጫ

ን ጥናታዊ ፅሁፍ የኔ መሆኑንና የተጠቀምኩባቸውን ምንጮች በትክክል የተጠቀምኩ እና
ጠቀስኩ መሆኔን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ም፡- ነብዩ ጋሹ

ርማ፡- -----------

ዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሙዩኒኬሽን ኮሌጅ
ማርኛ ቋንቋ፣ ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል
ህረ ምረቃ መረሐ ግብር
ዲስ አበባ፣ ሰኔ 2005 ዓ.ም